## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ያለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት

በሲሳይ ተበጀ

አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለM.Aዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ግንቦት 14,1990

# በአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ያለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን
በማስተማር /TEAM/ ለማስተርስ
ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ
ሲሳይ ተበጀ

ግንቦት 14, 1990

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ያለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት

በ

ሲሳይ ተበጀ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | |
| ፈታኝ | |
| ፈታኝ | |

# ምስጋና

ውድ ጊዜያቸውን በመሰዋት ፅሑፉን ደጋግመው በማንበብ፣ በማስተካከልና ምክር በመለገስ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ለዶ/ር ደጀኔ ለታ የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ::

ለጥናቱ መረጃ ማሠባሰቢያ የሚያገለግሉ መጠይቆችን በማረምና አስተያየት በመስጠት ከፍተኛ ትብብር ላደረጉልኝ ለአቶ ይልማ ከበደ፣ ለአቶ አበበ ገ/ፃድቅ፣ እና ለአቶ ሰለሞን ተሠማ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው::

የተለያዩ እገዛዎችን በማድረግ የረዱኝ የአቶ ስምኦን ተ/ሀይማኖት፣ የሲ/ር ታበይን ገድሉና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ዲን አቶ መላኩ ይማም ውለታቸው ከፍተኛና የማይዘነጋ ነው::

በትምህርት ላይ በቆየሁበት ጊዜ ቤተሰብ የማስተዳድር ሃላፊነት በአብዛኛው በመሸከም እኔንም በማበረታታትና የንባብና የፅህፈት አገልግሎት በመስጠት ከፍተኛ እርዳታ ያበረከተችልኝ ባለቤቴ ወ/ሮ ያለም ወርቅ ገ/ህይወት፣ የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ ያደረጉልኝ ወ/ሮ አያልነሽ ሰይፉ፣ አቶ አለሙ አሰፌ፣ የራይመር ቤተሰቦች፣ የአሜሪካን ኤምባሲ ሴቶች ማህበር፣ አቶ አሊጋዝ ከበደ፣ ወ/ሮ ዘርፌ በለው፣ አቶ ወዳጄ አበበ፣ ሚስተር ሀኑና፣ ለወ/ሮ ፀሐይነሽ ካሣው የተለዬ ምስጋና ይገባቸዋል::

በትምህርት ላይ በቆየሁባቸው ግዚያትም ሆነ በተለይ ለዚህ ጥናት በንባብ፣ በፅህፈትና በልዩ ልዩ መልክ እርዳታቸውን ለለገሱኝ ለወ/ሮ አስቴር አሰፋ፣ ለወ/ሮ ይታጠቁ ነጋ፣ ለወ/ሮ የሺ መብራት፣ ለወ/ሮ ሞራ ብራከን፣ ለተማሪ ሰለሞን ይበሉ፣ ለተማሪ አቤል አበበ ፣ ለተማሪ አመሀ ደሣለኝ፣ ለአቶ ክብሮም ሰይፉ፣ ለተማሪ ጥበበ አሉላ፣ ለተማሪ በለጠ ቀኔ፣ ለወ/ሪት ሰዊት ጌታቸው፣ ለተማሪ ህይወት ጥላዬ፣ ለወ/ሪት ራሔል ኤፍሬም ፣ ለተማሪ ሀይማኖት ሲሣይ፣ ለተማሪ ዩሀንስ አብርሀ፣ ለተማሪ ፍሥሀ ካሣ ለወ/ሪት ሪታ ወጋየሁ ንጋቱ፣ ለተማሪ አብነት ሲሳይ፣ ለተማሪ ኤልሳ ዘገዬና ለተማሪ መታሰቢያ ሲሳይ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ::

ለጥናቱ ወደ ውጤት መድረስ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ስሰበስብ ቀና ትብብር ያደረጉልኝ የስርአተ - ትምህርት ዝግጅት፣ ጥናትና ምርምር ተቋም ቋንቋ ቡድን አባላት፣ የአዲስ አበባ መስተዳድር ት/ቢሮ ስታትስቲክስ ክፍል ሠራተኞች፣ እንዲሁም የአብዬት ቅርስ፣ የከፍተኛ 4፣ የወንድይራድ፣ የዳግማዊ ምኒልክ፣ የጥቁር አንበሳና የአቃቂ ከፍተኛና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ርዕሳነ_መምህራን እና መጠይቁን የሞሉልኝ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን በላቀ ደረጃ የሚመሰገኑ ናቸው::

በመጨረሻም ትርፍ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ እያረሙና የሞራል ድጋፍ እየሰጡ በኮምፒውተር ለፃፉልኝ ለአቶ ዳንኤል አበበ፣ ለወ/ት ትዕግስት ኩምሣ እና ለወ/ሮ ቀፀላ መንግስቱ የተለዬ ምስጋናዬ ይድረሳቸው::

# ማውጫ

አርእስት ገጽ

ምስጋና

አጠቃሎ

የሠንጠረዥ ዝርዝር

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ …………………… 1

1.1. የጥናቱ ዳራ …………………… 1

1.2. የጥናቱ አላማ …………………… 3

1.3. የጥናቱ ጠቅሜታ …………………… 4

1.4. የጥናቱ ወሰን …………………… 5

1.5. የቁልፍ ቃላት መግለጫ …………………… 5

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት …………………… 9

2.1 በአሰሳ ቃላትን የማስተማር ዘዴ …………………… 9

2.1.1 የትርጉም ዝምድናዎች …………………… 10

2.1.1.1 ተመሳሳዮች …………………… 10

2.1.1.2 ተቃራኒዎች ……….,……… 12

2.1.1.3 ተካትቶዎች …………………… 12

2.1.2 አብሮነቶች …………………… 13

2.1.3 መዋቅራዊ ፍንጮች ከቃላት ምስረታ አንፃር …………………… 14

2.1.4 አውዳዊ የቃላት ማስተማሪያ ቴክኒኮች ከሁለንተናዊ የቃላት ገፅታ አንፃር …………………… 16

2.1.4.1 እውናዊ አውድ …………………… 16

2.1.4.2 አውዳዊ ነሲብ ስራ …………………… 19

2.2 ቃላትን መማርን በተሳትፎ፣ በጥናትና በትግበራ ክንውኖች የመማር ቴክኒክ …………………… 22

2.3 የቃላት ትምህርት እድገት ሑኢትዮጵያ …………………… 24

አርእስት ገጽ


ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች ...................... 28

3.1 የጥናቱ ዘዴ ...................... 28

3.2 የመረጃ ምንጮች ...................... 28

3.3 የናሙናዎች አመራረጥ ...................... 29

3.3.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ...................... 29

3.3.2 የ 9ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ናሙና አመራረጥ ...................... 29

3.3.3 የ 9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ዝግጂት ተሳታፊዎች አመራረጥ ...................... 30

3.3.4 የ 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፎች ናሙና አመራረና ...................... 30

3.4 የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ...................... 30

3.4.1 የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ...................... 30

3.4.2 ቃለ-መጠይቅ ...................... 33

3.4.3 የ 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ...................... 34

ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ትንተናና ማብራሪያ ...................... 37

4.1 የመረጃ ትንተና ...................... 37

4.1.1. ከመማሪያ መጽሐፉ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...................... 38

4.1.1.1. የመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች የአሰሳ ቴክኒክ ብቃት ...................... 38

4.1.1.2. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ክንውኖች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ብቃት ከቃላዊ አተያይ አንፃር ...................... 46

4.1.2. ከመምህራን መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...................... 58

4.1.3. ከቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...................... 68

4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ...................... 70

4.2.1. ከ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ...................... 70

| አርእስት | | ገጽ |
| --- | --- | --- |


ትንተና የተገኘ ውጤት

4.2.2. ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት …………………. 74

4.2.3. ከቃለ መጠይቅ የተገኘ ውጤት …………………. 76

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ መደምደሚያና መፍትሄ ሀሳቦች …………………. 81

5.1 ማጠቃለያ …………………. 81

5.2 መደምደሚያ …………………. 83

5.3 መፍትሄ ሀሳብ …………………. 86

ዋቢዎች …………………. 88

አባሪዎች …………………. 93

አባሪ ሀ ለ 9ኛ ክፍል መምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ …………………. 93

አባሪ ለ ለፌደራሉ ስርአተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም የቋንቋ ቡድን መሪ የቀረበ ቃለ መጠይቅ ………….;……… 102

አባሪ ሐ በ1984 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመውን የ 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላዘጋጁ የትምህርት ባለሙያ የቀረበ ቃለ መጠይቅ …………………. 104

አባሪ መ የቋንቋ ቡድን መሪው ቃለ መጠይቅ መልስ …………………. 106

አባሪ ሠ የመጽሐፉ አዘጋጅ ባለሙያ ቃለ መጠይቅ መልስ …………………. 110

አባሪ ረ ከ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በናሙናነት የተወሰዱትን ምንባቦችና መልመጃዎች ለመገምገም የተዘጋጀ ዝርዝር መፈተሻ (Checklist) …………………. 113

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት አላማ አድርጎ የተነሣው ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ የዋለውን አማርኛ የመማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ቃላትን መማርን ለመማር መርህ መሠረት ተዘጋጅቶ እንደሆነና እንዳልሆነ በክፍል ውስጥ ክንውኖች ላይ ከሚያደርሰው ተፅእኖ አንፃር መገምገም ነው።

በጥናቱ ሂደት ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በጽሁፍ ትንተና፣ በቃለ መጠይቅና በጽሁፍ መጠይቅ የመረጃ ማሳሰቢያ መሳሪያነት "በአሁኑ ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተመሠረተባቸው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች /Methods/ ቴክኒኮች /Techniques/ ና ስልቶች /Strategies/ ተማሪዎች ቃላትን እንዲማሩ በማስተማር ላይ ያተኮሩ ናቸው?" በሚል መሪ ጥያቄ ስር የሚከተሉትን አላማ ተኮር ጥያቄች ለመመለስ ይሞክራል። ጥያቄዎቹም

1ኛ/ የቃላት መልመጃዎቹ "እያሰላችሁ ተሳተፉ፣ አጥኑና በተግባር ተርጉሙ" የሚለውን ስልታዊ አካሄድ /Pattern/ መሠረት በማድረግ ተማሪዎች አንድ ወጥ የሆነውን ተግባራዊ የቃላት ማስፋፊያ መንገድ እንዲከተሉ ያደፋፍራሉ?

2ኛ/ የቃላቱ አቀራረብ ስልት ትርጉምን ፣የቃላት አጠቃቀምን፣ ምስረታንና የቃላት ሰዋሰውን በተገቢ ስርጭት ለአሰሳ በሚያመች መልክ አካተው ይዘዋል?

3ኛ/ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ የሚገኘው የቃላቱ አቀራረብ በመማሪያ መጽሐፉ መግቢያ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት፣ ክሂልና የእውቀት ዘርፍ አላማዎች ለመተግብር የሚያግዝ ነው? የሚሉት ናቸው።

እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ ገላጭ የምርምር ዘዴን መሠረት በማድረግ የመጽሐፍ ትንተናን፣ የጽሑፍ መጠይቅንና ቃለ-መጠይቅን በመሣሪያነት በጥቅም ላይ በማዋል ለመመርመር ተሞክሯል። በትንተናው መማሪያ መሐፉ ለቃላት አሰሣ፣ ለተሣትፎ፣ ለጥናትና ለትግበራ ክንውኖች የሰጠው ትኩረት በመፈተሻ ዝርዝር ነጥቦች ሲመረመር በጽሑፍ መጠይቁ የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪዎችን ፍላጎት ምን ያህል እንደሚያነሳሱ፣ የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ስልት የተማሪዎችን የክሂልና የቋንቋ እውቀት ለማዳበር የማስቻል አስተዋጽዎ ምን ያህል እንደሆነና በጥቅሉም የመጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በክፍል ውስጥ ተራክቦ ምን ያህል ተጽኖ እንዳሳደረ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ምስክርነት

ተገምግሟል፡፡ በቃለ መጠይቆቹ አማካኝነትም መማሪያ መጽሐፉ በሚዘጋጅበት ወቅት አዘጋጆቹ ለቃላት አመራረጡና አቀራረቡ የተከተሉት ሞዴል እንዳለ(እንደሌለ) እና በአጠቃላይ የትኛውን የቋንቋ ንድፈ ሃሣብ /Theory/ ተከትለው እንዳዘጋጁት በአዘጋጆቹ ምስክርነት ለማጥናት በመሞከር የሦስቱንም መሣሪያዎች ውጤት ለየብቻ ተንትኖ ወደ አንድ ማጠቃለያና መደምደሚያ በማምራት ቋንቋ ከሚባለው ረቂቅ ነገር ምንነት ማብራሪያ ጀምሮ ለማስተማር ከመሞከር ይልቅ ግዘፍ ነስተው ከሚታውቁት ከቃላት መጀመር እንደሚሻል በመፍትሄው ክፍል ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

በዚህ መሰረት ከክለሳ ድርሣናት በተገኙ ቃላትን መማርን በመማር መስፈርትና መርሆች በመጠቀም በተደረገ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት አቀራረብ ከቃላት አጠቃቀም ይልቅ ትርጉም ጠቋሚ የሆኑ ስልታዊ አካሄዶችን ለማስተማር ስለማይሞክር ዘዴዎቹ፣ ቴክኒኮቹና ስልቶቹ ቃላትን መማርን ለመማር የሚያስችል ብቃት ያለው አቀራረብ ይከተላሉ ማለት እንደማይቻል ታውቋል፡፡

የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪዎችን ፍላጎት ስለማያነሳሱና ግልፅ አስተያየትን በመጠየቅ የተማሪዎችን ተሳትፎ ስለማይጋብዙ ወደ ውይይትና ተግባር በመምራት ተማሪዎቹ ከአዳዲስ ቃላት ጋር እንዲተዋወቁ ስለማያደርጉ የጥናት ክንውኖቹ ከተሣትፎ ክንውኖቹ ጋር ስልታዊ ግንኙነት ስለሌላቸው፣ በፈተናአዊ አቀራረብ የተዘጋጁ በመሆናቸው ወደ ትግበራ ክንውኖች ስለማያመሩ፣ የትግበራ ክንውኖቹም በአብዛኛው ወደ ንባብ ክሂል ያደሉና የጥያቄ መመለሻ መንገዳቸው በአብዛኛው በፅሑፍ ይሁን በቃል ተለይቶ ያልታወቀ በመሆኑ፣ ጥያቄዎቹ በአብዛኛው የተማሪዎችን የግል /ነፃ/ አስተያየት ስለማይጠይቁ፣ ተማሪዎች በተማሯቸው ቃላት ከግልጋሎታዊ የቃላት ትርጉም አጠቃቀም ፣ምስረታና ሰዋሰዋዊ ባህሪ አሰሳ በመነሳት ክሂላዊ ተግባራትን እንዲፈፅሙ ስለማይደረጉና ወዘተ ... መልመጃዎቹ በተሣትፎ፣ በጥናትና በትግበራ ክንውኖች አካሄድ ላይ የተመሰረቱ አለመሆናቸው ተደርሶበታል፡፡ የቃላት አቀራረቡ ከቃላት ግልጋሎታዊ ሚና ይልቅ ለትንተና የበለጠ ትኩረት በመስጠት ትንተናዊ የቃላት ትርጉም ዘርፎችን አጠናክሮ ስለሚያቀርብ የቃላት ዘርፎችና ይዘቶችን በተገቢ ስርጭት ባለማካተቱ ቃላትን መማርን ለመማር የማያስችል መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የመማሪያ መፅሃፉ የቃላትን የክሂልንና የእውቀት ዘርፍ አቀናጂነት ሚና በአግባቡ ስለማያሳይና ቃላትን በክሂላዊነት ቴክኒክ ስለማያቀርብ የመፅሀፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ስልት ቃላትን መማርን በማስተማር ላይ የተመሰረተና ተገቢ ብቃት ያለው ነው ለማለት እንደማይቻል ግኝቱ ይጠቁማል፡፡

## የሠንጠረዥ ዝርዝር


| ሠንጠረዥ | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | የመምህራን መጠይቅ ስርጭት ......................... | 33 |
| 2. | በ1984 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት መልመጃዎች መግለጫ ከአሰሳ ቴክኒክ ብቃት አንፃር ......................... | 40 |
| 3. | የ1984 ዓ.ም. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የክሂልና የእውቀት ዘርፍ መልመጃዎች የጥያቄ አቀራረብ መግለጫ ......................... | 47 |
| 4. | የ1984 ዓ.ም. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መመሪያ መጽሐፍ የክሂልና የእውቀት ዘርፍ መልመጃዎች የመልስ አሰጣጥ መግለጫ ......................... | 51 |
| 5 | የ1984 ዓ.ም. ዕትም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ናሙና ጥያቄዎች በየምድብ ክሂላቸው፣ እውቀት ዘርፋቸው፣ ምንባባቸው፣ መልመጃና ጥያቄ ቁጥራቸው አመልካች ሠንጠረዥ ......................... | 54 |
| 6 | የ1984 ዓ.ም. የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሕፍ የጥናት ክንውኖች መግለጫ ......................... | 58 |
| 7 | የመምህራንን የግል ሁኔታ በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ ......................... | 59 |
| 7.1 | መጠይቁን የመለሱ መምህራን በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛን ያስተማሩባቸው አመታት ብዛት ......................... | 59 |
| 7.2 | መጠይቁን የሞሉ መምህራን በትምህርት ደረጃ ......................... | 60 |

| ሠንጠረዥ | | ገጽ |
|---|---|---|
| 7.3 | መጠይቁን የመለሱ መምህራን ከ1985 ዓ.ም. ወዲህ ሥራ ላይ የዋለውን የ9ኛ ክፍል አማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ በመጠቀም አማርኛን ያስተማሩባቸው አመታት ብዛት | ......................... 60 |
| 7.4 | መጠይቁን የመለሱ መምህራን ስልጠና | ......................... 60 |
| 8. | የቃላት መልመጃዎቹ አቀራረብ ባህርይና የክፍል ሥራ ክንውንን በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ መልሶች መግለጫ | ......................... 61 |
| 8.1 | የቃላት መልመጃዎቹ አቀራረብ ባህርይ | ......................... 61 |
| 8.2 | የተማሪዎች ተራክቦ | ......................... 62 |
| 8.3 | የቃላት መልመጃዎች የአስተራረም ሁኔታ | ......................... 63 |
| 9. | የቃላት መልመጃዎቹን ለመሥራት ተማሪዎቹ ያላቸውን ፍላጎትና ችሎታ በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ መልሶች | ......................... 63 |
| 10. | የቃላት መልመጃዎቹ ክሂልን ስለማዳበርና አለማዳበራቸው የመምህራን መጠይቅ መግለጫ | ......................... 64 |
| 11. | የቃላት መልመጃዎቹ የእውቀት ዘርፎችን የሚያዳብሩ ስለመሆናቸውና ስለአለመሆናቸው የመምህራን መጠይቅ መልሶች መግለጫ | ......................... 65 |
| 12. | በመማሪያ መጽሐፉ የጎላ ትኩረት ላልተሰጣቸው የቃላት ትምህርት የአሰሳ ይዘቶች መምህራኑ የሰጧቸው ትኩረት መግለጫ | ......................... 66 |
| 13. | የመማሪያ መጽሐፉን የአዳዲስ ቃላት ማስተማሪያ ስልቶች ትግበራ በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ መልሶች መግለጫ | ......................... 67 |
| 14. | ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ባለሙያዎች አጠቃላይ መረጃ | ......................... 69 |

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በመሠረቱ አንድን ቋንቋ ለማስተማር መማሪያ መፃህፍት ከመዘጋጀታቸው በፊት የስህተት ትንተና (Error analysis) ማድረግ ተገቢ ቢሆንም ይህ በአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት መከናወኑን ወይም አለመከናወኑን ወደ ማጣራቱ ስንመጣ አማርኛ ቀደም ሲል በሚሲዮን፣ በኋላም በመንግስት ት/ቤት በመደበኛ ትምህርትነት ከአንድ መቶ አመታት ላላነሰ ጊዜ ሲሰጥ ቢቆይም ቋንቋውን ለማስተማር ታስቦ በተለይ የተዘጋጁ መጻህፍትን መጠቀም ከተጀመረ ገና ሁለት አስርት አመታት መቆጠራቸውንና በዝግጅቶቹም ወቅት የፍላጐት አሰሳ አለመካሔዱን በመፃሕፍቱ ላይ አጠቃላይ ጥናት ካደረጉ አጥኚዎች እንረዳለን፡፡ አስፋው አመና (1975)፣ በክሬጌታ (1975)፣ ሰለሞን ግዛው (1978)፣ ደሴ ሙሉ ዓለም (1972)፣ አያሌው አስፋው (1985) ና በየነ ማሞ (1985)፣ ጌታቸው አዱኛ (1986)፣ እንደሚጠቁሙት ከሀያ አመታት በፊት በመማሪያነት ሲሰራባቸው የቆዩት ቅድመ 1966 አብዮት የአማርኛ መማሪያ መፃሕፍት ደራሲያን ለአጠቃላይ ትምህርት በገበያ ላይ እንዲውሉ ያዘጋጇቸው ነበሩ፡፡ አስፋውና ሞርሰን (1976፡ 448)፣ እንደሚያስረዱት መፃሕፍቱ ለማስተማሪያነት ተመርጠው የተመደቡ እንጂ በጥናት የተዘጋጁ ባለመሆናቸው እርስ በእርሳቸው ይዘታዊ ግንኙነት የሌላቸው፣ የመጀመሪያው ክፍል ለሚቀጥለው ክፍል መሠረት የማይጥል፣ በመካከላቸው ተከታታይነት የማይታይባቸውና ተማሪዎቹ የመጀመሪያውን ክፍል ትምህርት ሣይማሩ የሚቀጥለውን ክፍል ቢማሩ አዲስ ነገር ስለማያኙበት የትምህርቱ አሰጣጥ ተለጣጣቂነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል የሚሉት አስተያየቶች የስህተት ትንተና አለመደረጉንና ለቃላት ትምህርትም ትኩረት አለመሰጠቱን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

የስህተት ትንተናንና የቃላት ትምህርትን በአንድ ላይ በዚህ ቦታ ማንሳት ያስፈለገው በአሁኑ ጊዜ የተማሪዎች የቋንቋ ችግር በአብዛኛው የቃላት መሆኑን ዊልኪንስ (1978) ኮርኑ (1978)፣ ሮድስካና ሌሎችም (1985) በስህተት ትንተና ላይ ያተኮሩ አጥኚዎች ተማሪዎች ምን መማር እንዳለባቸው ለመወሰን የስህተት ትንተና ማድረግ አስፈላጊ ነው በሚል እምነት በአካሔዱት ተደጋጋሚ ጥናት በአሁኑ ጊዜ ከመዋቅር ይልቅ የቃላት ችግር በተማሪዎች ላይ ጉልቶ እንደሚታይ በመጠቆማቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ዊልኪንስ (1972) ይህንኑ የቃላትን የቋንቋ ትምህርት ማዕከላዊ ሚና ሲገልጹ ያለ ሰዋሰው በጣም ጥቂት ነገሮችን ማስተላለፍ ሲቻል ያለቃላት ግን ምንም ማለት እንደማይቻል ይጠቁማሉ፡፡ ከቅድመ አብዮት የአማርኛ መጻሕፍት የምናየው የይዘት ግንኙነት አለመኖር፣ የመጀመሪያው ለሚቀጥለው ክፍል መሠረት

አለመጣል፣ የተከታታይነትና የተለጣጣቂነት አለመኖር ችግርም ይህንኑ በቃላት ላይ መደረግ የሚገባውን ትኩረት የሚጠቁም ነው፡፡

በ1970 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መፃሕፍት ተዘጋጅተው ይቅረቡ እንጂ ጥራታቸውና ለተመደቡበት የክፍል ደረጃ መጣኝነት፣ በስርዓተ ትምህርቱ የተጠቀሱትን የቋንቋ ክሂሎችና የቃላት ትምህርት የተካተቱባቸውን የእውቀት ዘርፎች በማዳበር ከቋንቋ ትምህርት ግብ አስመችነት አንፃር ሲገመገሙ ቀደም ሲል የጠቀስናቸው አጥኚዎች በአዎንታዊ አይን አይመለከቷቸውም፡፡ ከእነዚህም መሀል ለምሣሌ አያሌው አስፋው (1985፡53) መማሪያ መፃሕፍቱ በቅድመ 1966 አብዮት ይሰራባቸው ከነበሩት የሚለዩት ለቋንቋ ማስተማሪያ ተብለው መዘጋጀታቸውና ምንባቦችና መልመጃዎችን በመያዛቸው መሆኑን ይመሰክራሉ፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ በየነ (1985) የተለያዩ የመመረቂያና የሲምፓዚየም ጥናታዊ ጽሑፎችን በመጥቀስ ያብራሩት ይህንኑ እውነት የሚያጐላ ነው፡፡ ይህም የመጀመሪያዎቹ የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት በስህተት ትንተና ላይ ተመስርተው የተዘጋጁ አለመሆናቸውንና በአሁኑ ጊዜ በቋንቋ ትምህርቶች ውስጥ ከፍተኛ ግምት ለሚሰጠው ለቃላት ትምህርት ትኩረት አለመሰጠቱን መገመት ያስችላል፡፡

በቀጣይነት ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አማርኛ መማሪያነት ተዘጋጅተው አሁን የሚሰራባቸውን መፃህፍት በሚመለከት የአጥኚዎች ግኝት በአብዛኛው አሉታዊ ገጽታን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህም መሀል በየነ (1985) የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች አራቱን ክሂሎች የማያዳብሩ መሆናቸውን በጥናት ውጤታቸው የጠቆሙት ለአብነት የሚጠቀስ ነው፡፡ አምባዬ ፀሐዬ (1987:11)ም፣ ከመርሀ ትምህርት እስከ መማሪያ መፃሕፍቱ በዘመናችን የሚሰራባቸውን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአማርኛ ትምህርት መሣሪያዎች ሁኔታ ሲገልጹ ከቋንቋው የትምህረት አላማዎች 40 % ያህሉ ግልጽነት እንደጐደላቸውና የተማሪዎችን የባህሪ ገጽታ እንደማያመለክቱ፣ 50% ትኩረታቸው በነቢብ (congnitive) ይዘት ላይ ያተከረ በመሆኑ የተማሪውን ሁለንተናዊ የእሴት (affective) እና የክህሎት (psychomotor) ባህሪ ገጽታ ይዘት ሚዛናዊ ትኩረት እንደማያመለክቱ፣ ቀሪው 50% የነቢብ ይዘቱም ቢሆን ከአራቱ የቋንቋው ክሂሎች አንጻር ሲታይ ሚዛናዊ ትኩረት እንዲኖረው ካለማድረጉም በላይ ለአሰካክና ለቃላት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑ የምንባቦች ይዘት ከተማሪው፣ ከኅብረተሰቡና ከአካባቢው ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር ውህደት ማጣቱና የቃላት ይዘቱም 29.2% ብቻ በቋንቋው ተናጋሪዎች ዘንድ በዘወትር ጠቀሜታ ላይ የሚውሉ (frequent words) መሆናቸውን በተደረገው ጥናት ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ ይህም የሚያሳየው መፃህፍቱ በዘፈቀደ እንጂ በስህተት ትንተና ላይ ተመስርተው የተዘጋጁ አለመሆናቸውን ነው፡፡

ሀ. ስለሆነም የ9ኛ ክፍልን ጨምሮ በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ላይ እስካሁን ከተካሄዱት ጥናቶች እንደምንረዳው በአብዛኛው በቋንቋው ትምህርት አጠቃላይ ሁኔታና በጥቂቱ ደግሞ በክሂሎች ላይ ያተኮሩ እንጂ በተለይ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ላይ የቃላት ትምህርት ብቃት ምርመራ ያልተካሄደ በመሆኑ፡፡

ለ. በውጭ ሀገር ቋንቋዎች ትምህርት ላይ በቅርቡ የተካሄዱ የጥናት ውጤቶ ች እንደሚጠቁሙት የተማሪዎቹ የቋንቋ ችግር ጉልቶ የሚታየው በቃላት ችሎታ ማነስ ረገድ በመሆኑና ከማንኛውም የቋንቋ ገጽታ ይበልጥ በቃላት ላይ ማተኮር ለሌሎች ገጽታዎች ቅንጅት መሠረት በመሆኑ ለቋንቋ ጥናት ውጤት ስኬታማነት የተሻለ መሠረት ስለሚጥል ይህ ጥናት በ9ኛ ክፍል ደረጃ አማርኛን ለማስተማር እንዲያገለግል የተዘጋጀውን መጽሀፍ የቃላት ትምህርት ብቃት ከዘመናዊ አመለካከቶች አንፃር ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመመርመር በመሞከር ጠቃሚ መፍትሄ እንደሚጠቁም ይታመናል፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ለጥሩ ወይም ለመጥፎ የክፍል ውስጥ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ “ቃላትን በዝርዝር ያስተምራል ወይስ ቃላትን መማርን ነው የሚያስተምረው?” የሚሉትን ጥያቄዎች በጥቅሉ ይመልሳል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ ጥናቱ

“በአሁኑ ጊዜ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ9ኛ ክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተመሠረተባቸው ዘዴዎች / methods/፣ ቴክኒኮች /techniques/ እና ስልቶች /Strategies/ ተማሪዎች ቃላትን እንዲማሩ በማስተማር ላይ ያተኮሩ ናቸው?” በሚለው መሪ ጥያቄ ስር ከክለሳ ድርሳናት በተገኙ መፈተሻዎች / Check List/ በመመርመር የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች በመሪ አላማነት ለመመለስ ይሞክራል፡፡

ሀ. የቃላት መልመጃዎቹ እያሰሳችሁ ተሳተፉ፣ አጥኑና በተግባር ተርጉሙ የሚለውን ስልታዊ አካሔድ መሠረት በማድረግ ተማሪዎች አንድ ወጥ የሆነውን ተግባራዊ የቃላት ማስፉፊያ መንገድ እንዲከተሉ ያደፋፍራሉ?

ለ. የቃላቱ አቀራረብ ስልቶች ትርጉምን፣ አጠቃቀምን፣ ምሥረታንና የቃላት ሰዋሰውን በተገቢ ስርጭት አካተው ይዘዋል?

ሐ. በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው የቃላት አቀራረብ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት፣ የክሂልና የእውቀት ዘርፍ አላማዎች ለመተግበር የሚያግዝ ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ጥናቱ እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች በመመለስ የዘጠነኛ ክፍልን የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት አቀራረብ ሁኔታ በማጥናት መፍትሔ ለመጠቆም ይሞክራል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

የመማሪያ መጽሀፉን የቃላት አቀራረብ ገንቢነት ባለው ሁኔታ ማጥናት የማስተማሪያ መሣሪያዎችንና የትምህርት ዘዴዎችን ለማሻሻል ከመርዳቱም በላይ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶችን በማሳደግ ያደጉት ስልቶች በፈንታቸው በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ጠቀሜታ የጐላ እንዲሆን ያግዛሉ፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ስላሉት አስፈላጊ እንደሚሆን በአጥኚው ይታመናል፡፡

ሀ. የሀገራችን የስነ ልሣን ተመራማሪዎች ከመዋቀር ባሻገር ለስነ ትርጉም፣ ለስነ ልቦናና ባህላዊ ሁኔታዎች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ስነ-ትምህርታዊ (pedagogic) የቋንቋ ትምህርት እገዛዎችን እንዲያደርጉ ለመጠቆም፣

ለ. ለወደፊቱ የሚዘጋጀው የ 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍም ሆነ ሌሎች መሰል መፃህፍት የተሻሉ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶችን በመያዝ እንዲጠናከሩ የተወሰነ እገዛ በማድረግ ለፌድራሉ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም ጠቃሚ ሀሳብ ለማቅረብ፣

ሐ. ለመምህራን ስልጠና የሚረዳ ጠቃሚ ሀሳብ በማቅረብ የአማርኛ ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ይበልጥ የተቃና ለማድረግ በሚደረገው ጥረት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከትና፣

መ. በማስተማር ተግባር ላይ ለሚገኙ መምህራን የአተገባበር ጥቆማ ለማድረግ፡፡

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት አቀራረብ ቃላትን መማርን በመማር ዘዴዎች (methods)፣ ቴክኒኮች (techniques) እና ስልቶች (Strategies) ላይ የተመሠረተ መሆን አለመሆኑን መመርመር ነው፡፡ በዚህም መሠረት አፍ ፈች ህፃናት በቋንቋ ለመዳ ወቅት የሚጠቀሙባቸውን የቃላት አፈጣጠር፣ አደረጃጀት፣ ህግጋትና ማህበራዊ አጠቃቀሞች ከክሂልና ከቋንቋ እውቀት ዘርፎች ጋር አቀናጅቶ ከስነ-ልቦናዊ፣ ከተግባራዊና ማህበራዊ ስነ ልሳን ዘርፎች የጥናት ግኝት በመውሰድ "እየተሳተፋችሁ፣ እያጠናችሁና እየተገበራችሁ በማሠስ ቃላትን ተማሩ" በማለት ምሁራን ያስቀመጧቸውን መስፈርት በመጠቀም የመጽሐፉን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ይመረምራል፡፡ በመሆኑም ጥናቱን ለማካሔድ በሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪና ሰፊ ጊዜ ምክንያት ከላይ ከተጠቀሱት ከአሰሳ፣ ከተሳትፎ፣ ከጥናትና ከትግበራ የቃላት ብቃት መገምገሚያ መርሆዎች ውጭ መካተት የሚችሉ ሌሎች የቃላት ትምህርት መርሆዎች በዚህ ጥናት አልተካተቱም፡፡

## 1.5 ቁልፍ ቃላት

ምስያዎች /Analogy/፡ በሁለት ነገሮች መሀል የሚደረግ ከፊል ተመሣሣይነት ወይም ንፅፅር፣ ምሳሌ ልብና ቧንቧ ምስያ አላቸው ብንል የሚያመሣሥላቸው ጉዳይ ፈሳሽ መርጨታቸው እንጂ ሌላው ሁኔታቸው አይደለም /ክሪስታል 1991፡ 17/ ፡፡

ርዴት /Comprehension/፡ በቀጥታና በግል ግንዛቤ እውቀት ደረጀዎች አንብቦ እና አዳምጦ የመረዳት ተግባር

ቀጥታ ጥያቄ /Question of litral Comprehension/፡ ከምንባብ ቀጥታ ቃል በቃል በመውሰድ መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች / ኑታል፣ 1982፡132/

ቅጠላ /Affixation/፡ በቃል ግንድ ላይ በስተመነሻ፣ በስተመድረሻና በስተውሥጥ ጥገኛ ምእላዶች የመጨመር ሂደት /ክሪስታል 1991፡ 11- 42/

ተለዋጭ /Metaphor/፡ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ አንድን ነገር ወይም ሰው ተክቶ በጥቅም ላይ የሚውል ዘይቤያዊ ቃል፣ ምሳሌ፣ "አንበሳ ነህ" ቢባል አንበሳ ለተነጋሪው ጉብዝና መግለጫ በመሆን የገባ ነው፡፡ /ሪቻርድስ፣ 1987፡179/፡፡

የተሣትፎ ክንውን /engagment activity/፡ የተማሪዎችን ፍላጐት በትምህርቱ እርዕስ እና ከርእሱ ጋር በተገናኙ ቃላት ላይ እንዲነሣሣ በማድረግ፣ ወደ ውይይት በመምራት፣ የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም በተሣትፎ እንዲረዱ በማድረግ፣ ሀሣብ እንዲሰጡ፣ መረጃ እንዲያወዳድሩና ወዘተ... በማደፋፈር ቃላትን ለጥናት የምናመቻችባቸው ክንውኖች /ሀርመርና ሮዝነር፣ 1991፡ix/፡፡

ተካትቶዎች /hymonyms/፡ በቃላት መሀል ያለውን በትርጉም የመካተት ግንኙነት የሚያመለክት ነው፡፡ መካተቱ /ሀ/ በውስንና በጠቅላይ፣ ምሳሌ፡- ትርንጉን፣ ብርቱካንን ወዘተ በፍራፍሬ ስር፣ /ለ/ በተወሰነና ባልተወሰነ፣ ምሳሌ፡- ቡናን፣ ለስላሳ መጠጥን፣ አልኮል መጠጥን፣ ወዘተ በሻይ ስር በማካተት ቃላትን በተዛምዶ ለማስተማር የሚያስችል የትርጉም ግንኙነት /ሀርመርና ሮዝነር፣ 1991-13/፡፡

የትርጉም ዝምድናዎች /Sense relations/፡ እርስ በርስ በመተካካት አለያም (በተወሰነ የትርጉም ሁኔታዎች ተመሳስለው በሌላው በመለያየት)፣ በመቃረንና በመካተት ቃላት በስነ ትርጉማዊ ውስብሰብ ግንኙነታቸው የሚደራጁበት የቃላት ማስተማሪያ ቴክኒክ፣ ምሳሌ፡ - ተመሳሳይ፣ ተቃራኒና ተካትቶ በሚል ቃላት በየአይነታቸው በቀጥታ ወይም ተዋረዳዊ ግንኙነታቸው /Paradigmatic relations/ እየተቧደኑ የሚጠኑባቸውን ስልቶች ያካተቱ /ሪቻርድስ 1987-180/፡፡

የትግበራ ክንውኖች /activating activities/፡ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ በተሳትፎና በጥናት ክንውኖች የተጠኑ ቃላትን በፈጠራ በጥቅም ላይ በማዋል ሙከራ የሚደረግባቸው የክንውን አይነቶች ሲሆኑ እነርሱም ቃላትን በአርዕስት መልክ በማስቀመጥ በትረካ መተግበርን፣ ምልልሶች፣ ገለፃዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች ወዘተ መፃፍ፣ ቃላቱን ተጠቅሞ ትችት መስጠትን፣ ወዘተን የሚያጠቃልሉ ክንውኖች፡ /ሀርመርና ሮዝነር፣1991፡X/፡፡

አሰሳ /exploration/፡ የቃላትን ሙሉ ትርጉም ለማወቅ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ስነ ልቦናዊ፣ ማህበራዊና መዋቅራዊ የቃላት ገፅታዎችን ለመማር ተማሪዎች በራሣቸው ፍላጐት /ተነሣሽነት/ ቃላትን የሚማሩበት ዘዴ /ሀርመርና ሮዝነር 1991:viii/ ፡፡

የቃላት አብሮነት /Collocation/፡ ቀጥተኛ የሆነ የፅንሰ ሀሳብን ግንኙነት ከቃሉ ፍቺ አኳያ የሚያሳይ፣ ከሌላው ቃል ጋር ባለው የአገባብ ዝምድና ላይ ብቻ የተመሰረተ የቃላት ጐናዊ ቁርኝት /Syntagmatic relation/ የቃላት አጠቃቀም ዘርፍ አካል የሆነ ቅደም ተከተላዊ ወይም አወቃቀራዊ ግንኙነት /ታይለር፣ 1990፡2 ፣ ሪቻርድ፣ 1987፡177/፡፡

የግል ግንዛቤ (ማገናዘብንና ማቀናበርን) (involving reorganization or reinterpretation)፣ መመርመርን (inference)፣ መገምገምን (evaluation) እና የግል አስተያየትን (Personal response) የሚጠይቁ፣ በጥቅሉ በአንቀ ውስጥ የሚገኘው ሐሳብ ያታው (ጠባዩ) የታሪክ ወይም የሌላ ጉዳይ ከሆነ ዋናውን ሐሳብ ለመለየት አንቀፁ ምን ፍሬ ነገር፣ ትርጉምና ዋጋ እንዳለው ለማስተዋልና አነቀፁ በውል ከታየ በኋላ አንባቢ ከግል ሕይወቱ ጋር እንዲያገናዝብ የሚያግዙ ጥያቄዎች የሚካተቱበት፣ የምንባቡን ሐሳብ ተከትሎ መደምደሚያውን የመስጠት፣ በምንባቡ ውስጥ ያሉትን የአጻጻፍ ሥልቶች የመረዳትና የምንባቡን አዝማሚያ የመለየት፣ ሐፊው በምን ምክንያት እንደፃፈ፣ ፍላጎቱ ምን እንደሆነ የመለየት እውቀትን የሚያካትት (ዳቪስ፣ 1983: 236)፣ ወደ አጠቃላይ የምንባቡ ፍሬ ሐሳብ የሚያሸጋግሩ፣ ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር የሚዛመዱ፣ የቋንቋውን ክሂሎች ቅንጅት የሚጠብቁና መምህራን ብቻ ሳይሆኑ ተማሪዎች የራሳቸውን አስተያየት የሚያንፀባርቁባቸው ሁኔታዎች የተካተቱባቸውን ጥያቄዎች የያዘ ጋርሌት፣ (1981 : 10)፣ ዊልያም፣ (1984፣12)፣ የተለያዩ ሐሳቦችን ከማንባቡ በማውጣት የተጠቃለለ ሐሳብ እንዲያቀርቡ የሚያግዙ፣ በምንባቡ ውስጥ ያሉ ዐረፍተ ነገሮችን ከመገንዘብ በተጨማሪ አጠቃላይ የምንባቡን ፍሬ ሐሳብ እንዲረዱ የሚያደርጉ፣ የምንባቡን አጠቃላይ ፍሬ ሐሳብ በዝርዝር ለማግኘት የግድ ምንባቡን በጥልቀት እንዲመረምሩ የሚያደርጉ፣ ምንባቡን አንብበው አጠቃላይ ፍሬ ሐሳቡን በመገንዘብ የራሳቸውን አስተያየት እንዲሰጡ የሚጋብዙ፣ የፀሐፊውን አቀራረብ፣ የምንባቡን ተአማኒነት፣ ሥነ-ጽሑፍ ከሆነ አተራረኩን፣ ወዘተ... ለመገምገም የሚያስችሉ የጥያቄ ባህሪ ያላቸው፣ ደራሲው የሰጠውን ሀሳብ መልሶ ለማንፀባረቅ የሚጋብዙ ሳይሆኑ የተማሪውን የግል አስተያየት ወይም አመለካከት የሚጠይቁ የርዴት አጠያየቅ ሥልቶች የተካተቱበት የጥያቄ ዓይነት (ናታል፣ 1982: 132)

**የቃላት ጥመራ/Compounding/፡** ሁለት የተለያዩ ቃላትን በማዋሀድ /በማጣመር/ አዲስ ቃል የመፍጠር ሂደት /ሪቻርድስ፣ 1987፡180/፡፡

**የጥናት ክንውኖች /Study activities/፡** እርዕሱ ያስተዋወቃቸውን ቃላት ይበልጥ ዘርዘር ባለ ሁኔታ ለማሰስ የተዘጋጁ ክንውኖች፣ ምሳሌ፡- በቃላት ሠንጠረዥ መጨረስ /በምስረታና በቃላት አብሮነት/፣ ክፍት ቦታ መሙላት፣ ማዛመድ ና ቃላትን መወያዬት፣ ወዘተ ክንውኖችን የሚያካትት /ሀርመርና ሮዝነር፣ 1991፡ix/፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. በአሰሳ ቃላትን የማስተማር ዘዴ

1980ዎቹ አመታት በተደጋጋፊ አቀራረብ/Cumulative - Approach/ የቃላት ትምህርት ማስተማር ሒደት የበላይነት የተቀዳጀባቸው፣ በመማር ማስተማር የክፍል ውስጥ ክንውን ተማሪዎች ወደ ማዕከላዊነት ደረጃ የተሸጋገሩባቸው፣ ቃላት እንደ ቋንቋ ክሂልና ተግባቦታዊ አላማዎችን ግብ ማስመቻ መሳሪያዎች ተደርገው የተቆጠሩባቸውና ለውጥ የተካሔዱባቸው አመታት ነበሩ፡፡ በነዚሁ አመታት ብዙ ምሁራን የቃላትን ሁለንተናዊ ገፅታ ከመተንተናቸውም በላይ ይህንኑ አሠሣዊ አተያይ በቃላት መማር ውስጥም ለማካተት ሞክረዋል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ የቃላት ትምህርት በመማር ማስተማር ሒደት ውስጥ ትርጉም ባላቸው ተግባቦታዊ ክንውኖች ተማሪዎችን የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባዋል በሚለው ሐሳብ ብዙ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ ማካርቲ፣ /1990፡121/ እንደሚሉት "የቃላት ትምህርት ስኬት ከሁሉም በላይ የሚወሰነው በተማሪዎችና በመምህራን እንዲሁም በተማሪዎቹ መሀል እርስ በርስ በሚደረግ ተራክቦ፣ ተማሪዎቹ አዳዲስ ቃላትን ለማወቅ በሚፈፅሙአቸው ተግባራትና ልምምድ ነው፡፡" እንደ ጌርነስና ሬድማን /1986፡76/ እምነት ተማሪዎችን ትርጉም ባለው የቃላት ትምህርት ማሳተፍና የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም በገዛ ራሳቸው እንዲማሩ የሚያስችል ስልጠና መስጠት ሁለት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ይኼውም፡-

ሀ. ተማሪዎች በሚማሩት ነገር ላይ ሐላፊነት እንዲሰማቸው ያደርጋል፣

ለ. ቃላት ማስፋፋትን አስመልክቶ ለተማሪዎች የግል ፍላጐት ትኩረት ስለሚሰጥና እያንዳንዳቸው የሚፈልጓቸውን ቃላት የራሳቸው አድርገው በመቁጠር እንዲማሩዋቸው ስለሚረዳ ፍላጐትን፣ ዕቅድንና አላማን ለማሳካት ያስችላል፡፡

በአጠቃላይ በአሰሳ ቃላትን የማስተማር ስልት የሚያተኩረው የቃላትን ትርጉም በተናጠል በማስተማር ላይ ሳይሆን በቃላት ውስብስባዊ ግንኙነት ተግባቦታዊ ክንውኖችን መሠረት ባደረገ፣ የተማሪዎችን ፍላጐትና ትኩረት በማነሳሳት ተግባር ሆኖ የሚከተሉትን የቃላት ሁለንተናዊ ገፅታዎች ያካትታል፡፡

### 2.1.1. የትርጉም ዝምድናዎች /Sense Relations/

የትርጉም ዝምድና በቃላት መሀል የሚገኝን ስነ-ትርጉማዊ ግንኙነት መሰረት ያደረገ ውስብስብ የቃላት ግንኙነት ነው፡፡ በቃላቱም መሐል የሚኖረው ግንኙነት አንድም እርስ በርስ በመተካካት አለያም በተወሰነ የትርጉም ሁኔታዎች ተገናኝተው በሌላዎቹ በመለያየት ላይ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህንንም ማካርቲ /1990፡16/ ሲገልፁት የትርጉም ዝምድናዎች በተለያዩ ቃላት መሐል ያሉ በቀጥታ የቃላት ግንኙነት ላይ ተመስርተው የተገነቡ የቃላት ዝምድናዎች መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ ዝምድና የተባለውም ግንኙነታቸውን ከነጠላው ቃል ፍቺ ለመለየት ነው፡፡ ምሁራን የቃላት ዝምድናዎችን ለአዳዲስ ቃላት ትምህርት ማደራጃ መርህነት እንድንጠቀምባቸው ሲጠቁሙ ቃላትን በስነ -ትርጉማዊ ግንኙነታቸው ማደራጀት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ዋንኛ ጉዳይ ነው ይሉናል፡፡

ብዙ መምህራን ቃላትን ለማስተማር አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የትርጉም ዝምድናዎች ተመሳሳይ፣ ተቃራኒና ተካትቶ ናቸው፡፡

#### 2.1.1.1. ተመሣሣዮች /Synonyms/

ተመሳሳይነት አንድ መሆንን፣ አለመለያየትን ሲያመለክት ሁለት ቃላት የአንድ ነገር ወኪል እንደሆኑና በፍቺም ልዩነት የሌላቸው መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ሆኖም ጌርንስና ሬድማን /1986፡15/ ፣ ሀርመርና ሮዝነር /1991፡19/ ሁለት ነገሮች ሙሉ በሙሉ ይመሳሰላሉ ብሎ ማሰብ አላዋቂነት ነው ይላሉ፡፡ ማካርቲ /1990፡17/፣ ተመሳሳይ ቃላት እርስ በእርስ ከሚለያዩባቸው ጉዳዮች መሀል አምስቱን እንደሚከተለው ያቀርባሉ፡፡

ሀ. ቃላት በትርጉም የሚቀራረቡ ቢሆኑም በአብሮነት ግን ከተመሳሳያቸው ጋር አብረው አይገቡም፡፡

ለ. ቃላት በትርጉም የሚቀራረቡ ቢሆኑም በአወቃቀር ባህሪያቸው ግን ይለያያሉ፡፡

ሐ. ቃላት በትርጉም የሚቀራረቡ ቢሆኑም በሚገቡበት አውድና በጥቅም ላይ በሚውሉበት ሁኔታ ግን ይለያያሉ፡፡

መ. ቃላት በትርጉም የሚቀራረቡ ቢሆኑም በአካባቢያዊ ስርጭቶቻቸው /ቀበልኛ በመሆንና ባለመሆን/ ግን ይለያያሉ

ሠ. ቃላት በትርጉም የሚቀራረቡ ቢሆኑም ከአገልግሎት ውጪ በመሆንና ባለመሆን ግን ይለያያሉ፡፡ /ጌርንስና ሬድማን፣ 1986፡15/፡፡

እንደነ ካርተርና ማካርቲ /1988-29/ አባባልም ተመሳሳዮች የሚባሉት የተካትቶዎች ሁለት ጉንዮሽ ገጽታ ያላቸው የቃላት ሥብስብ ናቸው፡፡ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን ማግኘት አልፎ አልፎ ብቻ የሚከሰት ጉዳይ መሆኑን ምሁራኑ ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳዮች መሀል ከሚታዩት ሌሎች ልዩነቶች ጥቂቶቹ:-

ሀ. አንዱ ከሌላው ይበልጥ አጠቃላይነት ያለው መሆኑ፣

ለ. አንዱ ከሌላው ይበልጥ ሀይል ያለው መሆኑ፣

ሐ. አንዱ ከሌላው ይበልጥ ስሜታዊ መሆኑ፣

መ. አንዱ ከሌላው ይበልጥ ገላጭ /ተቺ/ መሆኑ፣

ሠ. አንዱ ከሌላው ይበልጥ ሙያዊ መሆኑ፣

ረ. " " " ስነ-ፅሁፋዊ መሆኑ፣

ሰ. " " " የንግግር ቋንቋ መሆኑ፣

ሸ. " " " የህፃን ቋንቋ መሆኑ፣

ቀ. " " " ቀበልኛ /ዘዬ ቃል/ መሆኑ፣

የሚጠቀሱ ልዩነቶች ናቸው፡፡

ይህም የሚያሳየው ቃላት ምንጊዜም በአንድም ሆነ በብዙ አቅጣጫ የተለያዩ መሆናቸውን ነው፡፡ በአብሮነት ለመለያየታቸው ምሣሌ የሚሆነን ጋገረና ደፋ ለእንጀራና ለዳቦ በተለያየ ሁኔታዎች መግባታቸው ነው፡፡ ከዚሁም ጋር መዋቅራዊ አገባብ በሁለት ቃላት ተመሣሣይነት ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ በእርግጥ በተወራራሽነት የሚተካኩ ተመሣሣዮችም አሉ፡፡ ምሳሌ:- ድስቱን ከደነች /ገጠመች/፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መጠቀና ጠለቀ ለሃሳብ በቅርፅ ተቃራኒ ቢመስሉም በይዘት ግን ተመሳሳዮች ናቸው፡፡ ነገር ግን ለውሃ፣ ለጉድጓድ፣ ለሸለቆ ወዘተ ጥልቅ የሚለው ቃል ለሃሳብ ከምንጠቀምበት ትርጉም ተለይቶ ዝቅታን ሲያመለክት በተቃራኒው የጠለቀ ሃሳብ ስንል ፍቺው የመጠቀ ሃሳብ ማለት ስለሚሆን እላይ እንደገለፅነው ዝቅተኝነትን ሳይሆን ከፍታንና እድገትን ያሳያል፡፡ ይህም ማለት አንድ ቃል በሁለት የትርጉም መስክ ሊገባ ይችላል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ቃል በሁለት የትርጉም መስክ ሊገባ መቻሉንና ክስተቱም ስመ ብዙ / Poly Semi/ የሚባል መሆኑ /እንደነካርተር፣ 1988:29/ የተመሣሰሉን ጉዳይ በየትኛውም ሁኔታ ብንመለከት ችግሩ የሚፈታው በአውድ ብቻ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ለማጠቃለልም፣ ተመሳሳይ ቃላት አጠቃላይ ትርጉምን የሚጋሩና በተወሰነ አውድም ተተካኪነት ያላቸው ሆነው በጥልቀት ሲመረመሩ ግን የፅንሰ-ሃሳብ ልዩነት የሚታይባቸው የቃላት ቡድን በመሆናቸው የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ከማሳወቅ ባሻገር ተዋረዳዊ የቃላት ግንኙነት እያስለዩ አውዳዊ የትርጉም ጥቆማዎችን በፍንጭ ሰጭነት ስለሚያጠናክሩ ቃላትን

መማርን በአሰሳ፣ በተሳትፎ፣ በጥናትና በትግበራ የመማር እገዛቸው መሠረታዊነት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.1.1.2 ተቃራኒዎች /Antonyms/

ስሙ እንደሚያመለክተው የቃላቱ ግንኙነት የተመሠረተው በተቃርኖ ላይ ነው፡፡ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በተቃራኒያቸው አማካኝነት በመተርጎም እንዲማሩ ማድረግ እንግዳ ባይሆንም መታወቅ ያለበት ጉዳይ የተለያዩ ብዙ አይነት ተቃራኒዎች በቃላት መሐል መኖራቸው ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ አራቱ፣

ሀ. ተሰፋሪ ተቃራኒዎች

ለ. የማይሰፈሩ ተቃራኒዎች

ሐ. ተለዋጭ ተቃራኒዎች

መ. አቅጣጫዊ ተቃራኒዎች የሚባሉት ይገኙባቸዋል /ካርተርና ማካርቲ፣ 1988፡25/፡፡

እዚህ ላይ ሌላው ማወቅ ያለብን ነገር ተቃራኒዎች ምንጊዜም መሠረት የሚያደርጉት አውድን /Context/ መሆኑን ነው

### 2.1.1.3. ተካትቶዎች /Hyponyms/

ተካትቶ በቃላት መሀል ያለውን በትርጉም የመካተት ግንኙነት የሚያመለክት ነው፡፡ ማለትም የተለያዩ ቃላት ትርጉም በአንድ ቃል ስር የማሰባሰብ ግንኙነት ሲኖር ግንኙነቱን ተካትቶ /Hyponyms/ ማለት ይቻላል፡፡ አዳዲስ ቃላትን በስነ-ትርጉም ተመሳሳይነታቸው መቦደን ቃላትን መማርን የመማር አንዱ ስልት ነው፡፡ ቃላትን በዚህ ዓይነት ግንኙነታቸው በማደራጀት የሚካተቱ ውሱን ቃላትን ማሰባሰብ ግልፅ የሆነ ስዕላዊ የትርጉም ውክልናን ያቀርባል /ካርተርና ማካርቲ፣ 1988፡25 ፣ ማካርቲ፣ 1990፡20/፡፡ ይህንን በማስመልከት ሲያብራሩም ሁለት የተካትቶ አይነቶች ተዘውትረው እጥቅም ላይ ይውላሉ ይሉናል እነርሱም፡-

ሀ. የበታቾች በበላዩ ስር የተካተቱበት /Super Ordinate/

ለ. የተወሰኑና ያልተወሰኑ ተካትቶዎች /Marked and Unmarked hyponyms/ የሚባሉት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የትርጉም ዝምድና አዳዲስ ቃላት ለክፍል ውስጥ ትምህርትነት ያገለግሉ ዘንድ በማደራጀትና በማቅረብ ትውስታን እያጠነከሩ ራስን የማስቻል ሚናን የሚጫወቱ ስነ ልቦናዊ መሠረት ያላቸው ተዋረዳዊ የትርጉም ግንኙነቶች ናቸው፡፡ እንደ ጌርንስና ሬድማን /1986፡31/ የትርጉም ዝምድና ለቃላት ትምህርት ግጥምጥምነት፣ ለጠቃሚ ማዕቀፍ /Frame - Work/ የተወሰነ መስመር የመከተል አካሔድና ለተማሪዎቹም በቃላት መሐል ያሉ የድንበር ልዩነቶችን ለመረዳትና በአዳዲስ ቃላት ላይ ምርመራ ለማድረግ በመርዳት ይጠቅማሉ፡፡

### 2.1.2. አብሮነቶች

ከቃላት አጠቃቀም አንፃር የአብሮነቶችን ምንንነት ካርተርና ማካርቲ /1988፡82/ ሲገልፁ

> ቃላት እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት ቀጥታ ብቻ ሳይሆን ጐናዊም ነው፡፡ ቀጥታው የቃላት ግንኙነት ተዋረዳዊ ዝምድና /Paradigmatic - Relations/ ይባላል፡፡ እነዚህም በተቃራኒ፣ በተመሳሳይና በተካትቶ ግንኙነታቸው የሚታወቁ ቃላት በመሆናቸው በቃላት መሀል ያለን ቀጥታ የትርጉም ግንኙነት ሲያመለክቱ ጎናዊው ግን የቃላትን በአንድ ላይ አብሮ የመግባት ተዘውታሪነትን ያመለክታል በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

የብሪታንያ የስነ-ልሣን ቡድን ቃላትን በቅደም ተከተላዊ ዝምድና /Syntagmatic Relation/ ማየት ያስፈልጋል በሚል ሃሣብ ከግራ ወደ ቀኝ ፅሁፋዊ አቀማመጥን በመመልከት እንደ ቃላት አብሮነት ያለ አተያይ በስራ ላይ ማዋል ጀመረ፡፡ ይሕም ቀጥተኛ የሆነ የፅንሰ ሀሳብን ግንኙነት ከቃሉ ትርጉም አኳያ የሚያሳይና ከሌላው ቃል ጋር ባለው የአገባብ ዝምድና ላይ ብቻ የተመሰረተ ነበር፡፡

አብሮነቶች ከአንድ በላይ በሆኑ ቃላት ግንኙነት ላይ በመመስረታቸው ፈሊጦችን ይመስላሉ፡፡ ሆኖም

ሀ. በፈሊጦች ተለዋዋጭ ያልሆነ የቃላት ግጥሚያ ስለሚታይና በአብሮነት ግን ተለዋዋጭነት እንደሁኔታው ስለሚኖር፣

ለ. የፈሊጦች ትርጉም በቃላቱ ተናጠላዊ ትርጉም ላይ የማይመሰረት ሲሆን በአብሮነት ግን ለያንዳንዱ ቃል የሚሰጠው ትርጉም ጉልቶ ስለሚታይ ይለያያሉ /ዋላስ፣ 1982፡119/፡፡

ካርተርና ማካርቲ /1988፡73/ ስለዚሁ ሲያስረዱ፣ "ከአንድ ቃል ጋር አብሮ የሚገባው መታወቅ ስለቃሉ የሚሰጠው መረጃ የትርጉም ገለፃን ያህል አስፈላጊ ነው፡፡" ይሉናል፡፡ በመቀጠልም ቋንቋን በመማር ረገድ አብሮነት ሁለት ጠቀሜታዎች አሉት ይሉና፣ ዝርዝራቸውንም

"ሀ. ቃሉን በመተርጐም ከፍተኛ ድርሻ ስላለው፣

ለ. ምን አይነት ቃላት ቀጥለው መምጣት እንዳለባቸው አንባቢዎችን /አድማጮችን/ አስቀድመው እንዲያውቁ ለማድረግ በአብሮነት አንድ ሰው መጪውን ሀሳብ ሊተነብይ መቻሉ ናቸው፡፡" በማለት ያቀርባሉ፡፡

ከዚሁ ጋር እንካርተር /1988፡ 37-38/ ሲገልፁ "ተማሪዎች የቀደመውን በማየት የሚቀጥለው ወይም መጪው ሀሳብ ምን እንደሆነ ለመገመት ስለሚችሉ በአብሮነት የንባብ ችሎታቸውን ማጐልበታቸው የማያጠራጥር ነው" በማለት በተጨማምሪ ከእውቀት ዘርፎች አቀናጅነት ሚና አንፃርም የአብሮነት ጥናት በቋንቋ ለውጥ ገለፃና በስነ-ፅሁፍ የስታይል (የአፃፃፍ ስልት) ትንተና ውስጥ በጥቅም ላይ የመዋል ሚናቸውን ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ አንድን ቃል ቀድሞትም ሆነ ተከትሎት ከሚገባው ቃል ጋር በአገባብ ማጥናቱ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አባባል የአብሮነት ተገቢነት ዕውቀት የቃላት ዕውቀትን በማሳደግ ሒደት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው /ጌርንስና ሬድማን፣ 1986፡39፣ ታይለር፣ 1990፡2/፡፡

### 2.1.3. መዋቅራዊ ፍንጮች ከቃላት ምስረታ አንፃር

ዋላስ /1982፡86/፣ ነታል /1982፡67/፣ ማካርቲ /1990፡5/ ስለመዋቅራዊ ፍንጮች ሲያወሱ፣ የመዋቅራዊ ፍንጭ ዕውቀት የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማስፋትና ያልታወቀ ቃልን ትርጉም ለመጠቆም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ይሉናል፡፡ ጌርንስና ሬድማን /1986፡48/ም ሲገልፁት በተለይ ተማሪዎች ለመልዕክት መቀበያም ሆነ ማስተላለፊያ የሚያገለግሉ አዳዲስ ቃላትን መስርቶ ለመጠቀምና ትርጉማቸውን ለመረዳት ያላቸውን ጠቃሚታ ከፍተኛነት ያሰምሩበታል፡፡ የተማሪዎቹ የመልዕክት መቀበያ ቃላት ምስረታ ቁልፍ እውቀት መኖር በምስረታ በተፈጠሩ አዳዲስ የምንባቡ ቃላት እንዳይቸገሩ ስለሚያደርጋቸው ፍቻቸውን በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ፡፡ መልዕክት ማስተላለፊያዎቹንም በሚመለከት የቃላት ምስረታ መሠረታዊ ዕውቀት መኖር ተማሪዎችን የቃላት ዕውቀት ለማስፋትና ሀሣባቸውን በተሳካ ሁኔታ ለመግለፅ እንዲሁ ያስችላቸዋል፡፡

ስለሆነም እንደ ምሁራኑ አባባል ፍችን ለመግለጽም ሆነ ለመረዳት የንግግር ክፍልን ለመለወጥ በቃል ስር ላይ የሚጨመሩ በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውሉ ቅድመ-ግንድና ድህረ-ግንድ ቅጥያዎች በተማሪዎች ትኩረት ይሰጣቸው ዘንድ የሚጠኑበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

ተማሪዎች በአንድ ቋንቋ ውስጥ ቅጥያዎች እንዴት ቃልን እንደሚመሰርቱ የሚያሳይ ተግባርን እንዲያከናውኑ ማድረግ አዲስ ቃልን ለመረዳት የሚያስችል ጠቃሚ የቃላት ክሒል እውቀትን ማስጨበጥ ነው፡፡ ማካርቲ /1990 -5/ በዚህ ላይ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ ቅጥያዎችን በቃላት ምስረታ ተማሪዎች ሙከራ እንዲያደርጉባቸውና በስልትም እንዲጠቀሙባቸው ሲደረግ ምስረታ ቃላት እንደውሀ የሚቀዱበት የማይደርቅ ምንጭ ይሆናል ይሉናል፡፡

ዋላስ /1982፡86-87/ም ይህንኑ የቅጠላ ዘዴ ቃላትን ለማሳወቅ እጅግ ውጤታማና የቃላትን ፍቺ ከአውድ ለመረዳት ጠቃሚ መንገድ ነው ሲሉ የቅጠላ አይነቶችንም በፈጠራ መልክ ለማስተማር በሚያመችበት መንገድ ማደራጀትና መመደብ /መምረጥ/ ያስፈልጋል በማለት ይገልፃሉ፡፡ በዚህም መሰረት በቃላት ስርና ቅጥያዎች ላይ የተመሰረተ መልመጃም የቃላትን ፍቺ በአጠቃቀም ግልፅ ለማድረግ ይረዳል ይላሉ፡፡

ይህም ማለት ቃላትን በምን ማለትነት አተያይ ወይንም ከትርጉም አኳያ ስንመለከታቸው ፍቻቸውን ግልፅ አድርገው ሊያስረዱን የሚችሉ ሶስት ክፍሎች በእያንዳንዱ ቃል እናገኛለን፡፡ ክፍሎቹን በዝርዝር በመመልከት የእያንዳንዱን የቃል ክፍል ፍቺ መረዳት አጠቃላዩን ፍቺ ለመረዳት ያስችላል፡፡

በእንግሊዝኛው ከግሪክና ከላቲን የተወሰዱ በተማሪዎች ላይ ችግር እየፈጠሩ ያሉ የግብር /ረቂቅ/ መጠሪያዎች አሉ፡፡ እነዚህን ለመፍታት ተዘውትረው የሚታወቁትንና ፍቻቸው በውል የታወቀውን የግሪክና የላቲን ቅድመና ድህረ-ግንድ ቅጥያዎችንና ግንዶችን በመለየት መግጠምና መፈታታት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ በአማርኛም ከውጭ የምንዋሳቸውንና የተዋስናቸውን፣ በሀገራችንም ከግዕዝ የተወሰዱትን፣ ከሌላ ቋንቋዎችም ካሉ በማሰባሰብ የቃላት ዘሮችንና ቅጥያዎችን የመማር አስፈላጊነት ለዚህ ሁኔታ ተገቢ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የምስረታ እውቀት ረጃጅም ቃላትን ያለችግር እየፈታቱ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን እንዲሁም ስሮችን ለያይቶ ፍቻቸው ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል፡፡ በአውድ ውስጥም ትርጉማቸውን በጥሩ ሁኔታ ለመገመት ይረዳል፡፡ በመሆኑም የቅጥያዎችና የስሮች እውቀት ቃላትን ለማስፋፋት የአቋራጮች አቋራጭ መንገድ ነው/እስሚዝ፣ 1952፡87/፡፡

ዋላስ /1982፡85/ ይህንኑ ሲያረጋግጡ አስራ አራት የግሪክና የላቲን ስሮችን ማወቅ 14000 የእንግሊዝኛ ቃላትን ለማወቅ ያስችላል ይሉናል፡፡ በተጨማሪም ድህረ-ግንድ ቅጥያዎች ተግባራዊ ትርጉሞች አሏቸው በማለት እኚሁ ተመራማሪ ሲያስገነዝቡ ምንም ይሁን ምን የቃላት ትምህርት ውጤታማ የሚሆነው ተማሪዎች በገዛ ራሳቸው ሊማሩ የሚችሉባቸውን የተለያዩ የቃላት መማሪያ ስልቶች ማቅረብና እንዲማሩ ማድረግ ሲቻል መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆነም ትኩረታችን እንዴትና ምን እንደሚማሩ ራሳቸው ተማሪዎቹ እንዲመርጡና እንዲወስኑ ማስቻሉ ላይ መሆን ይገባዋል፡፡

## 2.1.4. አውዳዊ የቃላት ማስተማሪያ ቴክኒኮች ከሁለንተናዊ የቃላት ገጽታ አንፃር

ቃላትን በአውድ የመማር አስፈላጊነት ባብዛኞቹ የቋንቋ ምሁራን የሚደገፍ ሲሆን ጠቀሜታውም የቃላትን ልዩ ልዩ ገፅታና ህይወት ያለው ፍቺ በተግባር ለማሳየት ነው፡፡ የአንድን ቃል ልዩ ልዩ አገባብ ቀርቶ መሠረታዊ /እማሬያዊ/ ፍቺ በማወቅ ደረጃ እንኳን የቋንቋውን ቃላት በሙሉ የሚያውቅ አፍ ፈቺ ማግኘት እንደሚያስቸግር ላዶ/1964፣117-119/ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም አፍ ፈቺዎች /Native Speakers/ በጋራ የሚያውቋቸው ተግባራዊ ቃላት /functional words/ በሙሉና ህብረተሠቡ በከፍተኛ ደረጃ አዘውትሮ ከሚግባባባቸው የይዘት ቃላት በተጨማሪ በቃላት እውቀት መጠን ሊለያዩ የሚችሉት በትምህርትና በንባብ ጥረት ልዩነት ምክንያት ነው፡፡

ማኪ /1965፡69/ እንደሚያስረዱት ደግሞ ቃላት ከሌሎች የቋንቋ አባሎች ይበልጥ ተለዋዋጭነት ያላቸው ሲሆን ከለውጦቹ ምክንያቶች ዋናዋናዎቹ በተለያዩ ህዝቦች መሐል የሚደረጉ ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሌሎች ግንኙነቶች የምርት እድገት፣ ጥናታዊ ግኝቶች፣ ወዘተ... ሁኔታዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በመዋስ፣ በነባሮቹ ላይ ተጨማሪ ፅንሰ ሃሳብ በመደረብ፣ በማጣመር፣ ወዘተ ቃላት ያለማቋረጥ ስለሚለዋወጡና ስለሚበዙ የአንድን ቋንቋ ቃላት በሙሉ የሚያውቅ አንድም አፍ ፈቺ ባለቋንቋ ቀርቶ መዝገበ-ቃላት እንኳ ባለመገኘቱ የቃላትን ልዩ ልዩ ትርጉሞች በግልፅ ለማስተማር አውዳዊ ስልቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

### 2.1.4.1 እውናዊ አውድ /Authentic Reading Text/

ምዘንስኪ /1983፡25/ ቃላትን በመማር ማስተማርና አንብቦ በመረዳት መሀል ጠንካራ ግንኙነት እንዳለ አስምረውበታል፡፡ ስለዚህም ሲያብራሩ የአንድ ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በቃላት ችሎታ ማነስ ምክንያት ስለሚዳከም ተማሪዎች አንብቦ ለመረዳት የሚያስችል

በቃላዊ አቀራረብ /Lexical Approach/ ላይ የተመሠረተና የተጠናከረ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል ይሉናል፡፡

ስልቱን በሚያስጨብጥ መልኩ ምዘንስኪ /1983/ የምንባብን ለቃላት መማሪያ አውድነት በተለያየ ደረጃ የገለፁ የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት አውድ፡-

ሀ. ቃላትን ለማስታወስ

ለ. የንባብ ፍጥነትን ለመጨመርና

ሐ. የተሻለ አንብቦ ለመረዳት ያግዛል ይሉናል፡፡

እስሚዝ /1952፡134/ እንደሚያስገነዝቡት በቋንቋ ጥናት ላይ ስሜት ያለው ማንኛውም ሰው በተግባራዊ አውድ ቃላትን የማወቅና የመጠቀም ችሎታ ሊኖረው ይገባል ይላሉ፡፡ በተጨማሪም ሲያስረዱ ቃላትን የአንባቢዎችን እለታዊ ፍላጐት በሚያሟላ መልክ በተዘጋጁ ምንባቦች ማስተማር ተማሪዎች ቃላቱን እንዳይረሷቸው ስለሚያግዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

የአንድን ቃል የተለያዩ ገፅታዎች ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱና ዋንኛው የቃላት አብሮነት ነው፡፡ የዚህንም ዕውቀት አስፈላጊነት ማርቲን /1984፡133/ ሲያስረዱ በተለይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አስመልክቶ አንድ ሰው የቃሉን አብሮነት ልክ እስካላወቀ ድረስ ቃሉን ያውቀዋል ማለት አይቻልም በማለት ይጠቁማሉ፡፡

ላዶ /1964/ ቃላትን በአውድ ስለማስተማር ከፍተኛ አፅንኦት ሰጥተው ሲያስገነዝቡ የቃላት ዕውቀት ብዙ ሰዎች ከሚገመቱት በላይ መሆኑን በማስረዳት የቃላት ጥናት የተመሣሣይ ወይም የተቃራኒ ጥናት ብቻ ሳይሆን ቃላቱ የተገኙበት አውድ ጥናትም ነው ይሉናል፡፡ ይህም ማለት የቃላት እውቀት ብዙ ገፅታዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህም መሀል የተወሰኑት ገጽታዎች በአውድ ጉልተው ሲወጡ አውድ ያላመቻቸው ድብቅ እንደሆኑ ይቆያሉ፡፡ ስለዚህ ቃላትን ህይወት ባለው መልክ መረዳት ማለት የቃላቱን አጥኚ ከዚህ ቀደም ባልተጠቀመበት መልክ ወይም ፍቺ ሁኔታ ቃላቱን መጠቀም መቻል ማለት ነው /ላዶ፣ 1964:18/፡፡

የዚህ አይነቱ ቃላትን በአውድ የማስተማር ስልት በዋላስም የተነሳ ሲሆን ይህም ቃላትን እጅግ በአማረ ሁኔታ የማስተማር ስልት የሚገኘው በአውድ ውስጥ በተለይም ለማስተማር ተብለው ባልተፃፉ አውዶች /Authentic reading texts/ ውስጥ አስገብቶ በማስተማር መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች ለአፍ-ፈቺ በተዘጋጀ ፅሁፍ የቃላትን ፍቺ እንዴት እንደሚያገኙ ለመረዳት የሚያስችሉ የተለያዩ መንገዶችን መማር ይኖርባቸዋል፡፡

ብራይትና ማክግሪገርም /1978-30/ እንዲሁ ተማሪዎች መዝገበ-ቃላትን ሳይመለከቱና ሌላም ሰው ሳይጠይቁ አዳዲስ ቃላትን በአገባብ ያውቁ ዘንድ የቃላትን ፍቺ የማግኘት ስልት አስፈላጊነትንና አጠቃቀሙን በግልፅ ሊማሩትና እንዲያምኑበትም ሊደረግ ይገባል ይሉናል፡፡

ይህንን ለማድረግ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አዘጋጆችና መምህራኑ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወስ እንደሚገባቸው ይጠቁማሉ፡፡

ነጥቦቹም፡-

ሀ. ከምንባቡ ትርጉማቸው በቀላሉ የሚታወቅና ተማሪዎች ግን የማያውቋቸውን፣

ለ. የትርጉም ዝምድና ያላቸውንና በአንድ ላይ ሊያወያዩ የሚችሉትን፣

ሐ. በተዛምዶ ለማስተማር የሚቀሉትን፣

መ. ሥነ ፅሁፋዊ ቃና በጋራ ያላቸውን፣

ሠ. ውስጣዊ መዋቅራቸውን በመተንተን ማሳየት የሚችሉትን ቃላት መምረጥ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት አዳዲስ ቃላትን ለማስተዋወቅ ሁል ጊዜ ምንባቦችን መጠቀሙ የሚያስከትለው ችግርም እንዳለ የተደረሰበት ሲሆን ይኸውም፡-

ሀ. የቃላት ችሎታን ከማሳደግ አኳያ ከምንባቦች ጠቃሚ ቃላትን በመልመጃ ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ሁኔታን ማግኘት አለመቻል፣

ለ. የምንባብ ቃላት መልመጃዎች ብዙውን ጊዜ የሚፈትኑት መቀበያ ቃላትን /Receptive Words/ እንጅ ማስተላለፊያ ቃላትን /Productive words/ አለመሆኑ፣

ሐ. ማስተላለፊያ ቃላትን የማሳወቅ አጋጣሚ በምንባቦች አማካኝነት ቢኖር እንኳ አልፎ አልፎ መሆኑ ናቸው /ጌርንስና ሬድማን፣ 1986፡ 155/፡፡

አንዳንድ ምሁራን ለምሳሌም እነ ሞርጋን /1986/ እንደሚጠቁሙት ብዙ ጊዜ ጥሩ የሚባሉት ምንባቦች በጣም ረዥም በመሆናቸው የቃላት ብዛታቸው በአንድ ጊዜ መማር ከሚቻለው በላይ በመሆን ያስቸግራሉ፡፡ በሌላ አባባል ምንባቦች ሥርአታዊ የቃላት ምርጫን፣ ደረጃን፣ ቅንብርን ወዘተ ስለሚያጡና ከመጠን በላይም ብያኔን በማስተማርና

በመፈተኛ መሳሪያነት በተለይ የቃልን ትርጉም ከመፍታት አኳያ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ስለሚደረግ ችግሩ ቀላል የሚባል እንዳልሆነ ገልፀዋል::

እንደነዚሁ ምሁራን አስተያዬት ምንባቦች የአዳዲስ ቃላትን ሁለንተናዊ ገፅታዎች የመቀበያ ቃላት ዕውቀትን ወደ ማስተላለፊያ ቃላት ዕውቀትነት እያሸጋገሩና በተጨማሪም ምንባቦቹ አስደሳች ከሆኑ በተማሪዎች ዘንድ የቃሉን አይረሴነት በማጠናከር ቃላትን መማርን የመማር ሒደት ለማጉልበት ይረዳሉ:: ይህም ከላይ የተጠቀሱት ትችቶች የምንባብን ቃላት ማስተማሪያነት ዋጋ የሚያሰጡ ሳይሆኑ አዳዲስ ትወራዎችንና አስተሳሰቦችን መሠረት በማድረግ ድክመቶቻቸውን ለማስወገድ የሚያስችል ጥረት እንድናደርግ የሚያሳስቡ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው::

## 2.1.4.2. አውዳዊ ነሲብ ሥራ /Contexual guess work/

አውዳዊ ነሲብ ስራ ተማሪዎች ትርጉማቸው ተለይቶ ያልታወቀ ቃላትን ትርጉም ከአውድ ውስጥ እንዲገምቱ የሚደፋፈሩበት የቃላት ማስተማሪያ ቴክኒክ ነው:: ካርተርና ማካርቲ /1988/ ይህንኑ ሲያስረዱ በተለይ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ሊጠቀሙበት የሚችሉ ሲሆን ይህም ቃላትን ሁሉ ማስተማር ካለመቻሉ አንፃር ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ማወቅ የሚችሉበት ስልት ነው በማለት ይገልፃሉ:: ከዚህም አዳዲስ ቃላትን በተናጠል ከማስተማርና መዝገበ - ቃላትን አዘውትሮ ከመጠቀም ይልቅ አውዳዊ ነሲብን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ መረዳት ይቻላል:: በተጨማሪም አውዳዊ ነሲብ በተግባር መዋሉ የቃላት ትምህርትን ክሒላዊ ወደመሆን እንዲሸጋገር አድርጉታል:: የአውዳዊ ነሲብ ስልጠናን አስፈላጊነት አጠናክረው የሚገልፁት ምሁራን እንደሚሉት በአንብቦ መረዳት ጠንከር ያለ እውቀት ለማስጨበጥ፣ በዋናነትም የአንብቦ መረዳት ፍጥነትን ለመጨመር፣ በሒደቱም ለመዝናናትና፣ ችግር ፈቺ አሰራርን ለማለማመድ ስለሚጠቅም አስፈላጊ ነው ይላሉ /ኑታል፣ 1982፡70/::

ጌርንስና ሬድማን /1986፡84/ ከአውድ የመገመት ችሎታ በማያጠራጥር ሁኔታ ዋጋ ያለው ክሒል ነው ይሉና የተለያዩ ስልቶችን በአውዳዊ ነሲብ ስልጠና ሒደቱ ውስጥ እንዲካተቱ ያሳስባሉ:: ከስልቶቹ አንዱ ፍቺ አልባ የሆኑ /Non - Sense/ ቃላትን በያዙ ዐ.ነገሮች መጀመርና በፍቺ አልባ ቃላቱ ፈንታ የሚሞሉትን ቃላት ተማሪዎች እንዲተኩ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ይህም የቀደመ የቃላት ችሎታን መሠረት የሚያደርግ ሊሆን ይችላል:: እነዚሁ ምሁራን አንድን ትርጉም አልባ ቃል በተገቢው ቃል መተካት ትርጉምን ከአውድ የመገመት ችሎታን ለማዳበር የሚረዳ፣ በአብዛኛው የትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሚሰራበት ስልት ነው ይላሉ:: እንደኑታል /1982፡73/ አባባል እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባው አንድ

ዋና ነጥብ ተማሪዎች በሚገምቱበት ጊዜ ሊሆን የሚችለውን እንጂ ትክክለኛ ግምት ላይገምቱ የሚችሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ካርተርና ማካርቲ /1988፡63/ በሰጡት አስተያየት ጠቋሚ ፍንጮችን ለማግኘት ከፅሁፉ ርዕስ፣ ከሌሎች የንግግሩ ወይም የፅሑፉ ቃላት፣ ከሰዋሰዋዊ መዋቅሩ፣ ንግግር ከሆነ ከድምፀቱ፣ ፅሁፍ ከሆነም ከሥርዐተ-ነጥቡ መገመት የሚችሉበትን ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው ይሉናል፡፡ በተጨማሪም እነዚሁ ምሁራን ከአውድ አስቀድሞ ለመገመት ያስችላሉ ያሉዋቸውን ሲጠቅሱ የተማሪዎች በቂ የቃላት ዕውቀት፣ የንባብ ችሎታ፣ የሰዋሰው ዕውቀትና ዳራዊ የውሁድ አሀዶች /texts/ ዕውቀት ናቸው ይሉና ዘርዘር በማድረግም አምስት ደረጃዎችን ያልታወቁ ቃላትን መገመቻ ሂደቶች ሊሆኑ ይችላሉ በማለት እንደሚከተለው ያቀርባሉ፡፡ ሂደቶቹም፡-

ሀ. ያልታወቀውን ቃል የንግግር ክፍል ማወቅ፣

ለ. ያልታወቀውን ቃል የቅርብ አውድ የምንባቡን አገባብ (የአረፍተ ነገሩን) በጥልቀት መመርመርና አስፈላጊም ከሆነ ቀለል ባለ አባባል ለመተርጎም መሞከር፣

ሐ. ሰፋ ባለ አውዳዊ አገባቡ ያልታወቀውን ቃል ትርጉም መመርመር፣ ማለትም ቃሉ የሚገኝበት ሐረግና ዐ.ነገር አንፃር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ጉረቤት የምንባቡ ዐ.ነገሮች ጋር አያይዞ መመርመር፣

መ. ያልታወቀውን ቃል ትርጉም መገመት፣

ሠ. ግምቱ ትክክል መሆኑን ፈትሾ ማረጋገጥ ናቸው፡፡

በዚህ ሒደት ዋላስ /1982/ና እነካርተር /1988/ ትርጉም የሚጠቁሙ ናቸው ያሏቸውን ሲዘረዝሩ

1. የቃላት ተመሳሳይነት
2. የቃላት ተቃራኒነት
3. የምክንያትና የውጤት ግንኙነት
4. በአንድ ነገርና በነገሩ ጠቀሜታ መሀል ያለ ዝምድና
5. ገለፃ
6. ማስረጃ
7. ምዕላድ
8. የቃላት ብያኔያዊ ጥቆማ
9. የአጠቃላይ /ርዕሰ-ቃላት/ና የውሱን ቃላት ግንኙነት
10. ርዕሰ-ቃላት + ምሳሌ
11. በአውዱ ውስጥ የሚገለፁ ነገሮች፣ ሁኔታዎች፣ ድርጊቶችና ወዘተ ጠባይ

12. አጠቃላይ እውቀትና ወዘተ… ናቸው በማለት የአውድን ሁለንተናዊ የቃላት ገፅታ መግለጫነት በምሳሌ ያስገነዝባሉ፡፡

በመሆኑም ቃላትን ተግባራዊና ማህበራዊ ገጽታቸውን አጥፍቶ ህያውነትን ባጡበት መልክ ከአውድ ውጭ በመደርደር መጀመሪያ በተናጠል አጥንቶ ቀጥሎ ወደ አውዳዊነት ለመለወጥ በመታገል ዙሪያ ጥምጥምና አድካሚ የሆነ ቃላትን የመማሪያ ስልት ተግባራዊ በማድረግ ከማስተማር ይልቅ ለትምህርት የቀረቡትን ቃላት ሁለንተናዊ ማንነት በሚያሳዩ አውዶች ማስተማር ጠቃሚ በመሆኑ የሚከተሉትን ነጥቦች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ማካተት አስፈላጊ መሆኑን ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡
ነጥቦቹም፡-

1. ከቃላት ምስረታ /Word Formation/ አንፃር አፈጣጠራቸውን በሆሄያትና ድምጾች /Spelling and Sounds/፣ በቅጠላ /affixation/ና በጥመራ /compounding/ዝርዝር የቃላት ማስተማሪያ ስልትነት፣
2. ከፍቺ /meaning/ አንፃር ከመሰሎቻቸው ጋር ባላቸው ዝምድና /sense relations/አዛማጅ ፍቺ /association/፣ ስነ ትርጉማዊ ዋጋ፣ ነጠላና ድርብርብ የትርጉም ውክልና በአውዳዊ ፍች /contextual meaning/፣ በተገናኙና ባልተገናኙ ፍቺዎች /related and unrelated meanings/፣ ተመሳሳዮች /synonyms/ና ተቃራኒዎች /antonyms/፣ ተካትቶዎች /hyponyms/ የቃላት ማስተማሪያ ስልትነት
3. ከቃላት አጠቃቀም/word use/አንፃር ማን? መቼ? የት? ለምን ጉዳይ? በምን በምን የቃላት ግጥሚያዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ዋላስ /1982፡119/ና እነ ካርተር /1988፡19/ ከቃላት ምንነት ብያኔ የተሰጡትን መግለጫዎች መሰረት በማድረግ ተለዋጮችን /metaphor/፣ ፈሊጦችን /idioms/፡ ተረትና ምሣሌዎችን /proverbs/፣ አባባሎችን /expressions/፣ የቃላት አብሮነቶችን /collocations/፣ ምስያዎች /analogies/፣ መደበኛ ቃላትን /Formal words/፣ ኢመደበኛ ቃላትን /informal words/ እና ሞያ ነክ ቃላትን /technical words/ በቃላት ማስተማሪያ ስልትነት በመጠቀምና
4. በሰዋሰዋዊ ገጽታዎችም አገባባዊ ቦታቸውን በንግግር ክፍሎች ምድባቸው ስሞችን፣ ግሶችን፣ቅጽሎችን፣ተውሳከ-ግሶችን፣ መሥተዋድዶችንና ከቅጥያዎች ጋር ባላቸው ጥምረትም የቁጥር፣ የጾታ፣ የመደብና የጊዜ አመልካቾችን በቃላት ማስተማሪያ ስልትነት በመጠቀም በተዋረዳዊና ጉናዊ የቃላት ግንኙነቶች /paradigmatic and synitagmatic relations/ እያሰሱ፣ እየተሳተፉ እያጠኑና እየተገበሩ መማር ጠቃሚ ቃላትን መማርን የመማር ልምድ መሆኑ ናቸው፡፡ በተጨማሪም፡-

ሀ. በመዝገበ-ቃላት እጅግ አዘውትሮ ከመጠቀም አሰልችነትና በራስ መተማመንን ማሳጣት፣

ለ. ከአማርኛ ቋንቋ የመዝገበ-ቃላት ዘመናዊነት ችግርና የጥንቱም ቢሆን በየትምህርት ቤቱ ሊገኝ ካለመቻል፣

ሐ. በይሉኝታም ሆነ በስነ ስርአታዊ ምክንያቶች ነውርነት የተነሳ በየንግግሩ ተናጋሪን እያስቆሙ "ይኼ ቃል ምን ማለት ነው?" ብሎ በመጠየቅ ትርጉምን ለመረዳት ካለመቻልና የመልእክት ሽግግር ችግር ከመፈጠሩ አንፃር ችግር ፈች ከመሆን፣

መ. ተማሪዎችን እራሳቸውን በማስቻል የቃላት ትምህርትን ወደ ክሒልነት ደረጃ ከማሸጋገርና የእድሜ ልክ የቃላት ኢመደበኛ ትምህርትን ብቃትና ፍጥነት አራቱን የቋንቋ ክሂሎችና ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች በቅንጅት እንዲያዳብሩ ከማድረግና፣

ሠ. በጥቅሉም በሰው ልጅ የስልጣኔ እድገት ቋንቋ ሊጫወተው የሚችለውንና የሚገባውን ተግባራዊ፣ ስነ ልቦናዊና ማሕበራዊ ሚና ከማጎልበት አንፃር ጠቀሜታው የጐላ በመሆኑ በአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተሰራበት ያለውን የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሀፍ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለውን ብቃት በመገምገም ወደ ተገቢው የጥናት ውጤት፣ ድምዳሜና መፍትሄ ሀሳብ እንደሚያደርስ በማመን አጥኚው መገምገሚያ መስፈርቶችን ለማውጣት ተጠቅሞበታል፡፡ ዝርዝሩንም በአባሪ "ረ" ይመልከቱ፡፡

## 2.2 ቃላትን መማርን በተሳትፎ፣ በጥናትና በትግበራ ክንውኖች የመማር ቴክኒክ

የተሳትፎ፣ የጥናትና የትግበራ ክንውኖች በተግባራዊ ሂደት የአሰሳ ዘዴ ጋር በቅንጂት የሚሠራባቸው፣ ከአፍ ፈቺዎች ኢ መደበኛ አማማር ልምዶች ተወስደው በሳይንሳዊ ዘዴ በመቀናበር ተመልሰው ማብቂያ የለሹን የእድሜ ልክ የቃላት ትምህርት እንዲያጐለብቱ በመደበኛው ትምህርት ተማሪዎችን ማእከል ባደረገ /student centered/ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረቱ፣ የቃላትን የክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን አቀናጂነት ተግባራዊ እውቀት በተማሪዎች ዘንድ በማስረፅ በቋንቋ ብቃት ችግር ፈችነታቸው በዘመናችን ተወዳጅነትን ያገኙ ክንውኖች እንደሆኑ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው ዋና ጉዳይ የክንውኖቹ ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረት የተማሪዎች ማእከላዊነትና ቃላዊ አቀራረብ /lexical approach/ መሆኑን ነው፡፡ ሁለቱም ትርጉምን ማዕከል ያደረገው የተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አመለካከት /communicative

approach/ አካል በመሆናቸው አንድነታቸው የጠበቀ ቢሆንም የክንውኖቹን ገጽታ ለማጉላት ይረዳ ዘንድ ከተማሪዎች ማዕከልነት በመጀመር ምንነታቸውን ከምሁራን ጥናታዊ ስራዎች በመጥቀስ እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

የተማሪዎች ማእከልነት ከጉዳይ ተኮር አቀራረብ /subject centered aproach/ በብዙ መልኩ የተለየ በመሆኑ ይዘትን ከማስተላለፍ ይበልጥ በችግር ፈቺነት ላይ የሚያተኩር የትምህርት ንድፈ-ሀሳብ አይነት ነው፡፡ እውቀት በተማሪና በአካባቢ መሀል በሚካሔድ ተራክቦ የሚገኝ ነው የሚል እምነት ስላለው / ናይት፣ 1981፡94/ ትኩረቱ እንደላይኛው በተደራጀ ትምህርት ሽምደዳ ላይ ሳይሆን በችግር ፈቺነት ላይ ነው፡፡ ተማሪዎች ችግር ከመፍታት አኳያ በቡድን / በግል/ በንቃት እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡ ከግላዊ ብቃት ይልቅ ህብረታዊ ብቃትን መሰረት ያደረገ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ስለሆነም ትምህርት አሰሳዊ እንጂ ገለፃዊ /የሰጪነትና የተቀባይነት/ ሂደት አይደለም፡፡ በሂደት መሻሻልን ለማምጣት የሚጣርበት ስለሆነም የማስተማር ዘዴው /የእንዴት እናስተምር ጥያቄ/ ከትምህርቱ /የምን እናስተምር ጥያቄ/ ይበልጥ የሚተኮርበት ጉዳይ ሆኖ ይታያል፡፡

በዚህም መሰረት ት/ቤት ከማኅበራዊው አካባቢ ጋር የሚጣጣም ልዩ አካባቢ ነው ተብሎ ይታመናል /ጉድ ላድ፣ 1960፡ 5-19/፡፡

ከትምህርት ተኮር በተቃራኒው መምህሩ ተማሪዎች በሚያደርጉት ችግር የመፍታት ሙከራቸው እንደመመሪያ ሰጪ/መሪ/ ሆኖ ነው የሚቆጠረው፡፡ እንደ ጉዳይ ተኮሩ ሁሉን አድራጊ ባለስልጣን ሳይሆን ተማሪዎች ዳታን እንዲተነትኑ፣ እንዲተረጉሙ፣ እንዲገመግሙ፣ አቅጣጫውን እንዲያውቁ እና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ይመራል /ፕራት፣ 1971፡229/፡፡ አላማው ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፍ ላይ ብቻ ተወስነው እንዳይቀሩ ነፃ ለማውጣት ነው፡፡

ወደ ቃላዊ አቀራረብ ስንመጣ ሀርመርና ሮዝነር /1991-i/ የተሳትፎን፣ የጥናትንና የትግበራን ክንውኖች ጠቀሜታ ሲዘረዝሩ፡-

1. ተማሪዎች ለቃላት ትኩረት እንዲሰጡ፣ ቃላትን ማወቅ ማለት ምን ማለት መሆኑን እንዲያውቁና በቃላትም ሀይል ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙ፡፡
2. ተማሪዎች ከተወሰነ አርእስት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቃላት በትኩረት ለመማር እንዲችሉ ፣
3. የተማሪዎችን ፍላጐት ለማነሳሳትና ተግባራዊ የቃላት አጠናንንም በቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ የማስፋፍያ ዘዴ በተፈጥሮአዊ አካሄድ ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን

አቀናጅተው ለማስተማር ያገለግላሉ በማለት ተግባራዊ ንድፋቸውን በሚከተለው አይነት ያስቀምጣሉ፡፡

| |
|---|
| **ተሳተፉ** (ENGAGE) |
| **አጥኑ** (STUDY) |
| **ተግብሩ** (ACTIVATE) |

ከዚህ እንደምንገነዘበው ክንውኖቹ በተማሪዎች ፍላጐት ላይ ባነጣጠሩ ምንባቦች፣ ጥያቄዎችና ተግባራት ጀምረው ተማሪዎች ተፈላጊውን መረጃ በተተኳሪ ቃላት ላይ እንዲሰበስቡ ካደረጉ በኋላ ወደ ጥናት ክንውኖች በመሸጋገር በከፊል ቁጥጥር ስር በአውዶች፣ በሰንጠረዦች፣ በውይይቶችና በትንተናዎች አማካኝነት ደጋግመው እንዲጠቀሙባቸው በማድረግ በድግግሞሽ ልምድ በመፍጠር ወደ ማስተላለፊያ ቃላትነት (Productive Words) እንዲሸጋገሩ በማድረግ ክንውን ይፈፀማል፡፡ ይህም ይጠናከር ዘንድ በሚቀጥለው የትግበራ ክንውን ተማሪዎች የተሳተፉባቸውንና ያጠኗቸውን ቃላት በራሳቸው ፍላጐት ያለቁጥጥር ታሪክ እንዲናገሩባቸውና እንዲጽፉባቸው፣ ማስታወቂያዎችን፣ ቃለምልልሶችን፣ ደብዳቤዎችን፣ ወዘተ እንዲጽፉባቸው በማድረግ የቃላትን የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች አቀናጂነት ተግባራዊ ሚና በተማሪዎች የባህሪ ለውጥ እንዲገለጹ ተደርጐ የትምህርቱ ማብቂያ ይሆናል፡፡

ዝርዝሩን በአባሪ “ረ” ይመልከቱ፡፡

## 2.3. የቃላት ትምህርት እድገት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የነበረውንና ያለውን የቃላት ትምህርት እድገት ስንመለከትም እንደ አውሮፓው የቋንቋ ትምህርት ሁሉ በጥንታዊው ትምህርት ከአውድ ውጭ የሆኑ ዝርዝር ቃላትን በመሸምደድ የመጀመር ሂደትን ከማካሄድ አሁን እስከተደረሰበት ሰዋሰዋዊ ህጐች መከሰቻነት ደረጃ ያደገበትን ሂደት ማስተዋል ይቻላል፡፡ በጥንታዊው የግዕዝ ትምህርት ተማሪው የግዕዝ ቋንቋን ስርዓት በሚገባ ለማወቅ ቃላቱን ማጥናት ስለነበረበት ነጠላውን ግስና ህብረ ቃላትን ደረጃ በደረጃ የፊደሎችን`ተራ በመጠበቅ ያጠናል!!

የግዕዙ አካሄድ እስከ አሁን በቅኔ ቤት የሚሰራበት ከመሆኑ በተጨማሪ በዘመናዊውም በኩል ማስተማሪያ መጽሀፍት ሳይኖሩ ለገበያ የተዘጋጁን ልዩ ልዩ መፅሃፍት በመጠቀም መማር፣ ከዚያም በኋላ የተዘጋጁት መጻህፍት ብቃት ችግር ያለበት መሆኑ በተለያዩ ምሁራን መገለፁና እስከ አሁን የተዘጋጁት የአማርኛ ሰዋሰው መጻህፍት በቅርፅ መዋቅር ላይ እንጂ በስነ-ትርጉም መዋቅር ላይ አለማተኮራቸው የአማርኛ ቃላት ትምህርት እድገት ወደኋላ መቅረቱን የሚያመለክት ነው፡፡ በህላዌ ገብረ-እግዚአብሄር /1960/፣ ተክለ ማርያም ፋንታዬ /1957/ እና መስፍን ልሳኑ /1949/ እንደምንመለከተው ፅሁፎቹ በተዘጋጁበት ዘመን ቃላትን ያለ አውድ ማስተማር ተዘውትሮ ይሰራበት እንደነበረ በተግባር ተጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም ትንሣኤ /1988:52/ አሁንም እንኳ ቢሆን በየፈተናዎቹ ከአውድ ውጪ የሆኑ በርካታ ቃላትን በጥያቄ መልክ አዘጋጅቶ ማቅረብ የሚያመለክተው የቃላትን ሙሉ ትርጉም ማግኘት የሚቻለው በተለያየ አውድ ውስጥ መሆኑን ባለመገንዘብ ላይ የተመሰረተ ችግር መኖሩን የሚያመለክት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዘመናዊ የቃላት አተያይ አኳያ በአማርኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ላይ የተደረገና በዚህ ጥናት አቅራቢ ሊገኝ የቻለው አንድ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም በ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የቃላት ጥያቄዎች ላይ የተደረገው የትንሳኤ /1988/ ጥናት ሲሆን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ላይ ግን አራት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች መደረጋቸውን የሚያመለክቱ ስራዎች ተገኝተዋል፡፡እነዚህም፡-

1. በ2ኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ መማሪያ መፃህፍት ቃላት ተዘውታሪነት ደረጃ ጥናት ላይ ያተኮረ በመኮንን ሁንዴ /1984/ና
2. በዘመናዊ ቃላት ማስተማሪያ ስልቶች ትግበራ በአ.አ.ዩኒቨርስቲ ጀማሪ መርሃ ግብር የእንግሊዝኛ መማሪያ መፅሐፍ ምርመራ ላይ ያተኮረ በደሴ ብርሐኔ /1988/፣
3. በዘመናዊ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶች ውጤታማነት በ4ኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ትምህርት አሠጣጥ ተግባራዊነት ጥናት ላይ ያተኮረ በተስፋዬ መሕዘንቱ /1990/፣
4. ፍላጐትን በማነሳሳት ቃላትን የማስተማር ስልት በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራን ዘንድ ተቀባይነት ይኖረውና አይኖረው እንደሆነ በመመርመር ላይ ያተኮረ የዝንባሌና የአመለካከት ጥናት በአለሙ ሐይሉ /1994/ ናቸው፡፡

ከዝርዝሩ እንደምንረዳው በአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት ላይ የተደረገው ጥናት አንድ ብቻ በመሆኑና የቃላት ትምህርትም ለቋንቋ ትምህርት መጠናከር መሠረታዊነት ከላይ በ2.1 እና 2.2 የክለሳ ድርሳናት ማብራሪያ እንደምንገነዘበው ከፍተኛ በመሆኑ ይህ ጥናት ቀጥሎ የሚቀርቡትን በምሁራን ጥናት የተገኙ የቋንቋ ብቃት ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚረዳ ይታመናል፡፡

ከዚህ አይነቱ የቃላት ትምህርት ዕድገት የተገኘውን ውጤት የገመገሙ ምሁራን እንደሚያስረዱት በድርሰት ተግባር ላይ የተሰማሩ ምሁራን ሳይቀሩ የሚከተሉትን አይነቶች የቃላት ስህተት በፅሁፎቻቸው አዘውትረው ይፈፅማሉ ይሉናል፡፡ እነዚህም ለመፃህፍት ዝግጅት እንደ ፍላጐት አሰሳ /Needs analysis/ ስለሚቆጠሩ ለአብነት የሚከተሉትን እንጠቅሳለን፡፡

ሀ. የቃላት አለቦታቸው መግባት፣

ለ. የቃላት አብሮነት ጉድለት፣

ሐ. ኢ-መደበኛ ቃላትን ያለቦታቸው መጠቀም፣

መ. ያራዳ ቃላትን ቦታ ሳይለዩ መጠቀም፣

ሠ. የሰለቹ አነጋገሮችን መደጋገም፣
/አምሳሉና ደምሴ፣ 1982፥97/፣

ረ. አንድን ሃሳብ ከሚገባው በላይ የሚያጋንኑና የተሰለቹ ሃረጐችን መጠቀም፡፡ /የቃላትን አጠቃቀም ችግርን በተመለከተ/፣

ሰ. ያለበቂ ምክንያት የፅሁፍን ተነባቢነት በሚያዳክም መልኩ ቃላትና ሐረጐችን መደጋገም፡፡ /ከቃላት ምስረታ ጋር በተያያዘ/ ፣

ሸ. ተፈላጊውን ሃሳብ ለመግለፅ የሚችሉ ቃላት በአማርኛ እያሉ በቅንጦትና በግድየለሽነት ያለ አግባብ የውጭ ቋንቋ ቃልን መጠቀም፣

ቀ .በቀጥታ ከውጭ በተተረጐሙ ቃላት መጠቀም ፣

በ. በተጠቃለለና በተዝረከረከ መልክ ሀሳብን ወይም ስሜትን በሚገልፁ ቃላት መጠቀም፣ /የቃላት ትርጉምን በተመለከተ/፣

ተ. የቃላት ድረታ፣/የቃላት ሰዋሰውን በተመለከተ/ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡(ዳኛቸው 1977፥31)

ለማጠቃለል ከዚህ በላይ የቀረቡት ክለሳ ድርሳናት

ሀ. ማንኛውም ነገር፣ ሁኔታ፣ ድርጊት፣ ወዘተ... ይታወቅና ከቢጤም ጋር ስለእርሱ የሚፈለገው ይባል ዘንድ ስያሜ መስጠት እንደሚያስፈልግ፣

ለ. ያለቃላት ማሰብ ካለመቻል በተጨማሪ የቃላት ውስብስብና ድርብርብ የትርጉም ውክልና፣ከሌሎች የቋንቋ ገፅታዎች የበለጠው ተለዋዋጭነት፣ ከአንድ ሰው የማስታወስ አቅም በላይ መብዛት፣ በአንፃሩም በተዛምዶ ለመማር የሚያስችል ውሱን የአደረጃጀት ህግ ያላቸው መሆን፣ በየጊዜው በፈጠራም በጥቅም ላይ የሚውሉ መሆን፣ ወዘተ... በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተለየ ትኩረት እንድንሰጣቸው ከምንገፋፋባቸው ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ስለሚያስገነዝብና

ሐ. በዚህም መሠረት ሀርመርና ሮዝነር /1991፡IX/ ፣ዋላስ /1982፡12/፣ አምሳሉና ደምሴ /1982፡49/፣ ሙረይ /1982፡15 19/፣ ዳኛቸው /1977፡56-59/፣ ሞርጋንና ሪኢንቨልክሪ /1986፡3/፣ ማካርቲ /1990፡8/ እና ፍሪስቢ /1957፡94/ በጥቅሉ ቃላትን መማር ማለት የቋንቋን ትምህርት በሙሉ መማር ማለት መሆኑንና ቃላት ለአራቱም ክሂሎች፣ ለሰዋሰውና ለስነ-ፅሁፍ ዕውቀት መሠረቶች ናቸው በማለት የሠጡትን የዚህን ጥናት ትወራዊ መሠረት ስለሚያጠናክር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም በ2.1 እና 2.2 ስር በዝርዝር የቀረበውን የ"እያሰሳችሁ፣ እየተሳተፋችሁ፣ እያጠናችሁና እየተገበራችሁ ቃላትን መማርን ተማሩ፡፡" የሚለውን በቃላዊ አተያይ ዘዴ አማካኝነት ቋንቋን የመማር ሒደት በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ መካተት አለመካተት ለመመርመር በ2.3 የቀረቡትን "የቃላት ትምህርት ችግሮች በኢትዮጵያ" መነሻ አድርጐ በቃላት ዘርፎች፣ በአሰሳ ይዘቶችና በሒደታዊ የክሒልና የዕውቀት ዘርፍ ቅንጅት ክንውኖች የአስተሳሰብ፣ የአቀራረብ፣ የትንተናና የስነ-ዘዴ ድጋፍ ሰጪነት ማጥናት የሚያስችል አስተዋፅኦ ስለሚያበረክትም ለመረጃ አሰባሰብና ትንተና ጠንካራ መሠረት እንደሚጥል ይታመናል፡፡ የክለሳ ድርሳናቱን ለዚህ ጥናት መነሻ ድጋፍ ሰጪነት በአስተሳሰብ፣ በአቀራረብ፣ በአተናተን፣ በትወራና በስነ-ዘዴ የሚጫወተውን ሚና ለማስተዋል በአባሪ "ረ" የቀረበውን ዝርዝር መፈተሻ /check list/ ይመለከቷል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች

### 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ /Descriptive/ የምርምር ዘዴን መሠረት በማድረግ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ገምግሞ ይተነትናል፣ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ ይሞክራል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ጥናቱ በመደበኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍን የቃላት አቀራረብ የሚመረምር እንደመሆኑ በጥናቱ ዓላማ መሠረት ተፈላጊውን ውጤት ለማግኘት ስራ ላይ የዋሉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች የመጽሐፍ ትንተና፣ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ-መጠይቅ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሥርም የናሙና አመራረጥ፣ የጥናቱ መረጃ ምንጮች፣ የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ስልቶች በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

### 3.2. የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣

ለ. በአዲስ አበባ መስተዳድር ከሚገኙ መደበኛ የመንግሥት ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በናሙናነት የተመረጡት /የከፍተኛ 4፣ የአብዮት ቅርስ፣ የወንድይራድ፣ የዳግማዊ ምኒልክ፣ የጥቁር አንበሳና አቃቂ/ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መምህራን እንዲሁም

ሐ. በሥርዓተ-ትምህርት የቋንቋ ቡድን መሪና የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች ናቸው፡፡

የ9ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን በመረጃ ምንጭነት የተመረጡበት ምክንያት ለመማር ማስተማሩ ስራ የሚገለገሉባቸውን መሣሪያዎች በቅርብ እንደሚያውቋቸው ስለታመነ፣ በክፍል ውስጥ ተራክቦ፣ በተማሪዎች የባሕሪ ለውጥና ተማሪዎች ቃላትን እንዲማሩ መማሪያ መጽሐፉ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በአንደኛ ደረጃ መረጃ ምንጭነት መመስከር የሚችሉ ስለሆነና አስተያየታቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል አስተሳሰብ ስላለ ነው፡፡ መጽሐፉን

በማዘጋጀት የተሳተፉት የትምህርት ባለሙያዎችም የመጽሐፉን ዝግጅት በማስተባበርና በመገምገም ተግባር ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆናቸው በመረጃ ምንጭነት ተፈላጊ ናቸው::

## 3.3 የናሙናዎች አመራረጥ

### 3.3.1. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

በአዲስ አበባ መስተዳደር የሚገኙትን 23 የመንግሥት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሙሉ በጥናቱ ውስጥ ለማስገባት በገንዘብ፣ በጊዜና በመሳሰሉት ምክንያቶች ቢያዳግትም ከላይ በ3.2/ለ/ የተዘረዘሩት ስድስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከስድስቱ የመስተዳድሩ ዞኖች በአመቺነት ናሙና /purposeful sampling/ መሠረት ተመርጠው በጥናቱ ውስጥ ትኩረት እንዲያገኙ ተደርገዋል:: በመሆኑም ከአዲስ አበባ መስተዳድሩ ትምህርት ቢሮ የተገኘውን የት/ቤቶች የስም ዝርዝር መነሻ በማድረግና ከየዞኑ መጀመሪያ ተፅፎ የሚገኘውን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በመውሰድና የርእሰ-መምህራኑን ትብብርና ስምምነት በቅድሚያ በማግኘት ከላይ በ3.2/ለ/ የተጠቀሱት ስድስት ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከዞን አንድ እስከ ዞን ስድስት በቅደም ተከተል ተመርጠዋል:: ይህ ዓይነቱ አመራረጥ በመስተዳድሩ የዞን ትምህርት መምሪያዎች መለያየት፣ በቦታ አቀማመጥ፣ ከመምህራን ምደባና ዝውውር አኳያ በመምህራን መካከል ምናልባት ሊኖር የሚችለው የልምድ መለያየትና ለመምህራኑ አስተያየት መነሻ ከመሆን አንፃር በተማሪዎችም መሀል ከዳርና ከመሀል አዲስ አበባ ከመምጣት አኳያ ምናልባት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መለያየት ምክንያት በመረጃ አሰባሰቡ ላይ ሊኖር የሚችለው የተዋፅኦ ስብጥር ለጥናቱ ካለው ጠቀሜታ አንፃር ታስቦና ተገምቶ የተደረገ ነው::

መጽሐፉ አማርኛን በአፍ መፍቻነትም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚናገሩትን ሳይለይ ለሁለቱም በእኩል ደረጃ እንዲጠቀሙበት የተዘጋጀ ስለሚመስል የሁለቱንም ዓይነት የቋንቋ ተጠቃሚዎች አንፃራዊ አስተያየት ከመምህራኑ መሰብሰብ ቢቻል ጠቃሚ እንደሚሆን በአጥኚው ተገምቷል:: በመሆኑም በአብዛኛው ከአቃቂና ወንድይራድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ ተማሪዎች እንደሚገኙ ሲጠበቅ ከሌሎችም ክልሎች በቅርብ ጊዜ በተለያየ ምክንያት የመጡ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የለመዱ የመጽሐፉ ተጠቃሚዎች እንደማይታጡ ባለመዘንጋትም ጭምር ነው::

### 3.3.2. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ናሙና አመራረጥ

ከመስተዳደሩ ስድስት ዞኖች በአመቺነት ናሙና በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን በጠቅላላ አሥራ ዘጠኝ ብቻ ናቸው:: በዚህም ምክንያት በት/ቤቶቹ ውስጥ ያሉት መምህራን ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ

ናሙና መውሰድ ሳያስፈልግ በት/ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩት የ9ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን በሙሉ በጥናቱ እንዲታቀፉ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

### 3.3.3. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ተሳታፊዎች አመራረጥ

መጽሐፉ የተዘጋጀው በአገርአቀፍ ደረጃ በመሆኑ በጥናቱ ውስጥ ለመረጃ ሰጭነት የተመረጡት ሰዎች በዚሁ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡ መረጃዎችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ማግኘቱ ለጥናቱ ብስለት ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ በመታመኑ እነዚሁ በሀገረአቀፍ ደረጃ ያሉ የሥርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች ለጥናቱ መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት አንድ የቡድን መሪና ሦስት የመጽሐፉ ዝግጅት ቡድን አባሎች ብቻ በመሆናቸው በቁጥራቸው አናሳነት የተነሳ ያለ ናሙና መውሰድ 4ቱም የዝግጅት ተሳታፊዎች በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ታስቦ ነበር፡፡ ሆኖም ከመጽሀፉ አዘጋጆች ሁለቱ በጡረታና በዝውውር ከተቋሙ ስራቸውን በመልቀቃቸው አጥኚው ሊያገኛቸው ባለመቻሉ የቋንቋ ቡድን መሪውና አንድ የመጽሀፉ አዘጋጅ ብቻ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

### 3.3.4. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፎች ናሙና አመራረጥ

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በርካታ ጥያቄዎችን በማካተት በሦስት የተከፈሉ መልመጃዎችን በተናጠል ያስከተሉና እንደ ምዕራፍ የሚቆጠሩ 16 ምንባቦች ይገኛሉ፡፡ የአጥኝውን አቅምና የጊዜውን መጣበብ በማገናዘብ 25% /በቁጥር 4/ የሚሆኑት በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

እነዚህን ምንባቦች /ምዕራፎች/ ከጠቅላላው ለይቶ ለማውጣትም አጥኚው የተጠቀመው ስርአታዊ ናሙና /Systematic Sampling/ ዘዴን ሲሆን ክንውኑም ተፈላጊው ቁጥር /4/ እስኪገኝ ድረስ ከተራ ቁጥር 4 በመጀመርና በመጽሐፉ የምንባቦች ቅደም ተከተል አቀማመጥ መሠረት አራት አራት ምንባቦችን በመዝለል ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከአሥራ ስድስቱ የመጽሐፉ ምዕ ራፎች በጥናቱ የታቀፉት ምዕራፍ 4፣8፣12ና16 ሊሆኑ ችለዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.4.1. የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ

ለጥናቱ የሚያግዙ መረጃዎችን ለማሰባሰብ በ9ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን የሚሞላ የጽሁፍ መጠየቅ ተዘጋጅቷዋል፡፡ ይህም መጠይቅ የሚከተሉት ዋና ዋና አላማዎች አሉት፡፡

1. የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን ፍላጐት ምን ያህል እንደሚያነሣሱ ማወቅ፣

2. በመምህሩ ግንዛቤ አማካኝነት የመጽሀፉ የቃላት መልመጃዎች አቀራረብ ሥልት የተማሪዎችን ክሂልና እውቀት ለማዳበር የሚያስችል አስተዋጽኦ ያበረክቱ እንደሆነ ለማወቅና

3. የመጽሀፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በክፍል ውስጥ ተራክቦ ምን ያህል ተጽእኖ እንዳሳደረ ለማወቅ የታቀዱ ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት ለጥናቱ በተመረጡ በ6 የመንግስት መደበኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን በ9ኛ ክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበው መጠይቅ 49 ጥያቄዎችን የያዙ 5 ክፍሎች አሉት፡፡ ጥያቄዎቹም በአጥኚው ከተዘጋጁ በኋላ አስተማማኝነታቸውን፣ ግልፅነታቸውንና የቅደም ተከተል አጠባበቃቸውን ለማረጋገጥ ሲባል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

i/ በውጭ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል /Foreign Languages and Literature/ ፣

ii/ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል/Ethiopian languages and literature Department/ ና

iii/ በስነልሳን ክፍል /Linguistics department/ የሚያስተምሩ 3 መምህራን /ባለሙያዎች/ እንዲገመገሙ ተደረጓል፡፡ ባለሙያዎቹ ያቀረቡአቸው የማሻሻያ ሀሣቦች ከተካተቱ በኋላ መጠይቁ በዋናው ጥናት ላልታቀፉ 6 መምህራን ቀርቦ ተሞክሯል፡፡ ይህ ወቅት የምርምሩ መነሻ ጥናት/Pilot study/ የሚካሄድበት ወቅት ስለነበረ ለፅሁፍ መጠይቁ መሻሻል የቀረበው ሀሳብ የፅሁፍ መጠይቁን እንደገና ለማስተካከል አስችሏል፣ ማለትም የጽሁፍ መጠይቁ በመነሻ ጥናቱ ከተሞከረ በኋላ መምህራኑ የሠጧቸውን መልሶችና አስተያየቶች መሠረት በማድረግ ለጥናቱ አስፈላጊ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ለማስወገድ፣ ግልፅ ያልሆኑ ቃላትንና ሀረጋትን በመለወጥ አደናጋሪ /ጊዜ ፈጂ/ በመሆናቸው በመምህራኑ ትኩረት ያልተሠጣቸውን ጥያቄዎች ወደ መልስ አስመራጭ እንደአስፈላጊነታቸው በመቀየር ወዘተ ... የጽሁፍ መጠይቁ ለመጨረሻ ጊዜ ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

የጽሁፍ መጠይቁ በአጠቃላይ ጥያቄዎችን በ5 ክፍሎች በመክፈል የሚከተሉትን አካቷል፡፡

ሀ. “መግቢያ” በሚለው ክፍል ውስጥ በጽሁፍ የመጠይቁን አላማ በግልፅ አስቀምጧል

ለ. በጽሁፍ በመጠይቁ ክፍል አንድም የግል ሁኔታን ለመግለፅ ያስችል ዘንድ ስለመምህራኑ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና ወዘተ በመጠየቅ ዳራቸውን /background/ ለማወቅ በሚደረገው ጥረት ተገቢ አስተዋጽኦ ይኖረው ዘንድ 8 የምርጫ ጥያቄዎችን እንዲይዝ ተደርጐ ተዘጋጅቷል፡፡

ሐ. በጽሁፍ በመጠይቁ ክፍል ሁለትም የመማሪያ መፅሀፉን የቃላት መልመጃዎች በተመለከተ 27 ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚም 4 አማራጭ መልሦች ያሏቸው ሲሆን 27ቱም ጥያቄዎች የቃላትን ሁለንተናዊ ገጽታዎች በተመለከተ የክፍል ውስጥ ክንውን ሁኔታን ለመመርመር በሚያስችል መልክ በደረጃ ቅደም ተከተል በተዘጋጁ መመዘኛ አማራጮች እንዲመለሱ ሆነው ቀርበዋል፡፡

መ ክፍል ሦስት የመልመጃዎችን አሠራር በተመለከተ የመማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች የክፍል ውስጥ አተገባበር ሁኔታ ለመመርመር የሚያግዙ 4 ጥያቄዎች፣

ሠ. በክፍል 4 የቃላት መልመጃዎቹ በተማሪዎቹ የባህሪ ለውጥ ላይ የሚጫወቱትን ሚና በተመለከተ 9 የምርጫ ጥያቄዎች በክፍል 5 በመማሪያ መፅሀፉ የሚገኙ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶችን /Strategies/ እና ሌሎች ዘመናዊ ሥልቶችን በተመለከተ መምህራን ነፃ አስተያየታቸውን የሚሰጡበት አንድ ጥያቄ ያለ ምርጫ በቀጥታ /openended question/ በድምሩ 49 ጥያቄዎች ተካትተዋል፡፡

አማራጭ መመዘኛዎችን በሚመለከት ከአማራጮቹ መሀል 4 የውሳኔ ሀሳቦችን በጋራ የያዙ ጥያቄዎች ይገኙበታል፡፡ እነዚህም በሊከርት የደረጃ እስኬል /Likert Raiting Scale/ የተዘጋጁ ሲሆን ተጠያቂዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ገለልተኝነትን ወደሚመለከተው "አስተያየት የለኝም" ወደሚለው መካከለኛ አማራጭ እንዳያዘነብሉ ለመከላከል ሲባል ምርጫዎቹ ከ5 ወደ 4 ዝቅ ብለዋል፡፡ በመሆኑም የውሣኔ ሀሣቦቹ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ገለልተኝነት አቋምን ሳይጨምሩ ተዘጋጅተዋል፡፡

የጽሁፍ መጠይቁ ከላይ በተጠቀሰው ተዋረድ ተዘጋጅቶ እንደተጠናቀቀ ቀደም ሲል በተመረጡት 6 ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ቋንቋውን በሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር ልክ ተባዝቶ ተሰራጨ፡፡ አጥኚው መጠይቁን ካሠራጨ በኋላ ለመምህራኑ በሠጠው የሁለት ሣምንት ጊዜ ውስጥ ተሞልቶ ተመልሷል፡፡ እንደተመለሠም የተሠራጨውና የተመለሠው ቁጥር በመቶኛ ተሠልቶ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 1 የመምህራን መጠይቅ ሥርጭት

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የተሠራጨው ብዛት | የተመለሰው ብዛት | መቶኛ /%/ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ 4 ከፍተኛ 2ኛ/ደ/ት/ቤት | 4 | 4 | 100 |
| 2 | አብዩት ቅርስ ከፍተኛ 2ኛ/ደ/ት/ቤት | 2 | 2 | 100 |
| 3 | ወንድይራድ ከፍተኛ 2ኛ/ደ/ት/ቤት | 5 | 4 | 80 |
| 4 | ዳግማዊ ምኒልክ አጠቃላይ 2ኛ/ደ/ት/ቤት | 4 | 4 | 100 |
| 5 | ጥቁር አንበሳ ከፍተኛ 2ኛ/ደ/ት/ቤት | 2 | 2 | 100 |
| 6 | አቃቂ ከፍተኛ 2ኛ/ደ/ት/ቤት | 2 | 2 | 100 |
| | ጠቅላላ ድምር | 19 | 18 | 94.7 |

በዚህ ጥናት ስለተማሪዎች መረጃ የሚሰጡት መምህራኑ እንጂ ተማሪዎች አለመሆናቸው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡፡

ምክንያቶቹም 1. የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ዕድሜና ብስለት ለመጽሐፉ ግምገማ በቂ ነው ተብሎ አለመታመኑ፣

2. መምህራን በማስተማር /ስርዓተ ትምህርቱን/ በመገምገምና በውስጡ በማለፍ የሚሰጡት ጠቀሜታ የተማሪዎችንም አስተያየት ሊጠቀልል ይችላል ተብሎ መታሰቡ ናቸው፡፡

መጠይቁን በአባሪ "ሀ" ይመልከቱ፡፡

### 3.4.2 ቃለ-መጠይቅ

ቃለመጠይቅ የቀረበው በፌድራሉ በስርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ ጥናትና ምርምር ተቋም ለቋንቋ ቡድን መሪውና ለ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ አንድ አዘጋጅ ነው፡፡

የቃለመጠይቁ ዋና አላማ የመማሪያ መፅሀፉን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ዝግጅት የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ንድፈ ሀሣብ /Theory/ እንደተከተለ ለቃላት አመራረጡና አቀራረቡ በዝግጅቱ ወቅት አዘጋጆቹ የተከተሉት ሞዴል እንዳለ ወይም /እንደሌለ/ና በአጠቃላይ የትኛውን የቋንቋ ንድፈ ሀሣብ /Theory/ተከትለው እንዳዘጋጁት ለማወቅ ነው፡፡

ቃለ-መጠይቆቹ ለቋንቋ ቡድኑ መሪና አንድ አዘጋጅ በቅድሚያ እንዲዘጋጁበት በፅሁፍ ከመሠጠታቸው በፊት የጽሁፍ መጠይቁን ለገመገሙት 3 ባለሙያዎች ተሰጥተው ውይይት ከተደረገባቸውና ማሻሻያ ከታከለባቸው በኋላ በስራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

የአሠራር ሂደቱን በሚመለከት በአጥኚው እየተነበበ ተጠያቂዎች ሀሣባቸውን ሲገልጹ በጽሁፍ እንዲመዘግቡና በመቅረጸ-ድምጽ እንዲቀረጽ ተደርጓል፡፡ ቃለ መጠይቆቹና መልሶቹም በጥናቱ ውስጥ በአባሪነት ተያይዘዋል፡፡ /አባሪ "ለ" "ሐ"፣"መ"፣ ና "ሠ" ይመልከቱ/

### 3.4.3. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ጥናቱ በተለይ በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ የቃላት አቀራረብ ላይ ቢያተኩርም ቃላት ሚና የማይጫወቱበት ክሂልም ሆነ የእውቀት ዘርፍ ባለመኖሩ፣ የተሻለ የሚባለው የማስተማሪያ ዘዴም ክሂሎችን የእውቀት ዘርፎችንና ልዩ ልዩ የቋንቋ ገጽታዎችን በቃላት ትምህርት አቀናጅነት በውህደት የሚያስተምረው እንደሆነ በአጥኚው በመታመኑ፣ በርካታ ምሁራን በጥናታቸው ስለሚጠቁሙና "እያሳሳችሁ በመሳተፍ በማጥናትና በመተግበር ቃላትን መማርን ተማሩ" በሚል መርህ በናሙናነት የተመረጡ 4 የመፀሀፉ ምዕራፎች በተናጠልና በቅንጅት ይመረመራሉ፡፡

1. በአሰሳ የቃላትን ሙሉ ሀይል ለመጠቀም ከሚያስችል ሁለንተናዊ ገጽታ አንፃር ቃላትን ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ በሚመልስ መልኩ የቃላት ዘርፎችንና ይዘቶችን ያካተቱ የቃላት መልመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ይገኙና አይገኙ እንደሆን፣
2. በተሳትፎ፣ በጥናትና በትግበራ ክንውኖች ተናጠላዊና ህብረታዊ አካሄድ የመጽሀፉ መልመጃዎች በቃላት የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች አቀናጂነት 'ሚና ንግግርንና ማዳመጥ'ን፣ ንባብን፣ ጽህፈትን፣ ስነ-ጽሁፍንና ስነ-ልሳንን እያዳበሩ መሆን አለመሆናቸውን በሚፈትሹ ዝርዝር ነጥቦች ይመረመራሉ፡፡

ከ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በናሙናነት የተወሰዱትን ምንባቦችና መልመጃዎች ለመገምገም የተዘጋጀው ቃላዊ ዝርዝር መፈተሻ /Lexical Check-list/ ተግባራዊ ዓላማ ከመማሪያ መጽሀፉ ትንተና የሚገኘውን መረጃ አጠናክሮ ለማሰባሰብ ሲሆን ምንጮቹም በስሩ የተዘረዘሩት ፀሐፊዎችና መፅሀፎቻቸው ናቸው፡፡ በተመረጡት ናሙና የ9ኛ ክፍል የቃላት፣ የክሂልና የዕውቀት ዘርፍ መልመጃዎች ላይ ዝርዝር መፈተሻዎቹን በመጠቀም ግምገማውን የሚያካሒደው የዚህ ጥናት ተመራማሪ ከመሆኑም በላይ ዝርዝር መፈተሻው ለመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ዝግጅትም በመነሻነት አገልግሏል፡፡

በዝርዝር መፈተሻው ይተነተኑ ዘንድ በናሙናነት የተወሰዱት የ9ኛ ክፍል ምንባቦች

1. ምንባብ አራት /"ደብዳቤዎች"/፡
2. ምንባብ ስምንት /"የገብርዬ ፈተና - ክፍል-1"፣
3. ምንባብ አስራ ሁለት /"ሰውና እባብ"/፣
4. ምንባብ አስራ ስድስት /"የወላጅ ናፍቆት/ና እነዚህኑ ምንባቦች ተከትለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የቋንቋ ጥያቄዎችን በሙሉ የያዙት መልመጃዎች ናቸው፡፡

ዝርዝር መፈተሻዎቹ በመፅሐፉ መተንተኛነት በስራ ላይ የዋሉት በየቃላት ትምህረት ዘርፉ ስር በተዘረዘሩት የቃላት አሰሳ ይዘቶች የመማሪያ መፅሐፉን የቃላት መልመጃዎች መድቦ ብዛትና መቶኛቸውን በመለየት፣ የክሒልና የእውቀት ዘርፍ መልመጃዎቹን በአራቱ ክሒሎችና በሁለቱ የዕውቀት ዘፍሮች ስር በንዑሳን ክፍሎቻቸው ከፋፍሎ ብዛትና መቶኛቸውን ከመፈተሻው ነጥቦች አኳያ እየተነተኑ በፈርጅ በፈርጅ በመተርጐም ነው፡፡ ለዚህ አሰራር መሠረት የሆነው ትወራ /Theory/ ቃላዊ እይታ /Lexical Approach/ ሲሆን መነሻውም "ትርጉም የተግባቦት ማዕከል ነው" የሚል ሆኖ ቃላት በትርጉማዊ፣ ባጠቃቀማዊ፣በምስረታዊና በሰዋሰዋዊ ዝርዝር ሚናቸው አራቱን ክሒሎች ንግግር፣ ማዳመጥ፣ ንባብና ፅሀፈት እንዲሁም ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች /ስነ-ፅሁፍንና ስነ-ልሳንን/ ስለሚያቀናጁ "የቋንቋ ትምህርት የቃላት ትምህርት ነው" የሚል ነው፡፡ በቃላዊ አተያይ /Lexical Approach/ የቃላት የክሒሎችና የዕ ውቀት ዘርፍ አቀናጅነት ሚና በስዕል ሲገለፅ የሚከተለውን ይመስላል፡፡




ይህም ሲጠቃለል "እያሰሳችሁ በመሳተፍ፣ በማጥናትና በመተግበር ቃላትን በተናጠል ሳይሆን በልዩ ልዩ ውስብስብ ግንኙነቶቻቸው ቃላትን ብሎም ቋንቋን መማርን ተማሩ" የሚለውን የዚህን ጥናት መሠረታዊ መርህ ይሰጠናል፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ "ረ"ን ይመልከቱ /ሀርመርና ሮዝነር፣ 1991፡xii/፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃዎች ትንተና

ይህ ምዕራፍ በተለያዩ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበትና የሚብራሩበት ክፍል ነው፡፡ የጥናቱ መሠረታዊ አላማ በመደበኛ ትምህርት አገልግሎት በ1984 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ በቀጣዩ አመት በስራ ላይ በመዋል እስከ አሁን በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ደረጃ ለመደበኛ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ የሆነውን መጽሃፍ የቃላት ትምህርት ብቃት ለመመርመር መሆኑ ቀደም ብሎ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ ክፍል የሚቀርበው ትንተናም በጥናቱ መነሻ ላይ የቀረቡትን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል፡፡ ጥያቄዎቹም በጥቅሉ፡-

"በአሁኑ ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተመሠረተባቸው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች / Methods/ ቴክኒኮች /Techniques/ና ስልቶች /Strategies/ተማሪዎች ቃላትን እንዲማሩ በማስተማር ላይ ያተኮሩ ናቸው?" በሚል መሪ ጥያቄ ስር የተካተቱ ሲሆን ፣ በዝርዝርም፡-

1. የቃላት መልመጃዎቹን እያሰላችሁ ተሳተፉ፣ አጥኑና በተግባር ተርጉሙ የሚለውን ስልታዊ አካሄድ /pattern/መሠረት በማድረግ ተማሪዎች አንድ ወጥ የሆነውን ተግባራዊ የቃላት ማስፋፊያ መንገድ እንዲከተሉ ያደፋፍራሉ?

2. የቃላቱ አቀራረብ ስልት ትርጉምን፣ የቃላት አጠቃቀምን፣ ምስረታንና የቃላት ሰዋሰውን በተገቢ ስርጭት አካተው ይዘዋል?

3. በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኘው የቃላት ትምህርት አቀራረብ በመጽሐፉ መግቢያ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት፣ የክሂልና የእውቀት ዘርፍ አላማዎች ለመተግበር የሚያግዝ ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ለእነዚህም ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በሀርመርና ሮዝነር /1991፡1/ እንደተጠቀሰው በመማሪያ መጽሐፉ ትኩረት የተሰጠው የክሂልና የእውቀት ዘርፎች ቅንጅት ቃላትን መማርን፣ በመማር ዘዴ ላይ የተመሠረተና ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ መሆን አለመሆኑን በመገምገም ለተግባራዊ የቋንቋ ትምህርት አመችነት እንዳለው መፈተሽ ነው፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ በመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያነት በጥቅም ላይ የዋሉትን 1. የመማሪያ መጽሀፉን ይዘት

ትንተና፣ 2. በፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ትንተና እና 3. በቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተናን መሠረት በማድረግ ወደ ተገቢው ድምዳሜ ለመድረስ ተሞክሯል፡፡

### 4.1.1. ከመማሪያ መጽሀፉ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ክፍል የቀረበው ትንተና መማሪያ መፅሀፉ ለቃላት ትርጉም፣ ለቃላት አጠቃቀም፣ ለቃላት ምሥረታና ለቃላት ሰዋሰው ዘርፎችና እንዲሁም ለአሰሳ ይዘቶች ምን ያህል ትኩረት ሰጥቷዋል? ለተግባራዊነታቸውስ የትኞቹን ቃላትን መማርን የመማር ቴክኒክና ስልቶች ለመጠቀም ሞክሯል? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ "እየተሳተፋችሁ፣ እያጠናችሁና እየተገበራችሁ በማሰስ ቃላትን መማርን በመማር ዘዴ ቋንቋን ተማሩ" የሚለውን ቃላትን በተናጠል ከማስተማር ይልቅ በዝምድናቸው፣ ትንተናዊ የቃላት ማስተማሪያ ስልትን ከመጠቀም ይልቅ ግልጋሎታዊ ስልትን በስራ ላይ በማዋል ቃላትን፣ ብሎም ቋንቋን የሚያስተምረው መርህ በተግባር ላይ ውሎና አልውሎ እንደሁ በመከታተል ተሳትፎን፣ ጥናትን፣ ትግበራንና አሰሳን በመረጃ ትንተና መስፈርትነት ይጠቀማል፡፡

ለትንተናው አመቺ ይሆን ዘንድ አጥኚው የተከተለው ያሰራር ሂደት ከመማሪያ መጽሐፉ አስራ ስድስት ምዕራፎች መሀል አራቱን /25 %/ በስርዓታዊ ናሙና (Systematic Sampling) በመምረጥ

ሀ/ በቃላት የአሰሳ ቴክኒክና

ለ/ በመልመጃዎች አካሄድ እድገታዊ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ላይ በመመስረት የተመረጡት መልመጃዎች ምን ባህሪ እንደሚያሳዩ መመርመር ሲሆን፣ ይህም የተካሄደው የመማሪያ መጽሐፉን የቃላት ትምህርት፣ የክሂልና የእውቀት ዘርፍ መልመጃ ጥያቄዎች በመስፈርቱ መነሻነት በመመደብና የምደባውን ውጤት በመተርጐም ነው፡፡

#### 4.1.1.1 የመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች የአሶሳ ቴክኒክ ብቃት

ተማሪዎች በማሰስ ይማሩ ስንል

1. በትርጉም ዘርፍ ስር አውዳዊነት፣ የትርጉም ዝምድናዎች ማለትም /ተመሳሳዮች፣ ተቃራኒዎችና፣ተካቶዎች፣ ድርብርብ የትርጉም ውክልና ያላቸው ቃላትና መዝገበ-ቃላዊ ፍቺ እንዲኖራቸው ተደርጐ የቀረቡ፣

2. በቃላት አጠቃቀም ስር ተለዋጮች፣ ፈሊጦች፣ ተረትና ምሣሌዎች፣ የቃላት አብሮነቶች፣ ምስያዎች፣ መደበኛና ኢመደበኛ ቃላትና ሙያ ነክ ቃላት፣

3. በቃላት ምስረታ ስር የሚጠብቁና የማይጠብቁ ድምፆች የትርጉም ልዩነት የሚያሳዩባቸው ቃላት፣ በቅጠላ የሚመሰረቱ ቃላት በጥመራ የሚመሠረቱ ቃላትና

4. በቃላት ሰዋሰው ስር በንግግር ክፍሎች ውስጥ የሚካተቱት ስም፣ ቅፅል፣ ተውሳከ ግስ፣ ግስ፣ መስተዋድድና ቀጣይ ምዕላዶች /የመደብ፣ የጾታ፣ የቁጥር፣ የጊዜ፣ የባለቤት፣ ወዘተ... / በተማሪዎች የግል ጥረትና በመምህሩም አስተባባሪነት ቃላትን ሳይሆን ቃላትን መማርን ይማሩ ማለታችን ነው፡፡ ዝርዝሩን ከዚህ በታች በቀረቡት ሰንጠረዦችና ማብራሪያዎቻቸው ይመለከቷል፡፡

2. በቃላት አጠቃቀም ስር ተለዋጮች፣ ፈሊጦች፣ ተረትና ምሣሌዎች፣ የቃላት አብሮነቶች፣ ምስያዎች፣ መደበኛና ኢመደበኛ ቃላትና ሙያ ነክ ቃላት፣

3. በቃላት ምስረታ ስር የሚጠብቁና የማይጠብቁ ድምፆች የትርጉም ልዩነት የሚያሳዩባቸው ቃላት፣ በቅጠላ የሚመሰረቱ ቃላት በጥመራ የሚመሠረቱ ቃላትና

4. በቃላት ሰዋሰው ስር በንግግር ክፍሎች ውስጥ የሚካተቱት ስም፣ ቅፅል፣ ተውሳከ ግስ፣ ግስ፣ መስተዋድድና ቀጣይ ምዕላዶች /የመደብ፣ የጾታ፣ የቁጥር፣ የጊዜ፣ የባለቤት፣ ወዘተ... / በተማሪዎች የግል ጥረትና በመምህሩም አስተባባሪነት ቃላትን ሳይሆን ቃላትን መማርን ይማሩ ማለታችን ነው፡፡ ዝርዝሩን ከዚህ በታች በቀረቡት ሰንጠረዦችና ማብራሪያዎቻቸው ይመለከቷል፡፡

## በ 1984 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሐፍ የቃላት መልመጃዎች መግለጫ ከአሰሳ ቴክኒክ ብቃት አንፃር

ሠንጠረዥ 2

| ተ.ቁ | የቃላት ትምልርት ዘርፎች | የቃላት አሰስ ይዘቶች | የመማሪያ መጽሐፍ የቃላት ጥያቄ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አተናተን | | አጠቃቀም | | አብይ የአሰሳ ይዘቶች ድምር | | ንዑስ የአሰሳ ይዘቶች ድምር | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | የቃላት ትርጉም ዘርፍ /Word Meaning/ | 1.1 አውዳዊ ፍቺ | 3 | 42.86 | 4 | 57.14 | - | - | 7 | 14.58 |
| | | 1.2. የትርጉም ዝምድናዎች | 31 | 100 | 0 | 0 | - | - | 31 | 64.58 |
| | | 1.2.1 ተመሣሣይ | 21 | 67.74 | 0 | 0 | 21 | 61.74 | - | - |
| | | 1.2.2 ተቃራኒ | 10 | 32.26 | 0 | 0 | 10 | 32.26 | - | - |
| | | 1.2.3 ተካትቶ | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - | 0 | 0 |
| | | 1.3 ድርብርብ የትርጉም ውክልና ያላቸው ቃላት | 0 | 0 | 6 | 100 | - | - | 6 | 12.50 |
| | | 1.4 መዝገበ ቃላዊ ፍቺ | 4 | 100 | 0 | 0 | - | - | 4 | 8.33 |
| | | ድምር | 38 | 79.16 | 10 | 20.83 | 31 | 64.58 | 48 | 48.97 |
| 2 | የቃላት አጠቃቀም ዘርፍ /Word use/ | 2.1 ተለዋጮች /Metaphors/ | 12 | 92.31 | 1 | 7.69 | - | - | 13 | 65 |
| | | 2.2 ፈሊጦች /Idioms/ | 5 | 83.33 | 1 | 16.67 | - | - | 6 | 30 |
| | | 2.3 ተረትና ምሣሌ /Proverbs/ | 1 | 100 | 0 | 0 | - | - | 1 | 5 |
| | | 2.4 የቃላት አብሮነት | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - | 0 | 0 |
| | | 2.5 ምስያዎች /Analogies/ | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - | 0 | 0 |
| | | 2.6 መደበኛ ቃላት /Formal words/ | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - | 0 | 0 |
| | | 2.7 ኢ. ፤ መደበኛ ቃላት /Informal wards/ | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - | 0 | 0 |
| | | 2.8 ሙያ ነክ ቃላት /Technical words/ | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - | 0 | 0 |
| | | ድምር | 18 | 90 | 2 | 10 | - | - | 20 | 20.40 |
| 3 | የቃላት ምሥረታ ዘርፍ | 3.1 ቅጠላዎች /Affixations/ | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - | 0 | 0 |
| | | 3.2 ጥመራዎች /Compounding/ | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - | 0 | 0 |
| | | 3.3 ሆሄያትና ድምጾች /Spelling & Sound | 4 | 100 | 0 | 0 | - | - | 4 | 100 |
| | | ድምር | 4 | 100 | 0 | 0 | - | - | 4 | 4.08 |
| 4 | የቃላት ሰዋሰው | 4.1 የንግግር ክፍሎች /Parts of Speech/ | 0 | 0 | 13 | 100 | - | - | 13 | 50 |

| ተ.ቁ | የቃላት ትምልርት ዘርፎች | የቃላት አሰስ ይዘቶች | የመማሪያ መጽሐፍ የቃላት ጥያቄ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አተናተን | | አጠቃቀም | | አብይ የአሰሳ ይዘቶች ድምር | | ንዑስ የአሰሳ ይዘቶች ድምር | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | /Word Grammar/ | | | | | | | | | |
| | | 4.1.1 ስም | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - |
| | | 4.1.2 ቅፅል | 0 | 0 | 5 | 38.46 | 5 | 38.46 | - | - |
| | | 4.1.3 ግስ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - |
| | | 4.1.4 ተውሳከ ግስ | 0 | 0 | 5 | 38.46 | 5 | 38.46 | - | - |
| | | 4.1.5 መስተዋድዶች | 0 | 0 | 3 | 28.08 | 3 | 23.08 | - | - |
| | | ድምር | 13 | 100 | 0 | 0 | 13 | 50 | 13 | 13.27 |
| | | 4.2 ቀጣይ ምዕላዶች Morphems/ | 13 | 100 | 0 | 0 | - | - | 13 | 50 |
| | | 4.2.1 የመደብ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - |
| | | 4.2.2 የጾታ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | - | - |
| | | 4.2.3 የቁጥር | 7 | 53.85 | 0 | 0 | 7 | 53.85 | - | - |
| | | 4.2.4 የጊዜ | 1 | 7.69 | 0 | 0 | 1 | 7.69 | - | - |
| | | 4.2.5 የአሉታ | 1 | 7.69 | 0 | 0 | 1 | 7.69 | - | - |
| | | 4.2.6 የባለቤት | 4 | 30.77 | 0 | 0 | 4 | 30.77 | - | - |
| | | ድምር | 13 | 100 | 0 | 0 | 13 | 50 | 13 | 13.27 |

የዚህ ሰጠንረዥ መልዕክት በቃላዊ መስፈርቱ ሲመረመር፣

የሰንጠረዥ 2 ን መልእክት በቃላዊ ዝርዝር መፈተሻዎቹ ስንመረምር የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ አውዳዊ የቃላት ትርጉም ገፅታ ከትንተናና አጠቃቀም የቋንቋ ትምህርት ሚና አንፃር ሲታይ በአጠቃቀም ሰባት ጥያቄዎችን በማስመዝገብ (57.14%) ጥያቄዎቹ በቋንቋ ግልጋሎታዊ ባህሪ ላይ አተኩረው ቢገኙም የስርጭት ሁኔታቸውን በሚመለከት ከአብይ ክፍላቸው ከትርጉም ገፅታ ይዘቶች ጋር ሲወዳደሩ ግን (14.58%) በሚሆኑ ጥያቄዎች ስርጭት ብቻ በመወከላቸው የመማሪያ መፅሐፉ የቃላትን ሁለንተናዊ ገፅታ በአውድ የማስለየት ደረጃ ዝቅ የሚያደርግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ያው (57.14%) ከራሳቸው፣ (14.58%) ከትርጉም ዘርፍ ገፅታና (7.1%) ከጠቅላላው በናሙና ከተወሰዱት የመፅሐፉ የቃላት ጥያቄዎች 100% አንፃር የተገኘው ግልጋሎታዊ ገፅታቸውም ከሰንጠረዡ ወጣ ባለ ተጨማሪ ማስረጃ ሲመረመርም፡-

ሀ. ሁሉም ግልጋሎታዊ የቋንቋ ባህሪ ገፅታ አመልካች ጥያቄዎቻቸው "ቃላትና ሐረጎችን በዐ.ነገር በማስገባት ፍቻቸውን ጠቁም" በሚል በየአካባቢው ለየት/ቤቱና በየተማሪው ሁኔታ ከፍተኛ ልዩነትን በመፍጠር ወጥነት የሌለውና የትምህርት ደረጃን እኩልነት ሊያስጠብቅ በማይችል የክፍል ውስጥ ክንውን ተፅእኖን ያሳድራል፡፡ ይህንንም ለናሙና በተወሰዱት ምንባቦች ከምንባብ ስምንት፣ መልመጃ ሁለት ጥያቄ "መ" ና ከምንባብ አስራ ስድስት መልመጃ ሁለት ጥያቄ ሁለት ከ "ሀ"-"መ" ባሉት የቃላት ጥያቄዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ለ. አውዳዊ ነሲብ የምንባብ መማሪያ ቴክኒክን ስለማይጠቀሙ በዚህ ጥናት ክለሳ ድርሳናት (Review of related Litrature) ማስረጃ መሰረት ትርጉም ጠቋሚ በመፅሐፉ ውስጥ ፍንጮችን ተማሪዎች እንዲያውቁ የሚደረግበት የመጽሐፍ ክፍል ተለይቶ እንዲታወቅ ስላልተደረገ የመፅሐፉ የቃላት ጥያቄዎች አውዳዊ ገፅታ በአሰሳ ቴክኒክ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ድርብርብ የትርጉም ውክልናን በሚመለከትም በስርጭት ከአውዳዊ ገፅታ ቢያንስም በአውዳዊ ገፅታ የተጠቀሱት የአጠቃቀም ውሱንነትና የሁለንተናዊ ገፅታ ሚና አጎልባችነት ችግር ጎልቶ የሚታይበት በመሆኑ የመማሪያ መፅሐፉ የአሰሳ ቴክኒክ ተግባራዊነት ችግር የማያጣው ሆኖ ይታያል፡፡ ከዚሁ ጋር በአብዛኞቹ የቃላት አሰሳ ይዘቶች ጥያቄ አቀራረብ ተማሪዎች መልሶችን ከግል እውቀታቸው፣ ከመምህራን

ድጋፍና ከንባብ እንዲያገኙ እንጂ በመፅሐፉ አዘጋጅ በቀረቡ ከመፅሐፉ በስተጀርባ ከሚገኙ መልሶች የጥያቄዎችን መልስ በማመሳከር የአማግር ስልቶችን በሒደታዊ አቀራረብ ከመማር ይልቅ በውጤታዊ ስልት ላይ ብቻ በተመሰረቱ አጫጭር መልስ ባላቸው ጥያቄዎች አመላለስ ተግባር ብቻ ስለሚወሰኑ ተግባቦታዊ ችሎታን የማዳበር ሚናቸው የተገታ ይመስላል፡፡

1.4. የመጽሀፉን የትርጉም ዝምድና ገጽታ ስንመለከት ከሰንጠረዡ የምናገኘው መረጃ ተመሳሳይ ቃላትን ያለ አውድ በቀረቡ 21 (67.74%) የቃላት ጥያቄዎች ተወክሎ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም ተመሳሳይ የትርጉም ዝምድና በአጠቃቀም ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ በትንተና ላይ ከማተኮሩም በላይ በመማሪያ መጽሀፉ በአንድም ቦታ እንኳ የተመሳሳይ ቃላትን የተመሳስሎና የልዩነት ባህሪያት ከመጠየቅ አልፎ በምሳሌነት ስለማይጠቅሱ ተማሪዎች ራስን በመቻል መርህ የመምህራኑን ብቸኛ ድጋፍ በመፈለግ የግልና የቡድን ጥረታቸውን አጠናክረው እንዳይቀጥሉ ከሚያደርግ የጥገኝነት አሰራር የሚያላቅቅ አይመስልም፡፡ የተቃርኖ የቃላት ግንኙነቶቹም ቢሆኑ በተመሳሳይ የትርጉም ዝምድና የተከሰቱት ችግሮች በድጋሚ የሚታይባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ በመጠን በተመሳሳይ የትርጉም ግንኙነት በ (35.48%) አንሰው መገኘታቸውና በመልመጃ አቀራረብ ስርጭታቸውም በምንባብ ስምንት፣ መልመጃ ሁለት ጥያቄ "ሠ" መሠረት (50%) የሚሆነው የጥያቄ ክፍላቸው ከተመሳሳይ ጋር በአንድነት በመቅረብ በአምስት ጥያቄዎች አንድ አይነት የቃላት ምሳሌዎችን መጋራታቸውንና በምዕራፍ ሁለት በቀረብናቸው ክለሳ ድርሳናት ከተዘረዘሩት የማስተማሪያ ደካማ ጎኖቻቸው አንፃር ተመጣጣኝ ትኩረት እግኝተዋል ማለት ያስቸግራል፡፡

2. ከቃላት አጠቃቀም ገፅታ አንፃር "የመማሪያ መፅሐፉ የቃላት መልመጃዎች የመቀበያ (Receptive) ፣ የማስተላለፊያ (Productive) ክሒሎችና የእውቀት ዘርፎች አቀናጅ ሚና በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አባሪ "ረ" ጥያቄ 1.2 የመፈተሻ ዝርዝር ክፍል አሰሳው የቃላት አጠቃቀምን እንዲያካትት ለማድረግ ተሞክሯል?" በሚለው መሪ ጥያቄ ሥር በቀረቡት ንዑሳን ጥያቄዎች ሲመረመር ሁኔታው ከሞላ ጎደል የሚከተለውን ይመስላል. የቃላት አጠቃቀም ስሙ እንደሚያመለክተው ሊያተኩር የሚገባው በቃላት ግልጋሎታዊ ገፅታ ላይ ቢሆንም በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የታየው ሁኔታ ግን በሰንጠረዥ 2 (76.64%) የመፅሐፍ ትንተናው ውጤት ምስክርነት መሠረት አተናተን መብለጡን

የሚያመለክት ነው፡፡ ተማሪዎች ግላዊ ስብዕናን ከመገንባት አኳያ በተገቢ የዲስኩር ሞዴልነት ማንነታቸውን እንዲያጎለብቱና ከቃላት አጠቃቀም ገደብ አኳያ የቃላትን እርጅና /ዘመናዊነት/፣ መልክአ ምድራዊ፣ ማህበራዊ፣ የንግግር መግባቢያ መስክ (field of discourse) እና የቃላት አብሮነቶችን በመለየት የቋንቋው ተጠቃሚዎች የሚሆኑባቸው የመማሪያ ስልቶች በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ሊካተቱ ቢገባም ከላይ የጠቀስናቸውን የቃላት አጠቃቀም ባህሪያት የሚያካትቱት የመደበኛ፣ የኢ-መደበኛ፣ የሞያ ነክ፣ የቃላት አብሮነትና የምስያ ይዘቶች በመልመጃዎቹ ጥያቄዎች አለመወከል የአሰሳው ቴክኒክ በዚህ በኩል አለመሟላቱን የሚያመለክት ነው፡፡

በተጨማሪም በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ክለሳ ድርሳናት 2.3 የተጠቀሱትን የኢትዮጵያ ተማሪዎችንና የአንዳንድ ደራሲያንን የቃላት ችሎታ ድክመት አስመልክቶ በምሁራን ከተሰጠው ጥቆማ አንፃር አብዛኛው የስህተት አይነት የቃላት አጠቃቀም ሆኖ መታየቱ በዚህ በኩል መማሪያ መፅሐፉ የሚጠበቅበትን ላቅ ያለ ሚና አለመጫወቱ የመማሪያ መጽሐፉን የቃላት ብቃት ችግር በበለጠ የሚያጎላ ነው፡፡

3. ከቃላት ምስረታ አንፃር በሠንጠረዡ እንደሚታየው በመማሪያ መጽሀፉ ለቅጠላና ለጥመራ ምንም ትኩረት አለመሰጠቱ የቃላት ማእድንን እንደአስፈላጊነቱ በእርባታ ህጎች አማካኝነት በማውጣት በጽሁፍ መዝገበ ቃላት ያልሰፈሩትን ከአእምሮ መዝገበ ቃላት ( Mental lexicon) በማውጣት የመጠቀም ችሎታ እንዳይዳብር የሚገድብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ትኩረት የተሰጠው ሆሄያትና ድምጾች የሚለው የይዘት አይነትም ቢሆን ስርጭቱ ከጠቅላላው ሲታይ የጥያቄ ብዛቱ 4 (4.08%) ብቻ በመሆኑ፣ ይህም ቢሆን ያተኮረው በአተናተን (100%) እንጅ በአጠቃቀም ላይ ባለመሆኑና በአንድ የመልመጃ አቢይ ጥያቄ ስር በተካተቱ 4 የማጥበቅና የማላላት ስነ ልሳናዊ ጥያቄ ላይ ብቻ በማተኮሩ የቃላትን የክሂልና የእውቀት ዘርፍ አቀናጅነት የተማሪዎች ችሎታ ከፍ ማድረግም ሆነ የቃላትን ሁለንተናዊ ገጽታ በተማሪዎች የባህሪ ለውጥ ላይ እንዲታይ የማድረግ ድርሻው ሊጎላ የቻለ አይመስልም፡፡

4. ሠንጠረዡ እንደሚያመለክተው የመማሪያ መጽሀፉ የቃላት መልመጃዎች የቃላት ሰዋሰው ስርጭት አብዛኛውን የቃላት አሰሳ ይዘት ባካተተ መልክ የተከናወነ ቢሆንም የስርጭት መጠኑ መለያየት የሰፋ በመሆኑ አሰሳውን የተሟላ ያደርገዋል ብሎ መደምደም የሚያስቸግር ይመስላል፡፡ ለዚህም ከሠንጠረዡ የሚጠቀሱት ምሣሌዎች በቀጣይ ምዕላድ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎች የጥያቄ ብዛታቸው 7 በመሆኑ (53.85%) የውክልና ደረጃን ሲያገኙ አሉታንና ጊዜን የመሣሉት በአንዳንድ ጥያቄ ብቻ በመወከላቸው ከቅጥያ ምዕላድ የመማሪያ መጽሐፉ ጥያቄዎች ስርጭት በ (7.69%) ብቻ ሊወሰኑ ችለዋል፡፡

ለማጠቃለል፣ መግለጫው እንደሚያመለክተው ከቀረቡት የአሰሳ ዘርፎች መካከል ከፍተኛ ድርሻ የተሰጠው የቃላት ትርጉም ዘርፍ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የቃላት ሰዋሰው ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የቃላት አጠቃቀም ዘርፍ የሚከተል ሲሆን ዝቅተኛውን የትኩረት ደረጃ በማግኘት መጨረሻ የሆነው የቃላት ምስረታ ዘርፍ ነው፡፡

ከዚህ ሠንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው ከ ተ.ቁ. 1-4 የቀረቡት የአሰሳ ዝርዝር ይዘቶች የመጨረሻዎቹ ንዑሳን ክፍሎች ለምሳሌ፣ ከትርጉም ዝምድና እንደ ተመሳሳይና ተቃራኒ ያሉት ለየብቻ ሳይቆጠሩ በድምሩ 17 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ የትርጉም ዘርፍ አራቱን የቃላት አጠቃቀም ስምንቱን፣ የቃላት ምስረታ ሦስቱንና የሰዋሰው ዘርፍ ሁለቱን በማካተት በይዘት ብዛት መበላለጥ ይታይባቸዋል፡፡

ይዘቶቹ በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ውስጥ ያላቸው ስርጭት ሲመረመር ግን የቃላት ትርጉም ዘርፍ በአምስቱ የአሰሳ ይዘቶች 48 (48.98%) የቃላት ሰዋሰው ዘርፍ 26 (26.53%) ፣ የቃላት አጠቃቀም ዘርፍ 20 (20.41%) እና የቃላት ምስረታ ዘርፍ 4 (4.08%) ለቃላት መልመጃ ጥያቄዎች መሠረት መሆናቸው የስርጭቱን አለመመጣጠን ያመለክታል፡፡ ከቃላት አጠቃቀም ስምንት የአሰሳ ይዘቶች መሀል አምስቱ፣ ከምስረታ ሦስት የአሰሳ ይዘቶች መሀል ሁለቱና ከሰዋሰው በሁለት የአሰሳ ይዘቶች ስር ከተካተቱት ንዑሳን ይዘቶች መሀል አምስቱ የቃላት መልመጃዎች እንዲዘጋጅላቸው አለመደረጉ ከፍተኛ ትኩረት ከአገኘው ከቃላት ትርጉም ዘርፍ አንድ የአሰሳ ንዑስ ይዘት ብቻ ትኩረት አለማግኘት ጋር ሲወዳደር የስርጭቱን አድሏዊነት አጉልቶ የሚያሳይ ሊሆን ችሏል፡፡

ቃላትን መማርን በመማር እራስን ችሎ ከመንቀሳቀስ የተማሪዎች የባህሪ ገጽታ አኳያ ሲታይ ለክሂሎችና ለእውቀት ዘርፎች በቅንጅት መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱት፣

ሀ. የቃላት ውሱንና አጠቃላይ ትርጉሞችን ለያይተው በማሳየት ውስብስብ የቃላት ግንኙነቶችን የሚያሳውቁትን ተካቶዎችን ከትርጉም ዘርፍ አለማካተቱ፣

ለ. የቃላት አወቃቀርን በአጠቃቀም የሚያስለዩትን የቃላት አብሮነቶችን እና ምን? በማን? መቸ? እና የት? መባል እንዳለበት የሚያሳውቁትን መደበኛ፣ ኢ -መደበኛና ሙያ ነክ ቃላትን ከአጠቃቀም ዘርፍ አለማካተቱ፣

ሐ. ያልታዩ የስልጣኔ ክስተቶችን በመወከል የቋንቋን አዳዲስ ነገሮች፣ ሁኔታዎች፣ ድርጊቶች፣ ወ.ዘ.ተ.... የመግለፅ ባህሪ እውን ለማድረግ የሚያስችለውን የቃላት ማዕድን አወጣጥ ስልት የሚያቀዳጁትን የቅጠላና የጥመራ የአሰሳ ይዘቶች ከቃላት ምስረታ ዘርፍ አለማካተቱና፣

መ. በዐረፍተ ነገር ውስጥ የቃላትን ቦታ፣ ሙያ፣ ወዘተ... በመግለፅ የቃላትን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚያሳዩትን የአሰሳ ይዘቶች ከቃላት ሰዋሰው ዘርፍ ትኩረት እንዳያገኙ ማድረጉ የመማሪያ መጽሐፉ ሌላው ባህሪ ሆኖ ተገኝቷል:: ትኩረት የተሰጣቸውም ቢሆኑ 73ቱ (74.4%) በአተናተን እና 25ቱ (25.5%) የሚሆኑት በአጠቃቀም ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ቃላትን መማርን የሚያስተምሩ ሳይሆኑ ቃላትን በተናጠል ለማሳወቅ የሚሞክሩ ይመስላሉ::

#### 4.1.1.2. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ክንውኖች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ብቃት ከቃላዊ አተያይ አንፃር

በዚህ የምዕራፍ ንዑስ ክፍል በናሙናነት የተመረጡት የመማሪያ መጽሐፉ የቃላትና ሌሎች መልመጃዎች በተሳትፎ፣ በጥናትና በትግበራ ቃላዊ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነትን መነሻ ባደረገ የመልመጃዎች አካሄድ ላይ በመመስረት ተማሪዎች ተረድተው የመምህሩን ብቸኛ ድጋፍ ከመፈለግ ዕራስን ወደ መቻል የባህሪ ለውጥ ሽግግር ለማድረግ የሚያግዙ ክንውኖችን መያዝ አለመያዛቸውንና ንጥልጥል የፈተና (Discrete point test) ጥያቄዎችን ከማቅረብ ይልቅ ክሂሎችንና የዕውቀት ዘርፎችን በቅንጅት ለማዳበር የሚያስችል ተግባቦታዊ አካሄድን በመከተል የችግር ፈችነት ባህሪ ማካተት አለማካተታቸውን ለመመርመር ተሞክሯል:: ዋናው ትኩረት በ1984 ዓ.ም. ታትሞ የዚህ ጥናት መረጃ እስከ ተሰበሰበበት 1990 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ድረስ በተለይ በአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ነው::(ዝርዝሩን ከዚህ በታች በቀረቡት ሠንጠረዦችና ማብራሪያዎቻቸው ይመለከቷል::)

# የ1984 ዓ.ም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የክሂልና የዕውቀት ዘርፍ መልመጃዎች የጥያቄ አቀራረብ መግለጫ

| ተ.ቁ | | | የጥያቄ አቀራረብ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | የክሂልና የዕውቀት ጥያቄ አቀራረብ | | ክሂል የዕውቀት ጥያቄ ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ገለፃ | | | | | | እውነት ወይም ሐሰት | | | | | | ምርጫ | | | | | | ተግባር | | | | | |
| | | | ቀጥታ | | የግል ግንዛቤ | | ድምር | | ቀጥታ | | የግል ግንዛቤ | | ድምር | | ቀጥታ | | የግል ግንዛቤ | | ድምር | | | | | | | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | | የንግግር የማዳመጥ ክሂል | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 2 | 4.88 | - | - | 2 | 1.25 |
| | 1.1 | ምረካ | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 1 | 50 | 1 | 0.63 | - | - |
| | 1.2 | ውይይት | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 1 | 50 | 1 | 0.63 | - | - |
| | 1.3 | ክርክር | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 2 | | የንባብ ክሂል | 24 | 32.88 | 8 | 80 | 32 | 33.68 | 6 | 100 | 3 | 100 | 9 | 100 | 9 | 42.86 | 1 | 16.67 | 10 | 37.04 | - | - | - | - | 51 | 31.88 |
| | 3.1 | ርዱት(Comprehention) | 20 | 83.33 | 8 | 100 | 28 | 87.50 | 6 | 100 | 3 | 100 | 9 | 100 | 7 | 77.78 | 1 | 100 | 8 | 80 | - | - | 45 | 28.13 | | |
| | 2.2 | የቦርቃ ሐረጎች ትርጉም | 4 | 16.67 | - | - | 4 | 12.50 | - | - | - | - | - | - | 2 | 22.22 | | | 2 | 20 | - | - | 6 | 3.75 | | |
| 3 | | የጽህፈት ክሂል | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 2 | 100 | 2 | 1.25 | - | - |
| | 3.1 | ስርአት ነጥብ | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | 3.2 | ደብዳቤ መጻፍ | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | | | | | 2 | 100 | 2 | 1.25 | | |
| | 3.3 | የህይወት ታሪክ | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | 3.4 | አህጽሮተ ጽሑፍ | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 4 | | የሥነ ጽሑፍ እውቀት | 4 | 5.48 | 2 | 20 | 6 | 6.32 | - | - | - | - | - | - | - | - | 1 | 16.67 | 1 | 3.70 | - | - | - | | 7 | 4.37 |
| | 4.1 | የግጥም ትርጽ | 4 | 100 | - | - | 4 | 66.67 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 4 | 2.50 | - | - |
| | 4.2 | ምስል ፈጠራ (ዘይቤ) | - | - | 1 | 50 | 1 | 16.67 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 1 | 0.63 | - | - |
| | 4.3 | ገፀ-ባሕሪ አሳሳል | - | - | 1 | 50 | 1 | 16.67 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 1 | .063 | - | - |
| | 4.4 | ስነ ቃል (ተረትና ምሳሌ) | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 1 | 100 | 1 | 100 | - | - | 1 | 0.63 | - | - |
| 5 | | የቃላት ዕውቀት | 45 | 61.64 | - | - | 4.5 | 47.37 | | | | | | | 12 | 57.14 | 4 | 66.67 | 16 | 59.26 | 37 | 90.22 | | | 98 | 61.25 |
| | 5.1 | የቃላት ትርጉም ዕ ውቀት | 31 | 68.89 | - | - | 31 | 68.89 | | | | | | | 6 | 50 | 1 | 25 | 7 | 43.75 | 10 | 27.03 | 48 | 30 | | |
| | 5.2 | የቃላት አጠቃቀም ዕውቀት | 10 | 22.22 | - | - | 10 | 22.22 | | | | | | | 6 | 50 | 2 | 50 | 8 | 50 | 2 | 5.41 | 20 | 12.50 | | |
| | 5.3 | የቃላት ምስረታ ዕ ውቀት | 4 | 8.89 | - | - | 4 | 8.89 | | | | | | | | | | | | | | | 4 | 2.50 | | |
| | 5.4 | የቃላት ሰዋሰው ዕ ውቀት | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 1 | 25 | 1 | 6.25 | 25 | 67.57 | 26 | 16.25 | | |

በሠንጠረዥ 3 መሠረት ከፍተኛውን ቁጥር 83 (51.87%) የያዘው የገለፃ ጥያቄ አቀራረብ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 73ቱ (87.95%) በቀጥታ የጥያቄ አቀራረብና 10 (12.05%) ጥያቄዎች ደግሞ እንደቀጥታው አይነት "የሰጠሁህን አምጣ" በሚል አጠያየቅ ሳይሆን በግል ግንዛቤ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ በመቀጠልም በሁለተኛ የሚገኙት የተግባር ጥያቄዎች 41 (25.63%) ፣ በሦስተኛ ደረጃ የምርጫ ጥያቄዎች 27 (16.88%) ና በመጨረሻ ደረጃ የእውነት ወይም ሀሰት ጥያቄዎች 9 (5.63%) ናቸው፡፡ የምርጫና የእውነት ወይም ሀሰት ጥያቄዎች አቀራረብ ሲታይም በድምሩ በቀጥታ የጥያቄ አቀራረብ የቀረቡት ጥያቄዎች ብዛት 27 (16.88%) ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም ከገለጻ የቀጥታ አቀራረብ ብዛት ጋር ሲደመር ከመጽሐፉ ውስጥ በናሙናነት ከተወሰዱት 16 (100%) ጥያቄዎች 100 (62.5%) የሚሆኑትን ያካተተው የቀጥታ ጥያቄ አቀራረብ መሆኑን ከሠንጠረዡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የቀሩት 6 (37.5%) ጥያቄዎችም በተግባር 41 (25.63%) እና በገለፃ፣ በእውነት ወይም ሀሰትና በምርጫ የግል ግንዛቤ አጠያየቅ ደረጃ 19 (11.87%) ጥያቄዎችን ስለሚያካትቱ የመጽሐፉ ናሙና መልመጃዎች ጥያቄ አቀራረብ በአብዛኛው በገለፃ የጥያቄ አይነት ከመዘጋጀቱ ባሻገር የአጠያየቅ ደረጃውም በአመዛኙ በቀጥታ አጠያየቅ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የአቀራረብ ስልቱን ከክሂሎችና ከዕውቀት ዘርፎች ቅንጅትና ስርጭት አንፃር ስንመለከተው አራቱን ክሂሎች ለማስተማር የቀረቡት የናሙና መልመጃዎቹ ጥያቄዎች ከመጽሐፉ በቀጥታ በተወሰዱበት መልኩ ሲታዩ ቁጥራቸው በድምሩ 55 (34.38%) ሲሆን የዕ ውቀት ዘርፎች በድምሩ 105 (65.18%) በመሆናቸው መማሪያ መጽሐፉ ከክሂሎች ይበልጥ ለዕውቀት ዘርፎች ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱን እንረዳለን፡፡ ከክሂላዊ ጥያቄዎች መሀል 32 (58.18%) የሚሆኑት በገለፃ የጥያቄ አይነት በ 1ኛ ደረጃ፣ 9 (16.36%) የሚሆኑት በምርጫ አይነት በ 2ኛ ደረጃ፣ 4 (7.27%) የሚሆኑት በእውነት ወይም ሀሰት አይነት በ 3ኛ ደረጃ ና 10 (18.18%) የሚሆኑት ጥያቄዎች በተግባር በ 4ኛ ደረጃ የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ክሂሎቹ አብዛኛው በገለፃ የጥያቄ አይነት ላይ በማተኮራቸው ክሂላዊ የቋንቋ ተግባራት የተግባቦት አላማ መሠረትን የዘነጉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በገለፃ፣ በምርጫና በእውነት ወይም ሀሰት ከቀረቡትም መሀል 39 (70.99%) የሚሆኑት ክሂላዊ ጥያቄዎች በቀጥታ አጠያየቅ ላይ በመመስረቻውና ለግል ግንዛቤ የሰጡት ትኩረት 12 (29.01%) ብቻ በመሆኑ ተማሪዎች መረጃ ሰብሳቢዎች እንጂ ተርጓሚዎችና የመረጃው ውጤት ተጠቃሚዎች እንዳይሆኑ የመግታት አዝማሚያው ጎላ ብሎ ታይቷል፡፡ ተግባራዊ ክሂሉም ቢሆን በአብዛኛው የማስተላለፊያዎቹን ክሂሎች (Productive skills) እንጂ የመቀበያዎቹን ክሂሎች (Receptive skills)ን ባለማካተቱ በመጠን ማነሱ ብቻ ሳይሆን በክሂላዊ ተዋጽኦውም ችግር ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተለይ የንባብ ክሂልን ባለማካተቱና የማዳመጥ ክሂልንም ቢሆን ከንግግር ጋር በማዳበል

በተዘዋዋሪ እንጂ በቀጥታ ባለማካተቱ በመቀበያና በማስተላለፊያ ክሂሎች መሀል ሊኖር የሚገባውን የመረጃ አጠቃቀም ግንኙነት አዛብቷል፡፡

ይህም ማለት ከንባብና ከማዳመጥ የተገኙት መረጃዎች ለንግግርና ለጽህፈት ክሂሎች ማዳበሪያ ምንጭ እንዲሆኑ ተደርገው ተደጋጋፊነትን የሚያጠናክሩ ክሂላዊ ጥያቄዎች ቢዘጋጁላቸው ኖሮ የክሂሎቹ ቅንጅት የተዋጣለት ሊሆን ይችል እንደነበረ ለማስታወስ ነው፡፡

ከሰንጠረዥ 3 ጠቅላላ ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለውም የናሙና ጥያቄዎቹ እጅግ አንሰው መገኘት፣ በገለፃ የቀረቡትም ቢሆኑ በአብዛኛው በቀጥታ አጠያየቅ ላይ ማተኮራቸው፣ ለግል ግንዛቤ ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት፣ ከሁሉም ክሂሎች ይበልጥ ለንባብ ማድላት 51 (92.72%) የሚሆኑ ጥያቄዎች እንዲካተቱ ከማድረግ በተጨማሪ በመቀበያዎቹና በማስተላለፊያዎቹ መሀል ያለው የመረጃ መጋራት ግንኙነት አንሶ መገኘትና ከዚሁም አኳያ ለማዳመጥ ክሂል የተሰጠው ትኩረት "ተወያዩበት" በሚለው ከአንድ የመልመጃ ጥያቄ በመነሳት "መወያየት የማዳመጥና የመናገርን ክሂል በጋራ ያዳብራል" በሚል አንድምታ በተዘዋዋሪ በዚህ ጥናት ነጥብ ተሰጠው እንጂ በቀጥታ የማዳመጥ ክሂልን የሚመለከቱ ሆነ ተብለው የተዘጋጁ ጥያቄዎች ባለመኖራቸው የመማሪያ መፅሐፉ ክሂል ነክ ጥያቄዎች በበርካታ አጥኚዎች የተጠቀሱትን የሀገሪቱን ተማሪዎች የክሂል ችሎታ ማነስ ችግር በሚቀርፍበት መልክ ተዘጋጅተው የቀረቡ ናቸው ለማለት የሚያስደፍር እውነታን አያሳይም፡፡

ይኸው ሰንጠረዥ 3 እንደሚያመለክተው ለእውቀት ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት ተለይቶ ይታወቅ ዘንድ ስነ-ጽሁፍ በ 7 (4.37%) እና የቃላት እውቀት በ 98 (61.25%) ጥያቄዎች ከጠቅላላው የናሙና መልመጃዎቹ ጥያቄዎች መሀል በድምሩ በ 68 (65.62%) ጥያቄዎች በመወከላቸው ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ከክሂሎች ይልቅ ለእውቀት ዘርፎች መሆኑን ቢያመለክትም ለእውቀት ዘርፎች ከተሰጠው የ 105 (100%) ትኩረት መሀል የቃላት እውቀት በ 98 (93.33) ና ስነ-ጽሁፍ በ 7 (6.66%) የጥያቄ ድርሻ በመወከላቸው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኘው የእውቀት ዘርፍ አይነት በከፍተኛ ደረጃ የቃላት እውቀት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ይኸው የቃላት እውቀት ከተቀሩት የክሂልና የእውቀት ዘርፎች አንፃር ሲታይ በ (61.25%) መወከሉ ከሌሎች የቋንቋ ገጽታዎች ይበልጥ የመጽሀፉ ከፍተኛ ትኩረት በቃላት ትምህርት ላይ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ይህ ጥናት መማሪያ መጽሀፉ ላቅ ያለ ትኩረት በሰጠውና ሌሎች የሀገራችን ተመራማሪዎች ከአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ጋር በተያያዘ እስከአሁን ሰፊ ትኩረት ባልሰጡት በቃላት ትምህርት ላይ ማተኮሩ ተገቢነት ያለው መሆኑን በተዘዋዋሪ የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በመጽሀፉ ውስጥ ከቃላት ዘርፎች ውጭ ስነ -ልሳናዊ፣ የስነ-አገባባዊም ሆነ ሌላ ጉዳይ በመጽሀፉ መግቢያ በአጠቃላይ አላማነት እንደተጠቀሰው አለመካተቱ ቃላቱ በጥያቄነት የቀረቡት በአብዛኛው ስነ -ልሳናዊ የትምህርት

አላማዎችን ከግብ ለማድረስ እንጅ በቃላዊ አተያይ ተግባቦታዊ አላማን ግብ ለማስመታት እንዳልሆነ የትምህርቱ አቀራረብም ቃላትን መማርን በመማር ዘዴ፣ ቴክኒክና ስልት ላይ አለመመስረቱን የሚጠቁም ነው፡፡

ዘርፍ

| ድምር | | የመልስ አይነት | | | | | | የቋንቋ ገጽታ ትኩረት | | | | | | የክሂልና (የዕውቀት ዘርፍ) ጥያቄ አቀራረብ ባህሪ | | የክሂል(ዕውቀት ዘርፍ) ጥያቄ ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አጫጭር | | ረጃጅም | | ድምር | | አተናተን | | አጠቃቀም | | ድምር | | | | | |
| ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| . | . | . | . | 2 | 50 | 2 | 1.25 | . | . | 2 | 50 | 2 | 1.25 | . | . | 2 | 1.25 |
| . | . | . | . | 1 | 50 | . | 50 | . | . | 1 | 50 | 1 | 50 | 1 | 0.63 | | |
| . | . | . | . | 1 | 50 | . | 50 | . | . | 1 | 50 | 1 | 50 | 1 | 0.63 | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 51 | . | 51 | 32.69 | . | . | 51 | 31.88 | 51 | 32.69 | . | . | 51 | 31.88 | . | . | 51 | 31.88 |
| 45 | 88.24 | 45 | 88.24 | . | . | 45 | 88.24 | 45 | 88.24 | . | . | 45 | 88.24 | 45 | 28.13 | . | . |
| 6 | 11.76 | 6 | 11.76 | . | . | 6 | 11.76 | 6 | 11.76 | . | . | 6 | 11.76 | 6 | 3.75 | . | . |
| . | . | . | . | 2 | 50 | 2 | 1.25 | . | . | 2 | 50 | 2 | 1.25 | . | . | 2 | 1.25 |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| . | . | . | . | 2 | 100 | 2 | 100 | . | . | 2 | 100 | 2 | 100 | 2 | 1.25 | . | . |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | . | 7 | 4.49 | . | . | 7 | 4.38 | 7 | 4.49 | . | . | 7 | 4.38 | . | . | 7 | 4.37 |
| 4 | 57.14 | 4 | 57.14 | . | . | 4 | 57.14 | 4 | 57.14 | . | . | 4 | 57.14 | 4 | 2.50 | . | . |
| 1 | 14.29 | 1 | 14.29 | . | . | 1 | 14.29 | 1 | 14.29 | . | . | 1 | 14.29 | 1 | 0.63 | . | . |
| 1 | 14.29 | 1 | 14.29 | . | . | 1 | 14.29 | 1 | 14.29 | . | . | 1 | 14.29 | 1 | 0.63 | . | . |
| 1 | 14.29 | 1 | 14.29 | . | . | 1 | 14.29 | 1 | 14.29 | . | . | 1 | 14.29 | 1 | 0.63 | . | . |
| 98 | 62.82 | 98 | 62.82 | . | . | 98 | 61.25 | 98 | 62.82 | . | . | 98 | 61.25 | . | . | 98 | 61.25 |
| 48 | 48.98 | 48 | 48.98 | . | . | 48 | 48.98 | 48 | 48.98 | . | . | 48 | 48.98 | 48 | 30 | . | . |
| 20 | 20.41 | 20 | 20.41 | . | . | 20 | 20.41 | 20 | 20.41 | . | . | 20 | 20.41 | 20 | 12.50 | . | . |
| 4 | 4.08 | 4 | 4.08 | . | . | 4 | 4.08 | 4 | 4.08 | . | . | 4 | 4.08 | 4 | 2.50 | . | . |
| 26 | 26.53 | 26 | 26.53 | . | . | 26 | 26.53 | 26 | 26.53 | . | . | 26 | 26.53 | 26 | 1625 | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 151 | | 156 | 97.50 | 4 | 2.50 | 160 | 100 | 156 | | 4 | | 160 | 100 | 160 | | 160 | 100 |

በሰንጠረዥ 4 እንደሚታየው በ 1984 ዓ.ም. ዕትም የመረጃ ማሰባሠቢያ ዋና መሣሪያ ንባብ (81.87%) ሲሆን (18.12%) የሚሆነው ደግሞ ያልታወቀ በመሆኑ የተሰጠውን ድርሻ ከፍተኛነት ያመለክታል፡፡ የመልስ ማቅረቢያ መንገዱም በጽሑፍ ይቅረብ በቃል ተለይቶ አለመታወቁ በ (94.37%) መገለፁ ከ (97.5%) በአጫጭር መልሶች የመልመጃዎቹ ጥያቄዎች መመለስ እውነታ ጋር ተደምሮ የመልመጃዎቹን ክሂላዊ አለመሆን በጥቅሉ ሲያስገነዝበን ከመልመጃዎቹ ጥያቄዎች (97.5%) የሚሆኑት ከአጠቃቀም ይልቅ በትንተና ላይ ማተኮራቸው የጥያቄዎቹን በዕውቀት ሰጪነት አላማ ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት የሚያመለክት ነው፡፡

ሁኔታው ከተሳትፎና ትግበራ ክሂላዊ ክንውኖች አንፃር ሲታይ ተሳትፎውም ሆነ ትግበራ ተራክቦአዊ ውይይትን፣ መጠይቆችን፣ በጋራ መሙላትን፣ቃለ-ምልልስ ማዘጋጀትና በተግባር መሳተፍን፣ ታሪክ መናገርን፣ ደብዳቤዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ ወዘተ... መፃፍንና የመሣሠሉትን ረጃጅም የተሳትፎ መልሶች የማያካትቱ እንጂ የአጫጭር መልሶችን ዝርዝር የሚያመለክቱ ባለመሆናቸው የመማሪያ መፅሐፉ ትኩረት በተሳትፎና በትግበራ የጥያቄዎች አቀራረብና የመልሶች አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ጉዳዩ በሠንጠረዥ 3 ከተገለፀው ለማስተላለፊያ ክሂሎች ከተሰጠው (2.5%) ብቻ የክሂሎች ትኩረት ጋር ሲገናዘቡ ከላይ የጠቀስናቸው የተሳትፎም ሆነ የትግበራ ክንውኖች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በየትኛውም ዓይነት መንገድ ይኖራሉ ብሎ ማስረዳት እንደማይቻል የሚጠቁም ነው፡፡

የዕውቀት ዘርፎቹም ትኩረት ሲመረመር ለስነጽሑፍ የተሰጠው ትኩረት (6.66%) ብቻ መሆኑና ለቃላት ዕውቀት የተሰጠው በአንፃሩ(93.33%) መድረሱ በድምሩ ከጠቅላላው የጥያቄ ብዛት ጋር ሲወዳደር በተለይ ማስተላለፊያ ክሂልንም ሆነ መቀበያ ክሂሎችን የማዳበር አቅም ሊኖረው ይገባው የነበረው የስነ ጽሑፍ ዕውቀት ዘርፍ በ(4.37%) ብቻ መወሰኑ፣ ይኸው ቁጥርም ቢሆን አጫጭር መልስ በሚያስገኙ ጥያቄዎች ላይ ብቻ ከመመስረቱ ጋር ተዳምሮ የዕ ውቀት ዘርፍ ትኩረት በተሳትፎና ትግበራ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ለዕርማት ፍጥነት በሚያመቹ አጭር መልስ ፈላጊ ዝርዝር ዕውቀት ጥያቄዎች (Discrete point test) ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ በጥቅሉ ከዕውቀት ዘርፎቹ (93.33%) የሚሆኑት የስነ-ልሣን ዕውቀትን ለማስተላለፍና (6.66%) የሚሆኑት የስነ-ጽሑፍ ዕውቀትን ለማስጨበጥ ስለ ገፀባህሪ ምንነት፣ ስለ ተረትና ምሣሌ ትርጉምና የዘይቤ ዓይነት ዝርዝር ዕውቀት በፈተና መልክ ለመስጠት በመሞከር የፈተና ጥያቄ ዓይነቶችን ከማለማመድ ባሻገር ተግባቦትን አላማ ባደረገ የትምህርት ስርዓት ላይ ተመስርተው ስላልተዘጋጁ (65.62%) የሚሆኑት የመማሪያ መጽሐፉ ናሙና መልመጃ ጥያቄዎች "እያሰሳችሁ፣እየተሳተፋችሁ... እየተገበራችሁ ቃላትን መማርን ተማሩ" በሚል ተግባራዊ መሠረትነት የቀረቡ ናቸው ማለት የሚያዳግት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ላይ (31.88%) የሚሆኑ የንባብ ክሂል (100%) ጥያቄዎች እንደ ዕውቀት ዘርፎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ በትንተናና በአጫጭር መልሶች አሰጣጥ ክንውን ላይ መመስረት በዝርዝር

እውነታ ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩሩትንና ለክሂል መዳበር በመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያ በኩልም ሆነ በማቅረቢያ መንገድ ክሂሎችን በተቀናጀ መልክ የሚያዳብሩትን ጥያቄዎች ብዛት ወደ (97.5%) ስለሚያሳድገው የመማሪያ መጽሐፉ ናሙና መልመጃ ጥያቄዎች ትኩረት ከተሳትፎና ከትግበራ ክንውን ይልቅ ለዝርዝር ዕውቀት ፈተና ልምምድ በአደላ ዝግጅት ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው፡፡

ሠንጠረዥ 5

የ1984 ዓ.ም. ዕትም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ናሙና ጥያቄዎ በየምድብ ክሂላቸው፣ የዕውቀት ዘርፋቸው፣ ምንባባቸው፣ መልመጃና ጥያቄ ቁጥራቸው አመልካች ሠንጠረዥ

| ክሂል | ርዕስ | የምንባብ፣ የመለመጃዎችና ጥያቄ ኮድ ቁጥር |
|---|---|---|
| የንግግርና ማዳመጥ | ትረካ | 12.3.2 |
| | ውይይት | 16.3.3 |
| | ክርክር | - |
| ንባብ ክሂል | ርዴት በቀጥታ በገለፃ የሚመለሱ | 4.1.1.ሀ 4.1.1ለ 4.1.1ሐ 4.1.1.መ 4.1.1ሠ 8.1.1ሀ 8.1.1.ለ 8.1.1ሐ 8.1.1መ 8.1.1ሠ 8.1.1ረ 8.1.1ሰ 12.1.1ሀ 12.1.1ለ 12.1.1ሐ 12.1.1መ 12.1.1ሠ 16.1.1ሀ 16.1.1ለ 16.1.1ሐ |
| | ርዴት በግል ግንዛቤ በገለፃ የሚመልሱ | 4.1.1.ረ 8.3.1. 8.3.2. 8.3.3. 12.3.1. 16.1.1.መ 16.3.1 |
| | ርዴት በእውነት (ሀሰት) በቀጥታ የሚመለሱ | 8.1.2.ሀ. 8.1.2.ለ. 8.1.2.ሐ. 8.1.2.መ 8.1.2.ሠ 8.1.2.ረ |
| | ርዴት በእውነት ሀሰት በግል ግንዛቤ የሚመለሱ | 4.1.2.ሀ 4.1.2.ለ 4.1.2.ሐ |
| | ርዴት በምርጫ የጥያቄ ዓይነት በቀጥታ የሚመለሱ | 4.1.3.ሀ 4.1.3.ለ 4.1.3.ሐ 12.1.2.ለ 12.1.2.መ |
| | ርዴት በምርጫ የጥያቄ ዓይነት በግል ግንዛቤ የሚመለሱ | 4.1.3 ሠ 12.1.2. ሀ |

| ክሂል | ርዕስ | የምንባብ፣ የመለመጃዎችና ጥያቄ ኮድ ቁጥር |
|---|---|---|
| | የዝርው ሀረጎች ትርጉም | 4.2.3(2) 4.2.3.(3) 4.2.3(6) 16.2.1ለ 16.2.1.(ሐ) 12.2.1.ሠ |
| ጽህፈት | ስርዓተ-ነጥብ | |
| | ደብዳቤ መፃፍ | 4.3.1. 4.3.2 |
| | የህይወት ታሪክ | |
| | አህጽሮተ ጽሑፍ | |
| የስነ ጽሑፍ ዕውቀት | የግጥም ቅርፅ | 12.2.3.ሀ 12.2.3.ለ 12.2.3 ሐ 12.2.3መ |
| | ምስል ፈጠራ (ዘይቤ) | 12.1.2 ሐ |
| | ገፀ ባሕሪ አሳሳል | 16.3.2 |
| | ስነ ቃል (ተረትና ምሳሌ) | 12.2.6 |
| ስነ ልሣን | አውዳዊ ቃላት ትርጉም | 8.2.1ሀ 8.2.1.ለ 8.2.1.መ 16.2.2.ሀ 16.2.2.ለ 16.2.2.ሐ 16.2.2.መ |
| | የቃላት ትርጉም ዝምድና (ተመሣሣይ) | 4.2.2(1) 4.2.2(2) 4.2.2(3) 4.2.2(4) 4.2.2(5) 8.2.1ሠ1 8.2.1ሠ2 8.2.1ሠ3 8.2.1ሠ4 8.2.1ሠ5 8.2.1ቀ1 8.2.1ቀ2 8.2.1ቀ3 8.2.1ቀ3 8.2.1ቀ4 8.2.1ቀ5 8.2.1ቀ6 8.2.1ቀ6 8.2.1ቀ7 12.2.1ሀ 12.2.1ለ 12.2.1ሐ 12.2.1መ |
| | የቃላት ትርጉም ዝምድና (ተቃራኒ) | 12.2.2ሀ 12.2.2ለ 12.2.2ሐ 12.2.2መ 12.2.2ሠ 8.2.1ሠ1 8.2.1ሠ2 8.2.1ሠ3 8.2.1ሠ4 8.2.1ሠ5 |
| | ድርብርብ የቃላት ትርጉም ውክልና | 8.2.1ሰ1 8.2.1ሰ2. 8.2.1.ሰ3 8.2.1ሰ4 8.2.1.ሰ58.2.1.ሰ6 |
| | የመዝገኘ ቃላዊ የቃላት ትርጉም | 8.2.1ሸ(ለ) 8.2.1.ሸ(መ) 8.2.1.ሸ(ሠ) 16.2.1 መ |
| | ተለዋጮች | 4.2.3(1) 4.2.3(4) 4.2.3(5) 4.2.5.በ(5) 8.2.1.ሸ(ሀ)8.2.1ሸ(ሐ) 8.2.1.ሸ(ረ) 8.2.1 በ(1) 8.2.1በ(2) 8.2.1.በ(3) 8.3.4. 16.2.1ሀ 16.2.2ሰ |

| ክሂል | ርዕስ | የምንባብ፣ የመለመጃዎችና ጥያቄ ኮድ ቁጥር |
|---|---|---|
| | ፊሊጦች | 8.1.3ሀ 8.2.1ሐ 8.2.1ሽ(ሰ) 8.2.1በ 12.2.1ሠ16.2.2.ረ |
| | ተረትና ምሳሌ ከቃላት -አጠቃቀም አንፃር | 8.3.5 |
| | ሆሄያት ድምፁች | 8.2.1ረ(1) 8.2.1ረ(2) 8.2.1ረ(3) 8.2.4ረ(4) |
| | የስም ገላጮች (ቅፅል) | 16.2.5ሀ 16.2.5ለ 16.2.5 ሐ 16.2.5መ 16.2.5ሠ |
| | የግስ ገላጮች (ተውሳከ ግስ) | 16.2.4ሀ 16.2.5ለ 16.2.5ሐ 16.2.5.መ 16.2.5ሠ |
| | መስተዋድዶች | 16.2.3ሀ 16.2.3ለ 16.2.3ሐ |
| | ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎች | 4.2.4(1) 4.2.4(5) 4.2.4(6) 4.2.4(7) 4.2.4(8) 4.2.4(9) 4.2.4(10) |
| | ጊዜ አመልካች ቅጥያዎች | 4.2.4(11) |
| | አሉታን አመልካች ቅጥያዎች | 4.2.4(12) |
| | ባለቤትነትን አመልካች ቅጥያዎች | 4.2.4.(2) 4.2.4(3) 4.2.4(4) 8.1.3ለ |
| | ቃላት በዐ.ነገር ዓይነቶች ውስጥ | |
| | ድብልቅ ይዘቶች | |
| | ያልተለመዱ ሀረጎች | |

በዚህ ሠንጠረዥ ክፍል የተዘረዘሩት የክሂልና የዕውቀት ዘርፍ ርዕሶች በጥናቱ ውስጥ ከሠንጠረዥ 2 እስከ ሠንጠረዥ 5 የተጠቀምንባቸው ሲሆኑ በየርዕሱ ጎን የዘረዘርናቸው ኮድ ቁጥሮችም እያንዳንዱ ርዕስ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በስንተኛው ምንባብ፣ መልመጃ ና ጥያቄ እንደሚገኝ የሚጠቁም ነው፡፡ በመሆኑም የኮድ ቁጥሩ አቀማመጥ ከግራ ወደ ቀኝ ሲተረጎም በመጀመሪያ የምናገኘው የምንባብ ቁጥሩን፣ ቀጥሎ ከነጥብ በኋላ (በመሀል) የምናገኘውን የመልመጃ ቁጥሩንና በስተመጨረሻ (በስተቀኝ) የምናገኘው የጥያቄ ቁጥሩን ይጠቁማሉ፡፡ ይህንንም በሚከተለው ምሣሌ መመልከት ይቻላል፡፡

ምሣሌ ኮድ ቁጥር

4.2.1

↙ ↓ ↘

ምንባብ መልመጃ ጥያቄ

የመጽሐፉ ጥያቄዎች ከተሳትፎ ክንውኖች አንፃር ሲመረመሩ በየትምህርት ርዕሱ ውስጥ በመነሻነት የሚገኙት መልመጃዎች አንብቦ መረዳትን የሚፈልጉ አጫጭር መልሶችን የያዙ ጥያቄዎች እንጂ ስለ ጉዳዩ የቃላት ዕውቀትን ለማዳበር የሚገፋፉ አወያይ ጥያቄዎች ባለመሆናቸው ለተሳትፎ ክንውን ታስበው የተዘጋጁ ሆነው አይታዩም፡፡

በሠንጠረዡ እንደሚታየው ተራክቦአዊ ውይይትን የሚጋብዝ ጥያቄ ምንባብ 16፣ መልመጃ 3፣ ጥያቄ 3 ብቻ ሲሆን ይህም ለተሳትፎ ክንውን ታስቦ የተዘጋጀ አለመሆኑን የሚያመለክተው በስተመነሻ መልመጃ አንድ ላይ መገኘት ሲኖርበት በመልመጃ ሦስት ሦስተኛ ጥያቄ ላይ በስተመጨረሻ መገኘቱ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር የሚታየው ጉዳይ የመልመጃ አንድ ጥያቄዎችም ሆኑ ሌሎች ጥያቄዎችን በመመለስ አለዚያም በተሰጠ ምሣሌ መሠረት ነገሮችን መለየትን እንጂ የተማሪዎችን ስሜትና ፍላጎት ሊያነሳሱ የሚችሉ፣ ከግል ሕይወት ጋር የተገናኙና የግል አስተያየትን ወይም ልምድና ገጠመኝን የሚጠይቁ ስሜት ቀስቃሽ ጥያቄዎችን ስለማያካትቱ የተስትፎ ክንውኖች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ ማለት ያስቸግራል፡፡ ከራሳቸው ከምንባቦቹ ርዕሶች ስንነሳ "ደብዳቤ" የሚለውን ብንወስድ ተማሪዎች እስካሁን በግል ከተቀበሏቸውና ለሌሌሎችም ከፃፏቸው የትኞቹ የደብዳቤ መፃፍ ፍቅር እንዳሳደሩባቸው እና ደብዳቤ ጥሩ የመገናኛ መሣሪያ ስለሆነባቸው ምክኒያቶች ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር አያይዘው የሚገልፁባቸው ጥያቄዎች ቢካተቱባቸው ጥሩ የተሳትፎ ክንውኖች ሊሆኑ እንደሚችሉ ከነ ሀርመር (1991) መግቢያ የተገኘው ማስረጃ ይጠቁማል፡፡ ናሙና መልመጃዎቹ ይህን ለማሟላት ባለመሞከራቸው የተማሪዎችን ፍላጎት እያነሳሱ ያሳትፋሉ ማለት አያስደፍርም፡፡

በተጨማሪም በሠንጠረዡ የሚታዩት የናሙናው መልመጃ ጥያቄዎች በአብዛኛው በዝርዝር እውነታ ላይ ለተመሠረቱ ጥያቄዎች ተማሪዎች አጫጭር መልስ እንዲሰጡ ያደርጋሉ እንጂ ሚናን ለመጫወት የሚያስችሉ የቃለ ምልልስም ሆነ የተውኔት መልክ ያላቸው የምንባብ ክፍሎችን ባለመያዛቸው በጥናት ክንውን ከመቀበያ ወደ ማስተላለፊያ የቃላት ክሂላዊ ደረጃነት እንዲለወጡ የሚያደርግ ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ ይህም ከቃላት የክሂልና የእውቀት ዘርፍ አቀናጅነት ሚና አንፃር ሲታይ የቃላት ጥያቄዎቹ በተሳትፎ ክንውን መሠረትነት በጥናት ክንውን አልፈው ወደ ትግበራ የመለወጣቸውን ሁኔታ በድርጊት ስለማያመለክትና በመልመጃዎቹም ቢሆን በአንድም ቦታ እንኳ ከዚህ መልመጃ በአገኛችኋቸው ቃላት እንዲህ ያለ ጉዳይ ፃፉ (ተናገሩ) የሚል ጥያቄ ስለማይገኝ የመልመጃዎቹ አመሠራረት ከተሳትፎ ክንውን በመጀመር የሚያድግ ነው ማለት የሚቻል አይሆንም፡፡

ከፍተኛውን ትኩረት ያገኘው ትርጉም መፈለግም ቢሆን (44.89%) የሚሆኑት ጥያቄዎች የተዘጋጁት " እንዲህ ማለት ምን ማለት ነው? ተመሳሳይ ስጥ? ተቃራኒያቸውን ስጥ?" በሚል አይነት እንጂ ጥያቄዎችን ወደ ግል ሕይወት በመማምጣት ለምሣሌ አዳዲስ የስሜት መግለጫ ቃላትን ደርድሮ " ይህ አይነቱ ስሜት የሚሰማችሁ መቼ ነው?" እያሉ በመጠየቅና ተመሣሣይ ባህሪ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ አውጡ በሚል አይነት የቃላትን ትርጉም በአሰሳ በማሳወቅ ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ የጥናት ክንውኑ በዚህ በኩልም ቢሆን አለመሟላቱን የሚጠቁም ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ለትንተና ያመች ዘንድ ከሠንጠረዥ 2 እስከ ሠንጠረዥ 15 ባሉት ሠንጠረዦች አቀማመጥ ቅደም ተከተልና መመሳሰል መሠረት ተሳትፎንና ትግበራን በማስቀደም የጥናት ክንውንን በስተመጨረሻ አደርገን እንጂ በጥናቱ መስፈርት ("እያሰሳችሁ፣ እየተሳተፋችሁ፣ እያጠናችሁና እየተገበራችሁ ቃላትን መማርን ተማሩ") መሠረት አሰሳ መጀመሪያ፣ ተሳትፎ በሁለተኛ ደረጃ፣ ጥናት በሦስተኛ ደረጃና ትግበራ በአራተኛ ደረጃ የሚመጡ ከመሆናቸው አኳያ ሲታዩ የናሙና መልመጃዎቹ አቀራረብ በቃላት መልመጃዎቹ የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች አቀናጅነት ሂደት ላይ ያልተመሠረቱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

### 4.1.2. ከመምህራን መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በከፍተኛ 4፣ በአብዮት ቅርስ፣ በወንዲራድ፣ በዳግማዊ ምኒልክ፣ በጥቁር አንበሳና በአቃቂ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን የተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ አምስት ክፍሎች አሉት. ክፍል አንድ የመምህራንን የግል ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ክፍል ሁለት ደግሞ ስለ መማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ስልቶች ትኩረት የሚጠይቅ ነው፡፡ ክፍል ሦስት ስለ መማሪያ መጽሀፉ የቃላት መልመጃዎች አሰራር የቀረቡ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ክፍል አራት የመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ብቃት በተለይ ከተማሪዎች ባህሪ ለውጥ ጋር በተያያዘ የቀረቡ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ክፍል 5 የመምህራኑን ጠቅላላ አስተያየት በሚመለከት የሰጧቸው መልሶች በየምድባቸው ተተንትነው በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች ስለ መምህራኑ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ ሲሆኑ የመምህራኑን የትምህርት ደረጃ፣ የስልጠና ሁኔታ፣ የአገልግለት ዘመን ና ወዘተ...ን የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 7 የመምህራንን የግል ሁኔታ በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች

7.1 መጠይቁን የመለሱ መምህራን በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛን ያስተማሩባቸው ዓመታት ብዛት

| ተራ ቁጥር | የአገልግሎት ዘመን | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ከ1-5 ዓመት | 1 | 5.6 |
| 2 | ከ6-10 ዓመት | 5 | 27.8 |
| 3 | ከ11-15 ዓመት | 9 | 50 |
| 4 | ከ16-20 ዓመት | 1 | 5.6 |
| 5 | ከ21-25 ዓመት | 1 | 5.6 |
| 6 | ከ26-30 ዓመት | 1 | 5.6 |
| 7 | ከ30 ዓመት በላይ | - | - |
| ድምር | | 18 | 100 |
| አማካይ (Mean) የአገልግሎት ዘመን 11.7 ዓመት | | | |

7.2 መጠይቁን የመለሱ መምህራን ትምህርት ደረጃ

| ተራ ቁጥር | ትምህርት ደረጃ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | 12+1 | - | - |
| 2 | 12+2 / ዲፕሎማ | 13 | 72.2 |
| 3 | 12+3 | - | - |
| 4 | B.A. | 5 | 27.8 |
| 5 | M.A. | - | - |
| ድምር | | 18 | 100 |

7.3 መጠይቁን የመለሱ መምህራን ከ1985 ዓ.ም. ወዲህ ሥራ ላይ የዋለውን የ9 ኛ ክፍል አማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ በመጠቀም አማርኛን ያስተማሩባቸው ዓመታት ብዛት

| መራ ቁጥር | የ9ኛ ክፍል አማርኛን የማስተማር ልምድ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | 1 ዓመት | 2 | 11.1 |
| 2 | 2 ዓመት | 2 | 11.1 |
| 3 | 3 ዓመት | 2 | 11.1 |
| 4 | 4 ዓመት | 8 | 44.4 |
| 5 | 5 ዓመት | 4 | 22.2 |
| ድምር | | 18 | 100 |

7.4 መጠይቁን የመለሱ መምህራን ስልጠና

| ተ.ቁ | የትምህርት አይነት | የስለጠኑበት የትምህርት አይነት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አብይ ትምህርት | | ንዑስ ትምህርት | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | አማርኛ | 16 | 88.9 | 2 | 11.1 |
| 2 | እንግሊዘኛ | - | - | 9 | 50 |
| 3 | ስነ-ልሳን | - | - | 1 | 5.6 |
| 4 | ሌላ | 2 | 11.1 | 6 | 33.3 |
| | ድምር | 18 | 100 | 18 | 100 |

የመጠይቁ መላሾች የአገልግሎት ዘመን በሠንጠረዥ 7.1 ተመልክቷል፡፡ አብዛኛዎቹ /84.4%/ ከ 6 ዓመት እስከ 20 ዓምት ያገለገሉ ናቸው፡፡ አማካይ (Mean) የአገልግሎት ዘመን 11.7 ዓመት ሆኖ በመገኘቱ መጠይቅ መላሾቹ ከፍተኛ ልምድ ያካበቱና ስለሆነ ከስራውና በስራው ላይ ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር በሚገባ የሚተዋወቁ መሆናቸውን ይጠቁማል።

በትምህርት ደረጃ በኩል ሠንጠረዥ 7.2 እንደሚያመለክተው (72.2%) ዎቹ ዲፕሎማ ያላቸው ሲሆኑ የተቀሩት ከዚያ በላይ ናቸው።

በሠንጠረዥ 7.3 ላይ እንደሚታየው አብዛኞቹ (66.6%) መጽሐፉ ታትሞ በስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በተከታታይ እያስተማሩበት የቆዩ በመሆናቸው በመጽሐፉ ላይ ያላቸው እውቀት ከፍተኛ መሆኑንና የሚሰጡት አስተያየት የማያጠራጥር መሆኑን ያመለክታል።

ሠንጠረዥ 7.4 እንደሚያመለክተው የመጠይቁ መላሾች በሙሉ በአማርኛ አብይ ትምልርትነት የሰለጠኑ በመሆናቸው የአማርኛ ቋንቋን ትምልርት ለማስተማር ችሎታ ያላቸው መሆኑን ይጠቁማል።

ሠንጠረዥ 8 የቃላት መልመጃዎቹ አቀራረብ ባህርይና የክፍል ስራ ክንውን በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ መልሶች መግለጫ

8.1 የቃላት መልመጃዎቹ አቀራረብ ባህርይ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎቹ | በከፍተኛ ደረጃ ይቀርባሉ | በመካከለኛ ደረጃ ይቀርባሉ | በዝቅተኛ ደረጃ ይቀርባሉ | በፍጹም አይቀርቡም | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.3 | የቃላት መልመጃዎቹ በፅሑፍ በምን ያህል ደረጃ ይቀርባሉ? ብዛት % | 12<br>66.6 | 3<br>16.7 | 2<br>11.1 | 1<br>5.6 | 18<br>100 |
| 3.4 | የቃላት መልመጃዎቹ በቃል በምን ያህል ደረጃ ይቀርባሉ ብዛት % | 2<br>11.1 | 5<br>27.8 | 10<br>55.5 | 1<br>56 | 18<br>100 |

በሠንጠረዥ 8.1 እንደምንመለከተው የቃላት መልመጃዎቹ በቃል የመቅረብ ሁኔታቸውን በሚመለከት ከመምህራኑ የተሰጠው ምላሽ ዝቅተኛ ነው የሚል ሲሆን መጽሀፉን በማንበብ የሚሰሩ በመሆናቸው ግን መላሾች በሙሉ ይስማማሉ፡፡ ይህም በመጽሐፉ በከፍተኛ ደረጃ የሚቀርቡ መሆናቸውን ከሚገልፀው (66.6%) የመምህራኑ አስተያየት ጋር ሲገናዘብ የቃላት መልመጃዎቹ የማንበብ ክሂልን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያዳብሩ የሚጠበቅባቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

8.2 የተማሪዎች ተራክቦ

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 3.2 | የቃላት መልመጃዎች በክፍል ውስጥ በምን መልክ ይቀርባሉ? | | |
| | 1. በተናጠል በግለሰብ ደረጃ | 13 | 72.2 |
| | 2. በጥንድ | - | - |
| | 3. በቡድን | - | - |
| | 4. በጥንድና በቡድን | 1 | 5.6 |
| | 5. በጥንድና በግል | 1 | 5.6 |
| | 6. በግልና በቡድን | 1 | 5.6 |
| | 7. በሁሉም | 1 | 5.6 |
| | 8. በሌላ መንገድ | 1 | 5.6 |
| | ድምር | 18 | 100 |

8.3. የቃላት መልመጃዎች የአስተራረም ሁኔታ

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 3.1 | መልመጃዎችን የሚያርመው ማን ነው? | | |
| | 1. መምልሩ | 11 | 61.1 |
| | 2. ተማሪዎች የራሳቸውን በግል | - | - |
| | 3. አንዱ የሌላውን ስራ እየተለዋወጡ በግል | 3 | 16.7 |
| | 4. በቡድን ተደራጅተው የእያንዳንዱን ተማሪ በተራ ቡድን | 2 | 11.1 |
| | 5. ሁለት ሁለት እየሆኑ የሁለቱንም በጋራ | - | - |
| | 6. ሌላ መንገድ | 2 | 11.1 |
| | ድምር | 18 | 100 |

በሠንጠረዥ 8.2 እና 8.3 መሰረት የመጽሀፉ የቃላት መልመጃዎች የተሳትፎና የትግበራ ክንውን ሁኔታ ሲገመገም የመልመጃዎቹ አሰራር በተናጠል በግለሰብ ደረጃ የሚከናወን መሆኑ በ (72.2%) እና አራሚዎቹም ተማሪዎች ሳይሆኑ መምህራኑ መሆናቸው የመጽሐፉ የመልመጃ ክንውኖች በመማሪያ ክፍል ተራክቦ ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖ መምህራንን ማዕከል ያደረገና የተማሪዎችን የመማር ማስተማር ክንውን ማዕከላዊ ሚና ገድቦ ቃላትን መማርን የመማርን ዘዴ ተግባራዊ እንዳይሆን የሚያደርግ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 9 የቃላት መልመጃዎቹን ለመሥራት ተማሪዎቹ ያላቸውን ፍላጎትና ችሎታ በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ መልሶች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛ አማራጭ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ጥሩ | | ጥሩ | | ደካማ | | በጣም ደካማ | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 4.1 | ተማሪዎቹ የሚሰጧቸውን የቃላት መልመጃዎች ለመሥራት ያላቸው ፍላጎት | 3 | 16.7 | 5 | 27.8 | 7 | 38.9 | 3 | 16.7 | 18 | 100 |
| 4.2 | ተማሪዎቹ የቃላት መልመጃዎቹን ከሠሩ በኋላ ለማሣረም ያላቸው ፍላጎት | 7 | 38.9 | 4 | 22.2 | 3 | 16.7 | 4 | 22.2 | 18 | 100 |
| 4.3 | ተማሪዎቹ የቃላት መልመጃዎቹን መሠረት በማድረግ ጥያቄዎቹን የማቅረብ ጉጉት | 2 | 11.1 | 6 | 33.3 | 7 | 38.9 | 3 | 16.7 | 18 | 100 |

በሠንጠረዥ 8 ላይ እንደሚታየው መምህራኑ በሰጡት አስተያየት የቃላት መልመጃዎቹን ለመሥራት፣ ጥያቄዎችን ለማቅረብ፣ ለተጨማሪ ንባብና ባጠቃላይ ለቃላት ትምልርት ያላቸው ፍላጎት ደካማ መሆኑ ተጠቁመዋል። በአሃዝ እንደተገለፀውም መልመጃዎችን የመስራት ፍላጎት ድክመትና ጥያቄዎችን የማቅረብ ጉጉት ማነስ እያንዳንዳቸው በ (55.6%) ለተጨማሪ ንባብ ያላቸው ፍላጎት ደካማነት በ (66.7%) ና ባጠቃላይ ለቃላት ትምልርት ያላቸው ፍላጎት ደካማ መሆን በ (72.2%) መላሽ መምልራን አስተያየት ተገልጿል። በአንፃሩም ለማሳረም ያላቸው ፍላጎት ጥንካሬ በ (72.1%) ና ከስልተታቸው ለመማር ያላቸው ፈቃደኝነት በ (83.3%) የመምልራኑ አስተያየት ተጠቅሷል። ይልም የተማሪዎችን በመልመጃዎቹ አማካኝነት ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን የማቀናጀት ተግባርና እየተሳተፉ፣ እያጠኑና እየተገበሩ ቃላትን የማሰስ ተነሳሽነታቸውን መዳከም የሚገልፅ በመሆኑ የመልመጃዎቹ ቃላትን መማርን የመማር አላማ አለማሳካት ይገልፃል።

ሠንጠረዥ 10 የቃላት መልመጃዎቹ ክሒልን ስለማዳበርና አለማዳበራቸው የመምህራን መጠይቅ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛ አማራጭ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ጥሩ | | ጥሩ | | ደካማ | | በጣም ደካማ | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 4.4 | የቃላት መልመጃዎቹ የተመሠረቱባቸውን ምንባቦች አንብቦ የመረዳት የተማሪዎች ችሎታ | 1 | 5.6 | 5 | 27.8 | 9 | 50 | 3 | 16.7 | 18 | 100 |
| 4.5 | የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪ ዎቹን የጽልፈት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው አስተዋጽኦ | 1 | 5.6 | 5 | 27.8 | 8 | 44.4 | 4 | 22.2 | 18 | 100 |
| 4.6 | የቃላት መልመጃዎቹ የተማራዎቹን የማዳመጥ ችሎታ ለማ ዳበር ያላቸው አስተዋጽኦ | 3 | 16.7 | 2 | 11.1 | 9 | 50 | 4 | 22.2 | 18 | 100 |
| 4.7 | የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪ ዎቹን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ያላቸው አስተዋጽኦ | - | - | 3 | 16.7 | 11 | 61.1 | 4 | 22.2 | 18 | 100 |

ሠንጠረዥ 10 እንደሚያሳየው የቃላት መልመጃዎቹ የንባብና የጽልፈት ችሎታን እንደማያዳብሩ ለእያንዳንዱ ክሂል ከ (44.4%) በላይ በሆነ የመላሽ መምልራን ምስክርነት ተጠቁሟል። የንግግር ክሂልን እንደማያዳብሩም በ (61.1%) ና (22.2%) ደካማና በጣም ደካማ በሚል ቅደም ተከተል ተገልጿል። የማዳመጥ ክሂልን ያለማዳበር ችግር በአጠቃላይ የቋንቋ ክሂሎችን የማያዳብሩ መሆናቸውን በ (50%) ደካማና በ (22.2%) በጣም ደካማ በሚል ቅደም ትከተል ተገልጿል፡፡ የማዳመት ክሂልን ያለማዳበር ችግር በ (50.1) ደካማንና በ (22.1%) በጣም ደካማ የሚሉ የመምልራን አስተያየቶች መገለጹ የመልመጃዎቹን ከክሂል መዳበር ጋር አለመገናኘት የሚያመለክት ነው።

የማዳመጥ የንግግርና የጽሕፈት ክሂልን ለማዳበር የቃላት መልመጃዎቹ የሚጫወቱት ሚና በሚመለከት የመምልራኑ አስተያየት በጥቅሉ አሉታዊ በመሆኑ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙው የቃላቱ አቀራበብ ለደረጃው በተዘጋጀው ሲለበስ ላይ የቀረቡትን የቃላት ትምልርት፤ የክሂልና የእውቀት ዘርፍ አላማዎች ለመተግበር የሚያግዙ ናቸው? የሚለው የዚልን ጥናት መሠረታዊ ጥያቄ በአሉታዊ የሚመልስ ይሆናል።

ሠንጠረዥ 11 የቃላት መልመጃዎቹ የእውቀት ዘርፎችን የሚያዳብሩ ስለመሆናቸውና ስለአለመሆናቸው የመምህራን መጠይቅ መልሶች መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛ አማራጭ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ጥሩ | | ጥሩ | | ደካማ | | በጣም ደካማ | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 4.8 | የቃላት መልመጃዎች የስነ ጽሁፍ ችሎታን ለማዳበር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ | 3 | 16.7 | 2 | 11.1 | 6 | 33.3 | 7 | 38.9 | 18 | 100 |
| 4.9 | የቃላት መልመጃዎቹ የስነ መዋቅር ችሎታን ለማዳበር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ | 3 | 16.7 | 2 | 11.1 | 6 | 33.3 | 7 | 38.9 | 18 | 100 |

ይህ ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው የመማሪያ መፅሀፉ የቃላት መልመጃዎች አቀራረብ የስነ ፅሑፍና የስነ መዋቅር ችሎታን የማዳበር አስተዋፅኦ ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም ማለት በዚህ ጥናት መነሻ ምዕራፍ ከተገለፀው ቃላት መማርን ከማስተማር አኳያ፣ የእውቀት ዘርፎችን ከማዳበርና የቃላት ዘርፎችን በተገቢ ስርጭት ከማካተት አኳያ ሲታይ በሠንጠረዥ 18 በተገለፀው መሠረት ክሂሎችን ለማዳበር ካለመቻሉ ጋር ሲገናዘብ የመማሪያ መፅሐፉ የቃላት አቀራረብ ለቋንቋ ትምህርት ገፅታዎች ቅንጅት መሠረት የማይጥልና ቃላትን በምሉእነት የማያቀርብ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ሠንጠረዥ 12 በመማሪያ መጻህፉ የጎላ ትኩረት ላልተሰጣቸው የቃላት ትምህርት የአሰሳ ይዘቶች መምህራኑ የሰጧዋቸው ትኩረት መግለጫ

| ተ.ቁ | ይዘቶች | መመዘኛ አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም አተኩርበታለሁ | | በመካከለኛ ደርጃ አተኩርበታለሁ | | በዝቅተኛ ደረጃ አተኩርበታለሁ | | በጭራሽ ትኩረት አልሰጥም | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2.2ሀ | የትርጉም ዝምድናዎች (Sense relations) | 2 | 11.1 | 10 | 55.6 | 6 | 33.3 | - | - | 18 | 100 |
| 2.2ለ | ተረትና ምሳሌዎች (Proverbs) | 4 | 22.2 | 6 | 33.3 | 7 | 38.9 | 1 | 5.6 | 18 | 100 |
| 2.2ሐ | የቃላት አብሮነት (Collocation) | 1 | 5.6 | 1 | 5.6 | 9 | 50 | 7 | 38.9 | 18 | 100 |
| 2.2 መ | አባባሎች (Expressions) | 4 | 22.2 | 9 | 50 | 3 | 16.7 | 2 | 11.1 | 18 | 100 |
| 2.2ሠ | ምስያዎች (Analogies) | 1 | 5.6 | 10 | 55.6 | 6 | 33.3 | 1 | 5.6 | 18 | 100 |
| 2.2ረ | ጥመራዎች (Compounding) | 5 | 27.8 | 8 | 44.4 | 5 | 27.8 | - | - | 18 | 100 |
| 2.2ሰ | መደበኛ ቃላት (Formal words) | 8 | 44.4 | 8 | 44.4 | 2 | 11.1 | - | - | 18 | 100 |
| 2.2ሸ | ኢ-መደበኛ ቃላት (Informal words) | 3 | 16.7 | 9 | 50 | 5 | 27.8 | 1 | 5.6 | 18 | 100 |
| 2.2ቀ | ሞያ ነክ ቃላት (Technical words) | 4 | 22.2 | 4 | 22.2 | 8 | 44.4 | 2 | 11.1 | 18 | 100 |
| 2.2በ | በተማሯቸው አዳዲስ ቃላት ታሪክ እንዲናገሩ፣ ርዕስ እንዲሰጡና በተሰጡ ርዕሶች ላይ ትንታኔ እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡ | 1 | 5.6 | 6 | 33.3 | 8 | 44.4 | 3 | 16.7 | 18 | 100 |

ሠንጠረዥ 12 እንደሚያሳየው መምልራኑ በአብዛኛው ከሚጠቀሙባቸው የቃላት ይዘቶች መሀል የቃላት አጠቃቀም ዘርፍ ይዘቶች የሆኑት ተረትና ምሳሌ በ (38.9%)፣የቃላት አብሮነት በ (50%) ና ሞያ ነክ ቃላት በ (44.4%) በጥቅም ላይ የመዋል እድላቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ተረጋግጧል። ይህም በሌላ በኩል ሲታይ መማሪያ መፅሀፉ በሚገባ ሊያቀርበው ያልቻለውን

መምህራኑ ሙሉ ለሙሉ መጠቀም በሚያስችል መልክ ዝግጅት አድርገው ማስተማር አዳጋች እንደሆነባቸው የሚጠቁም ነው።

ሠንጠረዥ 13 የመማሪያ መጽሐፉን የአዳዲስ ቃላት ማስተማሪያ ስልቶች ትግበራ በተመለከተ የመምህራን መጠይቆች መልሶች መግለጫ

| ተ.ቁ | የጥያቄዎች ይዘት ትኩረት | መመዘኛ አማራጭ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ እጠቀምበታለሁ | | በመጠኑ እጠቀምበታለሁ | | አልፎ አልፎ እጠቀምበታለሁ | | ጭራሽ አልጠቀምብትም | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2.1ሀ | በማጥበቅና በማላላት የቃላት የተለያዩ ትርጉሞችን መመርመር (የሆሄያትና ድምጾች) | 9 | 50 | 7 | 38.9 | 2 | 11.1 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ለ | የተለያዩ ቅጥያዎችን ለይቶ ማመልከት (ጥቅያ) | 7 | 38.9 | 5 | 27.8 | 6 | 33.3 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ሐ | በአናባቢና በተናባቢ ድምጾች የሚጨርሱ ቃላትን መለየት(ሆህያትና ድምጾች) | 2 | 11.1 | 11 | 61.1 | 5 | 27.8 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1መ | የስም ገላጮችን ለይቶ ማውጣት(ቅፅል) | 5 | 27.8 | 7 | 38.9 | 5 | 27.8 | 1 | 5.6 | 18 | 100 |
| 2.1ሠ | የቃላትን የንግግር ክፍሎች ለይቶ ማውጣት(የቃላት ሠዋሰው) | 4 | 22.2 | 10 | 55.6 | 4 | 22.2 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ረ | ለእርባታ ስያሜ መስጠት (ቅጥያ) | 8 | 44.4 | 7 | 38.9 | 2 | 11.1 | 2 | 11.1 | 18 | 100 |
| 2.1ሰ | በምንባቡ ፍች መሠረት ዐ.ነገር መስራት (አውዳዊ ፍች) | 10 | 55.6 | 4 | 22.2 | 4 | 22.2 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ሸ | በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሠረት ፍቺ መስጠት (አውዳዊ ፍች) | 13 | 72.2 | 4 | 22.2 | . | . | 1 | 5.6 | 18 | 100 |

| ተ.ቁ | የጥያቄዎቹ ይዘት ትኩረት | መመዘኛ አማራጭ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ እጠቀምበታለሁ | | በመጠኑ እጠቀምበታለሁ | | አልፎ አልፎ እጠቀምበታለሁ | | ጭራሽ አልጠቀምብትም | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2.1ቀ | ለተሰጡት የመግለጫዎች ዝርዝር ሊቆሙ የሚችሉ ስሞችን መናገርና በግልባጭም ለስሞች ዝርዝር መግለጫ መስጠት (መዝገበ ቃላዊ ፍች) | 5 | 27.8 | 7 | 38.9 | 5 | 27.8 | 1 | 5.6 | 18 | 10 |
| 2.1በ | ከአንድ በላይ ፍችዎችን መስጠት (ድርብርብ ውክልና) | 9 | 50 | 5 | 27.8 | 4 | 22.2 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ተ | ተመሳሳይ ቃላት መስጠት (የትርጉም ዝምድና) | 6 | 33.3 | 8 | 44.4 | 2 | 11.1 | 2 | 11.1 | 18 | 100 |
| 2.1ቸ | ተቃራኒ ቃላት መስጠት (የትርጉም ዝምድና) | 9 | 50 | 4 | 22.2 | 5 | 27.8 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ኅ | በማዛመድ መተርጎም (የትርጉም ዝምድና) | 8 | 44.4 | 7 | 38.9 | 3 | 16.7 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ነ | በጥንድ ቃላት መሀል የሚገኝን የትርጉም ልዩነት ማመልከት (የትርጉም ዝምድና) | 6 | 33.3 | 8 | 44.4 | 4 | 22.2 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ኘ | በዐ/ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት በአገባባቸው መሠረት ትርጉም መምረጥ (አውዳዊ ፍቺ) | 8 | 44.4 | 4 | 22.2 | 6 | 33.3 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1አ | በምንባቡ ውስጥ ቃላቱ ለዘይቤነት የሚወክሉትን መጠቆም (ተለዋጭ) | 6 | 33.3 | 6 | 33.3 | 6 | 33.3 | . | . | 18 | 100 |
| 2.1ከ | በምንባቡ ሀረግን የሚተካ ቃል መምረጥ (መዝገበ ቃላዊ ፍች) | 4 | 22.2 | 8 | 44.4 | 6 | 33.3 | . | . | 18 | 100 |

በሠንጠረዥ 13 መሠረት መጠይቁን የሞሉ መምልራን መልሶች እንደሚያመለክቱት ሁሉም የመጽሐፉ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶች በመምልራኑ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ከ 2.1ሀ - 4.1ለ ካሉት የመምልራኑ ምላሾች እንረዳለን። ከቀረቡት 17 ክንውኖች 9 ከ (38.9% - 72.2%) መላሾች ሁልጊዜ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ሲገልፁ 7 የሚሆኑ ደግሞ ከ (33.3% - 61.1%) በሚደርሱ መላሾች በመጠኑ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተገልጿል። አልፎ አልፎ እጠቀማለሁና "ጭራሽ አልጠቀምም" በሚሉት አማራጮች ብልጫ አለመመዝገቡና መምልራኑ በአብዛኛው የመጽሐፉ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶች በክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ክንውን ተግባራዊ ማድረጋቸው የመማሪያ መጽሐፉን በክፍል ውስጥ የመምልርና የተማሪን ተራክቦ የመቆጣጠር ሚና የሚያሳይ ነው።

### 4.1.3. ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዘህ ርእስ ስር የሚጠቃለለው የፌድራሉ የስርአተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም የቋንቋ ትምልርት ቡድን መሪና የአንድ የመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጅ እንዲሁም አርታኢ አስተያየት ነው። የቋንቋ ቡድን መሪው በሥርአተ ትምልርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም የቋንቋ ቡድን ሃላፊነታቸው ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያገለግለውን የ፱ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ ዝግጅት፤ የማሻሻልና የልትመት መብቃት ተግባርን በሃላፊነት የሚመሩ ናቸው። በዝግጅቱ የተካፈሉ የትምልርት ባለሙያዎች በሙሉ ሀሳባቸውን ቢያካፍሉ ጠቀሜታው የጎላ እንደነበር ይታወቃል። ይሁን እንጂ የመፅሀፉ አዘጋጆች ከፌድራሉ ከስርዓተ ትምልርት ጥናትና ምርምር ተቋም ለቀው በሌላ ቦታ የሚሰሩ ስለሆኑና በዝግጅቱ ተካፋይ ከነበሩት ካሁኑ የቋንቋ ቡድን ሀላፊና ከአንድ ሌላ የመጽሀፉ አዘጋጅ በስተቀር ለቃለ መጠይቁ ሁሉንም ማግኘት ባለመቻሉ የሁለቱን ሰዎች የቃለ መጠይቅ መልስ እንደሚከተለው በማካተት ለማቅረብ ተሞክሯል። (ቃለ መጠይቆቹን በአባሪ "ለ" ና "ሐ" ላይ ይመልከቱ)

ሠንጠረዥ 14 ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ባለ ሙያዎች አጠቃላይ መረጃ

| ተ.ቁ | የሥራ ቦታ | የሥራ መደብ | የት/ደረጃ | አገልግሎት ዘመን | የሠለጠኑበት ዋና | የትም/ዓይነት ንዑስ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የፌድራሉ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም | የቋንቋዎች ትምልርት ቡድን መሪ | M.A. | 25 አመት | አማርኛን ማስተማር | - |
| 2 | የፌድራሉ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም | አርታኤነት . | B.A. | 18 አመት | በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ /አማርኛ/ | ሳይኮሎጂ |

ቃለመጠይቁ የተደረገላቸው የቋንቋ ትምልርት ቡድን መሪ አሁን ባሉበት የሥርዓተ ትምልርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም ለ 10 ዓመታት ቆይተዋል። በአሁኑ ወቅትም የቋንቋ ትምልርት ቡድን መሪ በመሆን እየሠሩ ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያገለግሉትን አማርኛ መማሪያ ማስተማሪያ ተከታታይ መፅሐፍት ዝግጅት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ጉዳዩን በአባልነት እየተከታተሉ ስለቆዩና አሁንም በሀላፊነታቸው ምክንያት ከመስክ ከሚገኘው መልሶ ምገባ (Feedback) ጋር ባላቸው ግንኙነትና በሚካሄደው የመፅሀፉ መሻሻል ላይ የመሪነት ሚና ስላላቸው ከርሳቸው የሚገኘው መረጃ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል።

አዘጋጅ ባለሙያው ምንም እንኳን በአሁን ጊዜ ከቋንቋው ቡድን ተዛውረው በማምረቻና ማከፋፈያ የትም/ሚኒስቴር ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ቢሆንም ቀድሞ ስላዘጋጁት መፅሀፍት የሚያውቁትን ቢገልፁ መረጃው እንደሚጠናከር ይታመናል።

ቃለ መጠይቁ የተደረገላቸው ሰዎች በሰጧቸው መልሶች እንደተጠቆመው አዘጋጆቹ ለመፅሀፉ ዝግጅት የተመረጡት የቡድኑ አባላት ስለነበሩ ቢሆንም ዝግጅቱ፤

ሀ. ከሙያ ተዋፅኦ አንፃር ብዙ ባለሙያዎችና የሕብረተሰብ ክፍሎች፤

ለ. በትምልርት ደረጃ አንፃርም ከዲፕሎማ እስከ ከፍተኛ ድልረ ምረቃ (PhD)፤

ሐ. በመምልራን ተዋፅኦም ከሀገሪቱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሙሉ የተወከሉበት እንደነበር ተገልጿል።

ሆኖም ትኩረቱ በልዩ ልዩ የቋንቋ ገፅታዎች ለምሳሌ:- በቃላት ላይ ሳይሆን በአጠቃላይ በክሂሎችና በእውቀት ዘርፎች ላይ ነው የሚለው የማያዳግም መልስ የቃላትን የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች አቀናጅነት ሚና እውቅና የማይሰጥ በመሆኑ በመፅሀፍ ትንተናና በመምልራን የጽሁፍ መጠይቅ ካነሳነው የቃላት ብቃት ችግር ጋር የሚዛመድ ሆኖ ተገኝቷል። ከመስክ በተገኙ መልሶች ምዝገባ የቃላት መልመጃዎቹን ችግሮች የሚጠቁም መረጃ ይገኝ እንደሁ ተጠይቆ የተገኘው መልስ በሁለቱም አኳያ በአብዛኛው የቋንቋን አጠቃላይ ጉዳዮች የተመለከተ ቢሆንም በተለይ አዲሱ የ፱ኛ ክፍል ጥራዝ ባለፈው ላይ ተመስርቶ የተሻሻለባቸውን ነጥቦች የቋንቋው ቡድን የውይይት ሪፖርት እንዳመለከተው:-

የተነደፉ ዓላማዎች ግልፅነት፤
የይዘቶች ግልፅነት፤
የአደራደር ግልፅነት፤
የቅደም ተከተል ግልፅነት፤
የመግለጫዎች በማያሻማ መልክ መቅረብ፤
የቃላትና ዐ.ነገር ግልፅነት፤
የሥርዓተ - ነጥቦችና የአንቀፆች ግልፅነት፤
የመልመጃዎች ግልፅነት፤
የምሳሌዎች በቂነት፤
ለደረጃው የቀረቡ ምንባቦች መጠን፣ ማነስ/መብዛት፣ ወዘተ የሚሉ በመሆናቸው

ለቃላት የተሰጠው ትኩረት እጅግ ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል። ተግባራዊ ሁኔታው በመላሾች እንደተገለፀው መልመጃዎቹ በተለይ ተሳትፎንና ትግበራን የሚያነሣሡ ካለመሆናቸውም በላይ ስልታዊ አካሄድ ስለ ቃላት መታወቅ ያለባቸውን ጉዳዮች ስለማያካትቱ እያስሳችሁ ተሳተፉ፤ አጥኑና ተግብሩ የሚለውን የመልመጃዎች አካሄድ ስልት የሚከተሉ አለመሆናቸው ተጠቁሟል። ለዝርዝር መልሱ አባሪ "መ" ና "ሠ" ይመልከቱ።

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

### 4.2.1 ከ 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ትንተና የተገኘ ውጤት

የ 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት ብቃት "እያሰሳችሁ፣ እየተሳተፋችሁ፣ እያጠናችሁና እየተገበራችሁ ቃላትን መማርን ተማሩ "በማለት የተማሪዎችን ማዕከላዊ ሚና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በሚያጠናክር መስፈርት ይመረመር ዘንድ ጥናቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች በመሪ የጥናቱ ዓላማነት ይዞ መነሣቱ ከዚህ በላይ በቀረቡት ማብራሪያዎች በየአጋጣሚው የተወሳ ጉዳይ ነው. በዚህም መሠረት:-

1ኛ. የቃላት መልመጃዎቹ "እያሰሳችሁ ተሳተፉ፣ አጥኑና በተግባር ተርጉሙ " የሚለውን ስልታዊ አካሄድ መሠረት በማድረግ ተማሪዎች አንድ ወጥ የሆነውን ተግባራዊ የቃላት ማስፋፊያ መንገድ እንዲከተሉ ያደፋፍራሉ?

2ኛ. የቃላቱ አቀራረብ ስልት ትርጉምን፣ አጠቃቀምን፣ ምሥረታንና የቃላት ሰዋሰውን በተገቢ ስርጭት አካተው ይዘዋል?

3ኛ. በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ የሚገኘው የቃላት አቀራረብ በመፅሐፉ መግቢያ ላይ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት የክሒሎና የእውቀት ዘርፍ አላማዎች ለመተግበር የሚያግዝ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ በአሰሳ የቃላት ትርጉምን፣ አጠቃቀምን፣ ምሥረታንና ሰዋሰውን ትኩረት በመስጠት ለማጥናት የተሞከረ ሲሆን የቃላቱን የክሒሎችና የዕውቀት ዘርፎች አቀናጅነት ሚና ለመመርመር የመልመጃዎቹን አካሄድ በተሳትፎ በጥናትና በተግባር ክንውኖች መመዘኛነት ለመመርመር ተሞክሯል.

አሰሳው የቃላት ትርጉምን ማካተት አለማካተቱን ስንመረምር አውዳዊ ፍች በ7(14.58 %) የትርጉም ዝምድና በ 31 (64.58%) ድርብርብ የትርጉም ውክልና በስድስት (12.5%) እና መዝገበ ቃላዊ ፍች በአራት (8.33%) የመማሪያው መፅሀፍ ናሙና የመልመጃ ጥያቄዎች በመወከል በድምሩ 48 (48.98%) የቃላት ጥያቄዎችን በማካተቱ ከቃላት አጠቃቀም፣ ከቃላት ምሥረታ እና ከቃላት ሰዋሰው የበለጠ ድርሻ ይዞ ተገኝቷል. ይሁን እንጂ ከሌሎች የቋንቋ ገፅታዎች አቀናጂነት ሚናው አኳያ ሲታይ በአውዳዊ ፍች 4(8.3%) ና በድርብርብ የትርጉም ውክልና 6 (12.5%) በድምሩ 10 (20.83%) በአጠቃቀም ላይ እና በትርጉም ዝምድና በአውዳዊ ፍች፣ በትርጉም ውክልናና በመዝገበ ቃላዊ ፍች በድምሩ በ 38 (79.16%) በትንተና ላይ በማተኮሩ ከተግባቦት ይልቅ ለስነ-ልሳናዊ ዕውቀት የበለጠ ትኩረት መስጠቱ ይስተዋላል፡፡ በትንተናውም በኩል ቢሆን በርካታ ውሱን ትርጉም ያላቸው ቃላት በጥቂት ጠቅላይ ቃላት የሚካተቱበትን የተካትቶ የትርጉም ግንኙነት (Hyponyms) ባለመያዙ ከአውዳዊና ከመዝገበ ቃላዊ ፍች ይበልጥ በተመሳሳይ እና በተቃራኒ የትርጉም ግንኙነቶች ላይ በይበልጥ በማተኮሩና አብዛኞቹ የቃላት ትርጉም ነክ ጥያቄዎች ከአውድ ውጭ የሚቀርቡ በመሆናቸው ተገቢውን ስነ-ልሳናዊ ሚና የሚጫወት አይመስልም፡፡ በመፃሀፉ የሰፈሩት የቃላት ትርጉም አጠቃቀም ጥያቄዎች ቃላትን ሰጥተው ዓረፍተ ነገር እንዲሰራባቸው የሚያዙ እንጂ ተግባራትን ከአውዳዊ ሁኔታዎች ጋር አካተው የሚተገበሩባቸውን መንገዶች ስለማያመቻቹ የትርጉም አጠቃቀም እውቀት ደረጃን የማሳደግ አቅማቸው ተለይቶ የሚታወቅና መደበኛነት ያለው አልሆነም፡፡

በቃላት አጠቃቀምም በአብዛኛው (90%) ለአተናተንና (10%) ብቻ ለአጠቃቀም ትኩረት በመስጠቱ መማሪያ መጽሐፉ እንደ ተለዋጮች ፈሊጦችና ወዘተ የመሣሠሉትን የቃላት አጠቃቀም ይዘቶች በትወራ ስልት ለተማሪዎች ለማቅረብ ሞክሮ እንደሆን እንጂ በአተገባበር ሲያቀርብ የታየበት ሁኔታ ጎልቶ አይስተዋልም፡፡ አሰሳ ለማድረግ ዋናው መሣሪያ የቃላትን ባህሪያት ለየቶ ማወቅ ቢሆንም መማሪያ መጽሐፉ የቃላት አጠቃቀም ይዘቶችንም ሆነ ሌሎች መሠረታዊ የባህሪ መለያዎችን ለምሣሌ " ሀረጎችን ለይ (ዓረፍተ ነገር ሰራባቸው) " በማለት

በጥቅል ስያሜዎቻቸው በማቅረብ የተማሪዎችን የቃላት ሁለንተናዊ ዕውቀት መሻሻል ስለሚገድብ ቃላትን መማርን የማስተማር ሚናው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የቃላት ምስረታን በተመለከተም ከናሙና መልመጃዎቹ በተገኘው ውጤት መሠረት ብዛታቸው 4 (4.08%) ብቻ በመሆኑና እነዛውም ቢሆኑ በአተናተን ላይ ብቻ ያተኮሩ በመሆናቸው አዳዲስ ቃላትን በመፍጠርም ሆነ የተፈጠሩትን በመረዳት ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ዝቅተኛ በመሆኑ ለመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ብቃት የሚያበረክቱት ድርሻ ይኸ ነው የሚባል አይደለም።

የመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ብቃት በቃላት ስዋሰው ገጽታው ሲታይም በርካታ የሰዋሰው ይዘቶችን በማካተት ጠንካራ ጎን እንዳለው ቢታወቅም ይዘቱ የተሰተዋለው የስርጭት ድርሻ ባለመመጣጠንና የቃላት ስዋሰው የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ጠቋሚ ሊሆኑ በሚችሉበት መልክ ባለመቅረባቸው በዚህም በኩል የሚታየው ችግር የአሰሰውን ብቃት ያዳከመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከመረጃ ልውውጥ አኳያ ተማሪዎቹ ቃላትን የሚማሩት በ(70.4%) በንባብና በ (29.59 %) ተለይቶ ባልታወቀ መረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያ አይነት በመሆኑ አሉ ከሚባሉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ግማሹን እንኳን ባለመጠቀም የዘመናዊነት ችግርም እንዳለበት በዚህ ጥናት የተደረሰበት ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ የቃላት ጥያቄዎቹ የሚመለሱት በቃል ይሁን በጽሑፍ ተለይቶ አለመታወቁ በ(94.89%) በመጽሐፉ ላይ በተደረገ ጥናት መረጋገጡ ሁሉም (100%) የቃላት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ብቻ የሚፈልጉ ሆነው መገኘታቸውና (74.48%) የሚሆኑት ጥያቄዎች በትንታኔ ላይ እንጂ በተገባቦታዊ አጠቃቀም ላይ አለማተኮራቸው በአሰሳ የቃላትን ሁለንተናዊ ገጽታ ለማሳየት በቂ ዝግጅት አለመደረጉን ይጠቁማል፡፡

የመጽሐፍ ትንተናውን ለማድረግ ከሠንጠረዥ 2-6 ከተሠባሠቡትመረጃዎች እንደምንገነዘበው መማሪያ መጽሐፉ ለንግግርና ለማዳመጥ ክሂል (1.25%)፣ ለጽህፈት ክሂል (1.25%) ናለንባብ ክሂል (31.87%) በድምሩ ለክሂሎች (34.37%) ብቻ ትኩረት ስለሚሰጥና ከዚህም የክሂሎች ትኩረት ውስጥ (92.72%) የሚሆኑት ጥያቄዎች በንባብ ላይ ብቻ ያተኮሩ በመሆናቸው ለክሂሎች የተመጣጠነ ድርሻ አለመኖርና ለማስተላለፊያ ክሂሎች በቂ ትኩረት ያለመስጠት ችግር ጎልቶ ይታያል፡፡ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የንባብ ክሂልም ቢሆን ሙሉ በሙሉ የተወከለው አጫጭር መልሶችን በሚፈልጉ ጥያቄዎች በመሆኑና ለማስተላለፊያ ክሂሎች መዳበር የሚበጁ መረጃዎችን እንዲሰጥ ሆኖ ባለመዘጋጀቱ የሚጠበቅበትን ዓላማ ግብ ያስመታል ማለት ያስቸግራል፡፡

ሁሉም ከአጠቃቀም ይልቅ በአተናተን ላይ በመመስረታቸው፣ በመጽሐፉ መግቢያ (60%) የአጠቃላይ ዓላማዎች ብዛት እንዲኖራቸው ተደርገው የታቀዱት ክሂሎች፣ (40%) ዓላማዎች ብዛት እንዲኖራቸው ከተደረጉት የዕውቀትዘርፎች የአነሰ ትኩረት ስለተሰጣቸው፣ ከዕ ውቀት ዘርፎች መሀልም (93.33%) የሚሆነው ለቃላት ዕውቀት የተሰጠ ትኩረት በመሆኑ፣ ቃላቱም ቢሆኑ ለቀጥታ የንባብ ጥያቄዎች መልስ አሰጣጥ እንዲያገለግሉ ሆነው የቀረቡ እንጂ ግንዛቤዎችን ለማዳበርና ለማስተለለፊያ ክሂሎች አገልግሎት በደረጃ ተግባር ላይ እንዲውሉ የሚያደርጉ የመልመጃ ክንውኖች ስለሌሏቸውና ወዘተ የቃላት ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን የማቀናጀት ሚና የተገደበ ሆኖ ይታያል፡፡ በተለይ በምዕራፍ ሁለት የተገለፀውን የብዙዎች ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀም ችግር በሚፈታ መልክ አለመዘጋጀቱ የመጽሐፉን የቃላት ብቃት ችግር በይበልጥ የሚያጎላ ማስረጃ ነው፡፡

በመሆኑም የመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ብቃት ከ"እያስሳችሁ ተሳተፉ አጥኑና ተግብሩ" መስፈርት አኳያ ሲታይ በአባሪ "ረ" የተዘረዘሩትን መፈተሻ ጥያቄዎች በአዎንታዊ መልክ ያለመመለስ ችግሮች ያሉበት መሆኑ በዚህ የመፃህፍት ትንተና ተደርሶበታል፡፡

ስለሆነም የመጽሐፉ ትንተና እንደሚያመለክተው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት መልመጃዎች በአባሪ "ረ" ከላይ ከተዘረዘሩት ነጥቦች በተለይ ከ4.1 - 4.9 የተጠቀሱትን ከአሰሳው መስፈርት፣ ከተራ ቁጥር 1.1 - 1.2.5 የሚገኙትን ፣ከተሳትፎ መስፈርት፣ ከተራ ቁጥር 2.1 - 2.6 የሚገኙትን ከጥናት መስፈርትና ከተራ ቁጥር 3.1 - 3.5 የሚገኙትን፣ ከትግበራ መስፈርት ባለማሟላት ምክንያት በምዕራፍ አንድ የተጠቀሰውን መሪ አላማ ("እያሰሳችሁ፣ እያጠናችሁና እየተገበራችሁ ቃላትን መማርን ተማሩ") የሚለውን መርህ ያላሟሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 4.1 - 4.9 ከተጠቀሱት ነጥቦች በተጨማሪ የመማሪያ መጽሐፉ የቃላት መልመጃዎች በመጠን ብዛት የሰጡት ትኩረት ሲታይ የቃላት ትርጉም በ (48.97%)፣ የቃላት አጠቃቀም በ(20.4%)፣ የቃላት ምስረታ በ(4.08%) እና የቃላት ሰዋሰው በ (26.53%) የቃላት ጥያቄዎች ባልተመጣጠነ ሁኔታ በመወከላቸው "የቃላቱ አቀራረብ ስልት ትርጉምን፣ አጠቃቀምን፣ ምስረታንና የቃላት ሰዋሰውን በተገቢ ስርጭት አካቶ ይዟል?" የሚለውን የጥናቱን መሪ ጥያቄ በመመለስ ረገድ የተመጣጠነ ስርጭት ስለሌላቸው ጥያቄውን በአወንታዊ መልስ የሚመልሱ ሆነው አልተገኙም፡፡

እንዲሁም የቃላት መልመጃዎቹ አቀራረብ ከዚህ በላይ ከተራ ቁጥር 1-3 የሰፈሩትን ነጥቦች በአለማሟላቱ፣ ከሂላዊ ጥያቄዎቹ በ2.5% የናሙና መልመጃ ጥያቄዎች ብዛት ብቻ በመወሰናቸውና በመሣሠሉት ምክንያቶች "በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ

የሚገኘው የቃላት ትምህርት የክሂልና የእውቀት ዘርፍ አላማዎችን ለመተግበር የሚያግዝ ነው?" የሚለውን ጥያቄ በአዎንታዊ መልክ ስለማይመልስ በአጠቃላይ ከትንተናው የተገኘው ውጤት በአሁኑ ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ9ኛ ክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተመሠረቱባቸው ዘዴዎች (mothods) ቴክኒኮች (techniques) እና ስልቶች (strategies) ተማሪዎች ቃላትን እንዲማሩ በማስተማር ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ መልክ የተዘጋጀ አለመሆኑ በጥናቱ ሂደት ተስተውሏል፡፡

### 4.2.2 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት

ለመምህራን በቀረበው መጠይቅ አማካይነት ለማወቅ የተፈለገው የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን ፍላጎት ምን ያህል እንደሚያነሳሱ፣ በመምህሩ ግንዛቤ አማካኝነት የመፅሀፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ሥልት የተማሪዎችን ክሒልና የቋንቋ እውቀት ለማዳበር የማስቻል አስተዋፅኦ ምን ያህል እንደሆነና የመፅሀፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በክፍል ውስጥ ተራክቦ ምን ያህል ተፅእኖ እንዳሳደረ ለማወቅ የታቀዱ ናቸው፡፡

የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪዎችን ፍላጎት ምን ያህል እንደሚያነሳሱ ለማወቅ የመምህራኑን ምስክርነት በማግኘት ረገድ የተደረገው ጥረት ያስገኘው ውጤት ተማሪዎቹ የሚሰጧቸውን የቃላት መልመጃዎች የመሥራት ፍላጎታቸው ደካማ መሆኑ (39.6%)ና በጣም ደካማ መሆኑ በ(16.7%) በመምህራኑ ምስክርነት ተገልጿል፡፡ መልመጃዎቹን መሠረት በማድረግ ጥያቄዎችን የማቅረብ ጉጉታቸው ሲታይም እንዲሁ ደካማ መሆኑ በ (38.9%) ና በጣም ደካማ መሆኑ በ (16.7%) ምስክርነት ተጠቁሟል፡፡ እነዚህም ውጤቶች መልመጃዎቹን ከሠሩ በኋላ ለማሳረም ካላቸው ፍላጎት ጋር ለካርድ ውጤት በመጓጓት ምክንያት ቢቃረኑም የመማር መሠረቶች የሆኑት ተነሳሽነትና ድርጊት ፈተናን ለማለፍ ከመጓጓት የበለጠ ትኩረት ሊሰጣቸው ስለሚገባ የመማሪያ መፅሐፉ የቃላት መልመጃዎች በተማሪዎቹ ፍላጎት ላይ ያላቸው ተፅእኖ አሉታዊ ገፅታው የጎላ መሆኑን የሚጠቁሙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ወደ ችግሩ ምክንያት ለመድረስ ስንሞክር ጉዳዩን ከመልመጃዎቹ ባህርያት ጋር በማያያዝ በተደረገው ጥረት የመልመጃዎቹ በፅሁፍ በከፍተኛ ደረጃ የመቅረብ ሁኔታ በ(66.6%)፣ በቃል በዝቅተኛ ደረጃ የመቅረብ ሁኔታ (55.5%)፣ የቃላት መልመጃዎቹ በተናጠል በግለሰብ ደረጃ የመሰራት ሁኔታ በ(72.2%) መገለፅና አራሚውም መምህሩ መሆኑ በ(66.1%) ምስክርነት መረጋገጥ የሚጠቁመው የመፅሀፉ የቃላት መልመጃዎች ተማሪን ማዕከል ላደረገ የክፍል ውስጥ ክንውን ታስቦ የተዘጋጀ አለመሆኑን ነው፡፡ ይህም በበለጠ የሚረጋገጠው በ4.2.1 የጥናቱ ውጤት ክፍል የጥቀሰነው ከ(97%) በላይ የሚሆኑት የመፅሐፉ መልሶች አጫጭር ሆነው ከመገኘታቸው ጋር ተዛምዶ ሲታይ ነው፡፡

በመምህሩ ግንዛቤ አማካኝነት የመፅሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ስልት የተማሪዎችን ክሂልና እውቀት ለማዳበር የማስቻል አስተዋፅኦው ምን ያህል እንደሆነ ወደሚመረምረው የመጠይቁ አላማ ስንሸጋገርም የቃላት መልመጃዎቹ የተመሠረቱባቸውን ምንባቦች አንብቦ የመረዳት የተማሪዎች ችሎታ ደካማና በጣም ደካማ መሆን በ(50%) እና በ (16.7%)፣ የተማሪዎቹን የፅህፈት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው አስተዋፅኦ ደካማና በጣም ደካማ መሆን በ(44.4%) እና በ(22.2%)፣ የተማሪዎቹን የማዳመጥ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው አስተዋፅኦ ደካማና በጣም ደካማ መሆን በ(50%) እና በ (22.2%)፣ የተማሪዎቹን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ያላቸው አስተዋፅኦ ደካማና በጣም ደካማ መሆን በ(61.1) እና በ (22.2%)፣ የስነ-ፅሁፉ ችሎታን ለማዳበር የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ደካማና በጣም ደካማ መሆን በ(33.3%) እና በ(38.9%) መገለፁና እንዲሁም የስነ መዋቅር ችሎታን ለማዳበር የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ደካማና በጣም ደካማ መሆን በ(33.3%) ና በ (38.9) የመምህራኑ ምስክርነት መጠቆም የመማሪያ መፅሐፉን የቃላት መልመጃዎች የክሒሎችና የእውቀት ዘርፎች አቀናጂነት ሚና ተጠናክሮ አለመቅረቡን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም በመፃህፍት ትንተናው የተደረሰበት የ (2.5%) ብቻ የክሒሎችና የእውቀት ዘርፎች የመማሪያ መፅሐፉ ትኩረት በመምህራን የመማር ማስተማር ትግበራ ላይ ከፍተኛ ችግር ማስከተሉን የሚጠቁም ሆኖ ታይቷል፡፡

የመፅሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በክፍል ውስጥ ተራክቦ ምን ያህል ተፅእኖ እንዳሳደረ ለመመርመር ታልሞ ወደተዘጋጁት የመምህራን መጠይቅ መልሶች ስንመጣም በመማሪያ መፅሐፉ አነስተኛ ትኩረት በተሰጣቸውና ምንም ትኩረት ባልተሰጣቸው የአሰሳ ይዘቶች ላይ መምህራኑ በአብዛኛው፣ በመካከለኛ ደረጃ ትኩረት ሰጥተው የተገኙ ሲሆን እንደ ተረትና ምሳሌ፣ የቃላት አብሮነቶችና ሞያ ነክ ቃላት ለመሳሰሉት ዝቅተኛ ትኩረት መስጠታቸው መማሪያ መፅሐፉ ያላካተታቸውን ይዘቶችና ስልቶች መምህራኑ ለክፍል ውስጥ ክንውኑ በግል ለማሟላት የሚጥሩ መሆናቸውን ከመጠቆም ባሻገር የመምህራኑ ትኩረት በመማርያ መፅሀፉ ይዘቶች ላይ ምን ያህል አንደሆነ ሲመረመር በተገኘው ውጤት አንደታየው በእብዛኞቹ (52.9%) ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸው በራሳቸው ምስክርነት ሲታወቅ (47.9%) በሚሆኑት ደግሞ በመጠኑ የሚጠቀሙ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ከዚህ ውስጥ የቃላት ትርጉም ዘርፍን የሚመለከቱት ከጠቅላላው የመምህራኑ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶች ትኩረት በሁልጊዜ በመጠቀም ድረጃ በ (32.39%)፣ የቃላት ምስረታና የቃላት ሰዋሰው እያንዳንዳቸው በ(11.7%) እና በ (5.8%) በቅደም ተከተል ትኩረት ማግኘታቸው መመስከሩና ለቃላት አጠቃቀም ምንም ትኩረት አለመስጠት በመማሪያ መፅሐፉ ለቃላት ትርጉም ከፍተኛውን ትኩረት ከመስጠት ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ የመማሪያ መፅሐፉን የቃላት አቀራረብ በክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ ያሳደረውን ተፅእኖ የሚያመለክት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጠኑ በመጠቀም ደረጃም ከቃላት ትርጉም (23.5%)፣ ከቃላት ምስረታ (5.8%) ና ከቃላት ሰዋሰው (11.7%) የሚሆኑት በክፍል ውስጥ ክንውን በስራ ላይ መዋላቸውንና ከመካከላቸው በጭራሽ ያለመጠቀም አለመኖር ጋር ተዳምረው የመማሪያ መፅሐፉ አቀራረብ ስልት በአብዛኛው በክፍል ውስጥ የሚተገበሩ መሆናቸውን ስለሚጠቁም በመማሪያ መፅሐፉ ላይ የታየው ድክመትም ሆነ ጥንካሬ በክፍል ውስጥ ተራክቦውም የሚታይ መሆኑ በግልፅ ሊታውቅ ችሏል፡፡

በመሆኑም ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው ትንተና እንደሚጠቁመው መምህሩን ማዕከል ያደረገው የክፍል ውስጥ ተራክቦ በመማሪያ መጽሐፉ እንደሚታየው ለቃላት ትርጉም ላቅ ያለውን ትኩረት በመስጠቱ፣ ለአጠቃቀም፣ ለምስረታና ለሰዋሰውም የተሰጠው ትኩረት ተመጣጣኝ በአለመሆኑና የተማሪዎችን ፍላጎት እያነሳሳ በጽሑፍም ሆነ በቃል የማሳተፍ ክንውኖቹ ተመጣጣኝ ከአለመሆናቸውም በላይ መልመጃዎቹ በግል(በተናጠል) በመሥራት በመምህሩ ብቻ የሚታረሙ በመሆናቸው የተማሪዎችን ማዕከላዊ ሚና ስለሚገድቡ የክፍል ውስጥ ተራክቦየቃላት መልመጃዎቹ "እያሰሳትሁ ተሳተፉ አጥኑና በተግባር ተርጉሙ የሚለውን ስልታዊ አካሔድ መሠረት በማድረግ ተማሪዎች አንድ ወጥ የሆነውን ተግባራዊ የቃላት ማስፋፊያ መንገድ እንዲከተሉ ያደፋፍራሉ?" የሚለውን የዚህን ጥናት መሪ ጥያቄ በአዎንታዊ መልክ ሊመልስ በማይችልበት አተገባበር የሚካሔድ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው ሁኔታዎችና በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኙት የቃላት ይዘቶችና ስልቶች በክፍል ተራክቦው በአብዛኛው ተዘውትረው መካተት የሚያመለክተው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይህን አስመልክቶ የታዩት ችግሮች ከሞላ ጎደል ወደ ተራክቦውም የሚሸጋገሩ መሆናቸውን የሚጠቁም በመሆኑ በክፍል ውስጥ ተራክቦው "የቃላቱ አቀራረብ ስልት ትርጉምን፣ አጠቃቀምን፣ ምስረታንና የቃላት ሰዋሰውን በተገቢ ስርጭት አካቶ ይዟል?" የሚለውን ጥያቄ በመጽሐፉ ተጽዕኖ ምክንያት በአዎንታዊ መልክ እንደማይመልስ በመምህራኑ ምስክርነት ተጠቁሟል፡፡

### 4.2.3 ከቃለ መጠይቅ የተገኘ ውጤት

ቃለ መጠይቁ ያስፈለገበት ምክንያት ከመጽሐፍ ትንተናውና ከመምህራኑ መጠይቅ ትንተና የተገኙትን ውጤቶች በመጽሐፉ አዘጋጆች ከተሰጡት አስተያየቶች ጋር በማገናዘብ ወደ ተሻለ ድምዳሜ ለመድረስ ታስቦ ነው፡፡

የቃለ መጠይቁ ዋና ዓላማ መማሪያ መጽሐፉ በሚዘጋጅበት ወቅት አዘጋጆቹ ለቃላት አመራረጡና አቀራረቡ የተከተሉት ሞዴል እንዳለ (እንደሌለ)ና በአጠቃላይ የትኛውን የቋንቋ ንድፈ ሀሳብ (Theory) ተከትለው እንዳዘጋጁት ለማወቅ መሆኑ በምዕራፍ 3 በዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ መጠቀሱ ይታወሳል፡፡ በዚህ ረገድ ከመጠይቁ የተገኘው ምላሽ ለመጽሐፉ

ዝግጅት በስራ ላይ የዋለ በምሁራን በጋራ የሚታወቅ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ሞዴል ያልተጠቀሰ ከመሆኑም በላይ “እያሰሳችሁ፣ እየተሳተፋችሁ፣ እያጠናችሁና እተተገበራችሁ ቃላትን መማርን ተማሩ“ የሚለው መርህ ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት መነሻ እንዳልሆነ፣ የቃላት ትርጉም፣ አጠቃቀም አመሠራረትና ሰዋሰው በተመጣጠነ ስርጭት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ እንዳልተካተቱና የቃላቱ አቀራረብም በመማሪያ መጽሐፉ መግቢያ የተጠቀሱትን የክሂልና የእውቀት ዘርፍ አላማዎች ለመተግበር በሚያግዝ መልክ በቃላት የክሂሎችና የእውቀት ዘርፍ አቀናጅነት ሚና ላይ ተመስርተው የቀረቡ መልመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ ሁኔታ እንደሌሉ የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑት የሚከተሉት የአባሪ “መ“ እና የአባሪ “ሠ“ ነጥቦች ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

1. በዚህ ጥናት አባሪ መ ውስጥ በሚገኙ የፌደራሉ ስርዓተ ትምህርት ቋንቋ ቡድን መሪ ቃለ መጠይቅ ጥያቄ ተራ ቁጥር 2፣ 3፣ 5፣ 6 ና 7 የተጠቀሱት መልሶች ወደ ቃላት ትምህርት ያዘነበለ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት አለመኖሩን መግለፅ፣

2. በዚህ ጥናት አባሪ “ሠ” ውስጥ በሚገኙት የቀድሞ የአማርኛ ፓናል አባል እና የመጽሐፉ አዘጋጅ ቃለ መጠይቅ ጥያቄ ተራ ቁጥር 3 ና 8 በተጠቀሱት መልሶች የዝግጅቱ አላማዎች በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ መግቢያ የተጠቀሱት መሆናቸውን መግለፃቸውና በእነዚህም ውስጥ ስለ ቃላት ትምህርት የተጠቀሰ ዝርዝር አላማ አለመኖር፣

3. በቋንቋ ቡድን መሪው ጥያቄ 4 መልስ የምንባቦቹ አመራረጥ መስፈርት ላይ በመመርኮዝ፣

   3.1. የክፍሉን ተማሪዎች ደረጃ መመጠን

   3.2. የይዘቶች ከተማሪዎች ማህበራዊ አውድ ጋር መጣጣም

   3.3. ዘላቂነት

   3.4. የተሟላ መልዕክት የማስተላለፍ ሁኔታ

   3.5. የቋንቋ ጥያቄዎችን ለማውጣት የሚኖር አመችነት

3.6. ማሳሰብና ማመራመር መቻል

3.7. ተግባራዊ መሆን መቻል

3.8. ከኪነ ውበት አቀራረብ አንፃር፣ ማራኪና ሳቢ መሆን እንጂ የምንባቦችና የመልመጃዎች በአሰሳ" በትሳትሮ" በጥናትና በትግበራ ክንውኖች ላይ መመስረት አለመሆኑ፣

4. በአማርኛ ፓናል አባሉ የመጽሐፉ አዘጋጅ ጥያቄ ስድስት መልስ መሠረት የምንባቦቹ መምረጫ መስፈርት መሠረት፣

4.1. ከ1ኛ - 8ኛ ካሉት የመፃህፍት ይዘቶች ጋር ያለ ጎናዊና አምዳዊ ግንኙነት መጠበቅ፣

4.2. የስድና የግጥም ምንባቦች ደረጃ መጣኝነት፣

4.3. የምንባቦች መልዕክት፣ የአፃፃፍ ስልት፣ የቃላት ሁኔታ፣ ሰዋሰዋዊ አካባቢ ወዘተ...

4.4. የዝግጅት ቡድን አባላት በግል ግንዛቤ የንባብ ምርጫና በውይይት የቡድን ምርጫ፣

4.5. የባለ ሙያዎች ትችትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ የሚሉት እንጂ የቃላትን ሁለንተናዊ ገጽታ በአሰሳ ማሳየት፣ ለአውዳዊ ነሲብ ስራ በቃላት ብዛት መጠን፣ ትርጉም ጠቋሚዎችን በአይነት ማመጣጠን፣ ምንባቡ በርዕሱ ዙሪያ ተጨማሪ ቃላትን የሚያሰባስብ መሆን፣ ከተማሪዎች የግል ህይወት ጋር መገናኘትና የመሳሰሉትን ማሟላት መቻል (አለመቻል) በሚሉ መስፈርት ላይ አለመምስረት፣

5. በአማርኛ ፓናል አባሉ የመጽሐፉ አዘጋጅ ጥያቄ አራት መልስ መሠረት የመጽሐፉ የቋንቋ ገጽታዎች አመራረጥ ሁኔታ የተመሠረተው፡-

5.1. ከ1ኛ 8ኛ ክፍል የትምህርት ደረጃ ካሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቋንቋ ገጽታዎች ጋር ተከታታይነትና ተለጣጣቂነትን በመጠበቅ፣ አውዳዊና ጎናዊ ግንኙነቶችን መሠረት በማድረግ፣

5.2. ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን እንዲካተቱ በማድረግ፣

5.3. የቃሎች፣ የፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ የዘይቤና የቅኔ ዕውቀት የሚገኙባቸው ይዘቶች እንዲካተቱ በማድረግና፣

5.4. በትምህርት ሂደት ወቅት ይዘቶች የተሰጠውን የክፍለ ጊዜ ብዛት የሚሸፍኑ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንጂ የቃላት አሰሳን፣ የተሳትፎ ክንውኖችን፣ የቃላት ጥናት ክንውኖችንና የትግበራ ክንውኖችን ተግባራዊነት፣ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የጠበቀ አለመሆን፡፡

6. በአማርኛ ፓናል አባሉ የመጽሐፉ አዘጋጅ ጥያቄ አምስት መልስ መሠረት የመማሪያ መጽሐፉ የቃላት አመራረጥ መስፈርት፡-

6.1 ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት በማስታወስ ዕውቀታቸውን እንዲያጠናክሩና አዲስም እንዲያውቁ ማድረግ፣

6.2 የክፍል ደረጃ መጣኝነት፣

6.3 በቅጥያ "ለ" ካሉት የመጽሐፉ ማመሣከሪያዎች ለደረጃው የሚመጥኑትን መምረጥ፣

6.4 ከሌሎች ረዳት መፃህፍት፣ የመዝገበ ቃላት፣ የሰዋሰው፣ የቅኔና የዘይቤ መጽሐፎች የምርጫ ተዋጽኦ እንጂ የቃላት አሰሳን፣ በቃላት የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎችን አቀናጅነት መሠረት ያደረገ የውይይት፣ የንባብና የቃላት ተግባር ተሳትፎን፣ የቃላት ጥናትንና የተጠኑ ቃላትን ወደ ክሂላዊና እውቀታዊ ዘርፎች በትግበራ የማሳደግ ሂደትን የማይከተል መሆኑ፣

7. በአማርኛ ፓናል አባሉ የመጽሐፉ አዘጋጅ ጥያቄ ሰባት መልስ መሠረት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ቴክኒክና ስልት ሞዴል (የመልመጃዎች አካሔድ) ተብለው የተዘረዘሩት፡-

7.1 ተማሪው የቃሎችን ትርጉም ፈልጎና መርምሮ እንዲያውቅ ማስቻል፣ በዐ. ነገር ውስጥ በአላቸው የአገባብ ትርጉም፣ በመዝገበ ቃላት ውስጥ በአላቸው ትርጉም፣ በውስጣቸው በያዙት የትርጉም ብዛት፣ በቃሉ ውስጥ ድምፆች ሲጠብቁና ሲላሉ ያላቸው ትርጉም፣ ዕማሬያዊና ፍካሬያዊ ትርጉም፣

7.2 የቃሎችን ሰዋሰዋዊ አገባብ፣ የስሞችን ጠባይ፣ ስሞችንና ተውላጠ ስሞችን፣ የግሶችን ጠባይ የአገባብ ቃሎችን፣ ቅፅሎችን፣ ተውሳከ -ግሶችን፣ መስተዋድዶችንና መስተጻምሮችን፣ የቃል አጋኖ ፀባዮችንና ወዘተ... ማሳወቅና ማስለየት፣

7.3 የቃሎችን አመሠራረት፣ ነፃ ምዕላዶችን፣ ቀጣይ ምእላዶች፣ ድርብ ቃሎችን፣ ቃሎችን ከሌሎች ቃሎች መመሥረትና ወዘተ ማሳወቅ የሚሉት መሆናቸው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለቃላት ትርጉም፣ ለቃላት ምስረታና ለቃላት ሰዋሰው ትንተናዊ ባህሪ ትኩረት መሰጠቱን እንጂ ለአጠቃቀማዊ ባህሪያቸውና ለራሱም ለቃላት አጠቃቀም ዘርፍ አቀናጅነት ሂደት ስለማይገልጽ የተሰጠውን ትኩረት ስለማያመለክት፣ በተግባር በመማሪያ መጽሐፉ ናሙና መልመጃዎች ውስጥ ሲታይ ለቃላት ምስረታ የተሰጠው ትኩረት በሰንጠረዥ ሁለት መሠረት በአይነትም ሆነ በመጠን እጅግ አነስተኛ ስለሆነና የቃላትን የክሂሎችና የዕውቀት ዘርፍ አቀናጅነት ሂደት ስለማይገልጽ በአዘጋጆቹ ምስክርነት የቀረበው ማስረጃ የመማሪያ መጽሐፉን አሰሳዊ፣ ተሳትፎአዊ፣ ጥናታዊና ትግበራዊ ባህሪ የሚገልፅ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአንፃሩ ግን መማሪያ መጽሐፉ በአጠቃላይ የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች መዳበር ፍላጎት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀቱ በቃለ መጠይቁ መላሾችና በመማሪያ መጽሐፉ መግቢያ ከመገለፁ በስተቀር ለክሂልና ለእውቀት ዘርፎች መዳበር በሚያስፈልጉ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሲሰጥ አለመታየቱ ታውቋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ መደምደሚያና መፍትሄ ሀሳብ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ ጥናቱ የደረሰበት መደምደሚያና ከጥናቱ ጋር የተዛመዱ አስተያየቶች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ ቃላትን መማርን በመማር ዘዴ ላይ የተመሠረተ የቃላት ትምህርት ብቃት በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ መካተት አለመካተቱን ማረጋገጥ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በጥናቱ የሚመለሱት መሰረታዊ ጥያቄዎች በዚሁ ጥናት ውስጥ ባለፉት ምዕራፎች የተገለፁ ሲሆን እነዚህም መሰረታዊ የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስና ከጥናቱ ግብ ለመድረስ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች ተተንትነዋል፡፡ በትንተናው የታቀፉ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት መልመጃዎች በአበይት የመመዘኛ መስፈርቶች ማለትም በአሰሳ ፣ በተሳትፎ ፣ በጥናትና በትግበራ (ቃላትን መማርን ለመማር በሚያስችሉ መርሆዎች) ተገምግመዋል፡፡ በግምገማውም የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የጽሁፍ መጠይቆችና ቃለመጠይቆች የያዟቸው መረጃዎች በቅደም ተከተልና አግባብነት ባለው ቦታ ሁሉ ተተንትነዋል፡፡ ትንተናው ከተካሄደም በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

በአዲስ አበባ መስተዳድር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በስራ ላይ ያለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለቃላት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ ሲሆን ለዚህም ማስረጃው ከመልመጃዎቹ (61.25%) የሚሆነው በቃላት ትምህርት ላይ ማተኮሩና የቀሩት ክሂሎችንና ሌሎች የቋንቋ ዘርፎችን የሚመለከቱ መሆናቸው ነው፡፡ የናሙና መልመጃዎቹ በተመሠረቱበት የመጽሐፉ መግቢያ አምስት /5/ አጠቃላይ አላማዎች መኖራቸው የተገለፀ ሲሆን ከእነዚህም ሦስቱ /60%/ በክሂሎች ላይ የቀሩት /40%/ ደግሞ በቋንቋ እውቀት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ዝርዝር ዓላማ ያልተነደፈላቸው ስለሆነ ትምህርቱ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በመሄድ ፈንታ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ለመምጣት የሚሞክር መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህም መሠረት የቃላት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ የሚታወቀው በመልመጃ ጥያቄዎቹ መጠን እንጂ በዝርዝር አላማዎቹ አግባብነት ባለመሆኑ ፣ የመግቢያው ማዕከላዊ ሀሳብም "ቋንቋ መግባቢያ መሳሪያ ነው" የሚል በመሆኑና ለቃላት ገፅታዎች የዝርዝር አላማ ትኩረት ባለመሰጠቱ የክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ቅንጅት መሰረት የሆኑት የሚደመጡና የሚነገሩ የቋንቋ ንጥረ ነገሮች ሳይሆኑ "ረቂቅ ባህሪ ያለው ቋንቋ" መሆኑ ተስተውሏል፡፡

የአሰሳ ቴክኒክ ብቃቱ በመማሪያ መጽሐፉ ናሙና መልመጃዎች አግባብነት ስንመረምር ከትርጉም ዘርፍ ተካቶ ፣ ከቃላት አጠቃቀም የቃላት አብሮነት ፣ ምስያዎች ፣

መደበኛ ቃላት ፣ ኢመደበኛ ቃላትና ሞያነክ ቃላት የአሰሳ ይዘቶች አንዳችም ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ታውቋል፡፡

የስርጭት ሁኔታቸውን በሚመለከትም ለቃላት ትርጉም ዘርፍ (48.97%) ለቃላት አጠቃቀም (20.4%) ለቃላት ምስረታ (4.08%) እና ለቃላት ሰዋሰው (26.53%) በጥያቄዎች ትኩረት መሰጠቱ በአሰሣው የተመጣጠነ የቃላት ስርጭት አለመኖሩን የሚያመላክት ነው፡፡ ለዚህም ተጨማሪ ማስረጃ የሚሆነው ለቋንቋ ቡድን መሪው ከቀረበው መጠይወቅ መልስ የተገኘው መረጃም በመጽሀፉ ውስጥ ለቃላት ትምህርት ይበልጥ ትኩረት መሰጠቱን አሌ ማለቱ ነው፡፡

ከፌድራሉ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ ጥናትና ምርምር ተቋም የቋንቋ ቡድን መሪና ከአንድ የመጽሀፉ አዘጋጅ ቃለ መጠይቅ ምላሽ በተገኘው መረጃ መጽሀፉ በህዝብ ተዋፅኦ የተዘጋጀ ነው ቢባልም ከመጽሀፉ ዝግጅት ቀደም ብሎ በወጡ የምሁራን ጽሁፎች እንደተገለፀው ከጥናት የተገኙ የተማሪዎችን የቃላት ስህተቶች ትንተና ከተማሪዎች ፍላጎት አሰሳ አኳያ አካቶ መፍትሄ ለመስጠት አለመሞከሩ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በይበልጥ የሚያጎላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቃላት መልመጃዎቹን አካሄድ በተመለከተም አሰሳን አስመልክቶ ያነሳነው እንዳለ ሆኖ ምንባቦቹ የግል አስተያየትን ከመጠየቅ ይልቅ ተዘዋዋሪነት የሌላቸውን ቀጥታ ጥያቄዎች፣ እውነት ወይም ሀሰት፣ አማራጭ መልሶችን የያዙና ሌሎች አጫጭር መልስ የሚፈልጉ በዝርዝር እውነታ ላይ ያተኩሩ ጥያቄዎችን ባለመያዛቸው የተማሪዎችን የውይይት ፍላጎት ለማነሳሳት በቂ ሆነው አልተገኙም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የመጽሐፉ ዝግጅት ተለይቶ በታወቀ ሞዴል ላይ አለመመስረቱ መሆኑን ከቃለመጠይቁ ምላሽ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በትግበራውም በኩል ተማሪዎች በተማሩዋቸው ቃላት ደብዳቤዎችን፣ ማስታወቂያዎችን፣ የህይወት ታሪኮችን፣ ገጠመኞችን፣ ዘገባዎችንና ወዘተ እንዲጽፉና ልዩልዩ የንግግር አይነቶችን እርስ በርስ እንዲያካሂዱ ስለማያደርግ አንዳንድ መሰል ተግባራት ቢኖሩም ከመጽሐፉ ባጠኗቸው ቃላት እንዲያከናውኗቸው የሚያደርግ ፍላጎት የማነሳሳት ተግባር ባለመኖሩ ፣ ከመጽሐፉ በተጠኑ ቃላት የሚተገበሩ አንዳንድ ተግባራትም በመዋቅርና በአሰካክ ላይ ብቻ የተመሰረቱ በመሆናቸው በማህበራዊ የቋንቋ ጠቀሜታ ላይ ባለማተኮራቸውና እነርሱም ቢሆኑ ከተሳትፎ ክንውኖች በመጀመር በጥናት ክንውኖች አልፈው ተያያዥነት ባለው ሁኔታ ወደ ትግበራ በስልታዊ አካሄድ በደረጃ ያላደጉ በመሆናቸው "ተሳተፉ፣ አጥኑና ተግብሩ" የሚለውን መርህና ስልታዊ አካሄድ የሚያሟሉ አይደሉም፡፡ በጥናት ክንውኖቹ የሚካተቱት የመማሪያ መጽሐፉ የቃላት አቀራረብ ስልቶችም ከማይካተቱት ጋር ሲወዳደሩ አናሳ በመሆናቸው ይህንኑ ከላይ የተጠቀሰውን የአካሄድ አለመከተል ችግር የሚያባብሱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የቃላቱን ክሂልና የዕውቀት ዘርፍ አዳባሪነት በሚመለከትም ከክለሳ ድርሳናት በተገኘ መረጃ መሰረት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ በተደረገው ትንተና ከተገኙት የድክመት ማስረጃዎች በተጨማሪ የመምህራን መጠይቅ መልስም ይህንኑ አሉታዊ እውነታ የሚያጠናክር ነው፡፡ በዚህም

ምክንያት መልመጃዎቹ በክፍል ውስጥ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽእኖ የጎላ በመሆኑ የመማሪያ መፅሐፉን የቃላት አቀራረብ ስልት ማሻሻል ማለት የክፍል ውስጥ ክንውኖችን ገፅታ መለወጥ ማለት መሆኑ ታውቋል፡፡ የቃላት ትርጉምን ያለ መዝገበ ቃላትና ያለሌሎች እርዳታ ለማወቅ የሚያስችለውን አውዳዊ ነሲብን ከሰዋሰዋዊ ፍንጮችና ሌሎች እንደ በምስረታ አዳዲስ ቃላትን የመፍጠር ስልት በመጽሐፉ ውስጥ አለመገኘታቸው ቃላትን መማርን የመማር ተግባር ተፈፃሚነት እንዲኖረው ለማድረግ አለመቻሉን የሚያመለክት ነው፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

1. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ከሞላ ጐደል አንብቦ ከመረዳት ክሂል ጋር የተያያዘ፣ አውዳዊ አቀራረብን የተከተለ፣ በሒደታዊ ሳይሆን በውጤታዊ ልምምድ ላይ ያተኮረና ከቃላት አጠቃቀም ይልቅ ለቃላት ፍቺ ቅድሚያ የሠጠ ነው፡፡ ሆኖም ቃላትን መማርን የመማር ዘዴዎችን /Methods/፣ ቴክኒኮችን /Techniques/ እና ስልቶችን /Strategies/፣ መሰረቱን ስንመረምር ለመዋቅራዊ ስነ-ልቦናዊ የቃላት ገፅታ አመልካች የቃላት ይዘቶች ለምሳሌ ከትርጉም ዘርፍ ለተካትቶ፣ ከቃላት አጠቃቀም ዘርፍ ለቃላት አብሮነት፣ ለምስያዎች፣ ለመደበኛና ለኢመደበኛ ቃላት፣ ለሞያ ነክ ቃላትና ከቃላት ምስረታ ዘርፍም ለጥመራ አንዳችም ትኩረት አለመስጠቱ ተማሪዎች በማሰስ ዘዴ ቃላትን እንዲማሩ ሊያደርግ የሚችልበትን ሁኔታ አለማመቻቸቱ እንደ አንድ ችግር የሚታይ ነው፡፡ ቃላትን መማርን የመማር ተግባር መሰረት ከሚሆኑት ዘዴዎች ዋንኛው የቃላት ንጥረ ነገሮች፣ የንጥረ ነገሮች እርስ በርስ ውስጣዊ ግንኙነት፣ በቃላት መሀል ያለ እርስ በርስ ዝምድናና ወዘተን መሰረት ያደረገ የቃላት አፈጣጠር በመሆኑ ይህንን የቃላት አፈጣጠር ተከትሎ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን የትምህርት አቀራረብ አለማደራጀት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጐት አነሳሽነት በየጊዜው እየተለዋወጡና ብዛታቸውም ከአንድ ሰው የመማር አቅም በላይ የሆኑትን ቃላትን የሚማሩባቸውን ስልቶች እንዳያገኙ ማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም የዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ተማሪዎች የቃላት ክሂልን በመጨበጥ ያለመዝገበ ቃላትና ያለ ሌሎች እርዳታ ሊማሩ የሚችሉበትን አውዳዊ ነሲብ ስራ (Contextual guess work) ቴክኒክ እንዲማሩ ባለማቅረቡ ቃላትን መማርን ለመማር በሚያስችል ስልት ተጠናክሮ የተዘጋጀ ነው ለማለት አይቻልም፡፡
2. የመማሪያ መጽሀፉ መልመጃዎች በምንባብ ጥያቄዎች የሚጀምሩ፣ በሁለተኛ ደረጃም ቃላትንና ሌሎች ስነልሳናዊ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎችን የሚያቀርቡና በመጨረሻም አብራራ፣ አቅርብ፣ ውይይት አድርግ፣ ፃፍ፣ አንብብ፣ ወዘተ የሚል አደረጃጀት ያላቸው ቢሆኑም

   ሀ. የምንባቦቹ ጥያቄዎች ባብዛኛው አጫጭር መልሶች ያሏቸውና የግል ግንዛቤን የማይጠይቁ ቀጥታ "ጥያቄዎችን መልስ"፣ "እውነት ወይም ሐሰት" በል፣

"ከቀረቡልህ መሃል ምረጥ"፣ ወዘተ የሚሉ በመሆናቸው የተሳትፎ ስሜት አነሳሽ ውይይቶችን በተማሪዎች አእምሮ ስለማያጭሩ አዳዲስ ቃላትን ለማጥናት በሚያመቻች መልኩ የሚያስተዋውቁ ባለመሆናቸው፣

ለ. ተማሪዎች ባብዛኛው በተናጠል ሳይሆን በጥንድና በቡድን እንደ መጠይቅ መሙላት፣ ልዩ ልዩ ነገሮችን በማወዳደር በግል አስተያየታቸው ላይ የተመሠረተ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና የመሳሰሉትን ለሚቀጥለው የጥናት ክንውን ደረጃ የሚያመቻች ተግባርን አለመፈፀም ስለሚታይባቸው የተሳትፎ ክንውኖችን ይዘዋል ማለት አይቻልም፡፡

ለጥናት ክንውኖችም እንደ ሰንጠረዥ መጨረስ፣ ክፍት ቦታዎችን መሙላት፣ ማዛመድ፣ ቃላትን መወያየት፣ የቃልን ትርጉም መፈለግና በሁለት ቃላት መሀል ያለን የትርጉም ልዩነት ማሳየት የሚሉ ክንውኖች በመፅሃፉ ውስጥ ቢኖሩም ከጠቅላላ የመጽሀፉ ቃላት መልመጃ ጥያቄዎች ቁጥር ጋር ስለማይመጣጠኑ ከተሳትፎ ክንውኖች ያልመነጩና ወደ ቀጣዮቹም የትግበራ ክንውኖች የማይሻገሩ በመሆናቸው ክንውኖቹ ለፈተናዊ ጥያቄ አቀራረብ ሲባል የቀረቡ እንጂ "የተሳተፉ፣ አጥኑና ተግብሩን" የመልመጃዎች አካሄድ ለመጠበቅ ሲባል የተዘጋጁ ባለመሆናቸው የቃላት ትውስታን /memory/ የሚያጠናክሩ አይደሉም፡፡ የትግበራ ክንውኖችንም በሚመለከት ከላይ ስለመጽሀፉ መልመጃ ሶስት ባህሪ ያነሳናቸው ከመቀበያ /Receptive/ና ከማስተላለፊያ /productive/ ክሂሎች ጋር የተያያዙት ጥያቄዎች በተማራችኋቸው ቃላት ከውኑ ስለማይሉ፣ የጥያቄዎቹ ትኩረት ባብዛኛው ከሌሎች ክሂሎች ይበልጥ ወደ ንባብ ያደላ በመሆኑ፣ ጥያቄዎቹ ባብዛኛው የተማሪዎችን የግል /ነፃ/ አስተያየት ከመጋበዝ ይልቅ የተገደበ አስተያየትን በመስጠትና በአጫጭር መልስ ፈላጊ ዝርዝር እውነታዎች ላይ የተመሰረቱ ሰለሆነ፣ አብዛኞቹ የማቅረቢያ መንገዳቸው በፅሁፍ ይሁን በቃል የማይታወቅ በመሆኑና በሌሎችም ምክንያቶች በቃላት ተግባቦታዊ ግብ ላይ የተመሰረቱ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የቃላት መልመጃዎቹ በተሳትፎ፣ በጥናትና በትግበራ ላይ የተመሠረቱ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ከአሰሳ አንፃርም ከላይ በተራ ቁጥር 1 በተጠቀሰው ችግር ምክንያት መልመጃዎቹ ተማሪዎችን ቃላትን እያሰሱ መማርን እንዲማሩ የማያደርጉ መሆናቸው ታውቋል፡፡

3. የቃላት መልመጃዎቹ ከ4ቱ ዘርፎች ለቃላት ትርጉም ትንተናዊ ፍቺ ይበልጥ ትኩረት በመሥጠታቸው፣ ዘርፎቹንና ይዘቶቹን ከተግባቦታዊና ከቋንቋ ትንተና አንፃር ስንከፍላቸው መማሪያ መጽሀፉ ከተግባቦት ይልቅ በትንተና ላይ ያተኮሩ የቃላት መልመጃዎችን ስለሚያቀርብና ከተማሪዎች የሚጠበቀውን የባህሪ ገጽታ በሚያሳየው የፌድራሉ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ ጥናትና ምርምር ተቋም የትምህርት አካሄድ ማሳያ ሠንጠረዥ (flow chart) እንደገለፀው ከዐረፍተ ነገር ጀምሮ ያለውን ደረጃዊ የጽሁፍ አነባበብ ችሎታውን

ያዳብራል በሚል የትንተና አካሔድ ከተግባራዊ ሥነልሳን ልምዶች ይልቅ ገላጭ ሥነልሳንን በተከተለ መንገድ ከድምጽ እስከ አረፍተ ነገር፣ ከዚያ እስከ አንቀጽና ድርሠት በሚጓዝ መሠላላዊ አካሔድ መልመጃዎቹን ስለሚያቀርብ በቃላት ዘርፎችና ይዘቶች የተመጣጠነ ሥርጭትና የክሂልና የእውቀት ዘርፍ የቃላት አቀናጅነት ተግባር ላይ የተመሠረቱ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶችን ይጠቀማል ማለት ያስቸግራል፡፡

4. የቃላት መልመጃዎቹ በዝርዝር እውነታ /objective/ ጥያቄዎች በ 97.5 % አይነት የተዘጋጁ በመሆናቸው የክሒሎችንና የእውቀት ዘርፎችን ቅንጂታዊ ትምህርት ለማካሔድ ስለማያሥችሉ፣ ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰውን የመልመጃዎች አካሔድ በመከተል የቃላትን የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች አቀናጂነት ሚና ስለማያሣዩና በተማሪዎች ላይ የሚታየውን የችሎታ ለውጥ አስመልክቶ የተማሪዎችና የመምህራን ምስክርነት እንደሚጠቁመው የቃላት መልመጃዎቹ 4ቱን ክሂሎች የማያዳብሩ በመሆናቸው በመፅሐፉ መግቢያ የተጠቀሱትን የንግግር፣ የማዳመጥ፣ የንባብና የጽህፈት ክሂሎች፣ የሥነልሳንና የሥነ ጽሁፍ የእውቀት ዘርፎችን ለመተግበር የሚያግዙ የቃላት ማስተማሪያ ሥልቶች አሏቸው ማለት ያሥቸግራል፡፡

በጥቅሉ ሲታይ የመጽሐፉ መልመጃዎች አቀራረብ ችግር መንስኤ ቤትን ለመስራት ከግድግዳው መሰረት (ቃላት) ከመነሳት ይልቅ ከጣራው (ቋንቋ) በመጀመር ትምህርቱ በተጨባጭ ነገር ላይ ተመስርቶ ተጨባጭ ክሂሎችንና እውቀት ለማስገኘት አለመሞከር ነው፡፡ በሌላ አባባል የክሂልና የእውቀት ዘርፍ ትምህርትን ሲነገሩ የሚደመጡትንና ሲጻፉም የሚታዩትን ተጨባጭነት ያላቸውን ቃላትን ትቶ “ቋንቋ መግባቢያ መሣሪያ ነው” በሚል መነሻ በቃላት በኩል ካልሆነ ለሰዎች መገንዘቢያ መሣሪያዎች ( Sense-Organs) ቅርበት የሌለውን ቋንቋን በመማሪያ መጽሐፍ መግባቢያ አነሳሱ፣ ተግባሩ ፣ ጥቅሙና ወዘተ እንዲህ ነው ተብሎ የማይጨበጠውን ጥቅል ነገር ለማስረዳት በመሞከርና በጥቅሉ ነገር ላይ የተመሠረቱ ጥቅል አላማዎችን የመማሪያ መጽሐፍ የዝግጅት መሰረት አድርጐ ያለ ዝርዝር ዓላማ ለማቅረብ መሞከር የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አብይ የችግር መንስኤ ነው፡፡ “ከድምፅ በመጀመር ምዕላድን ፣ ቃላትን ፣ ሀረጐችን ፣ ዐርፍተ ነገሮችንና ፣ ድርሰቶችን በየተራ በመለየት ቋንቋ እናስተምር” በሚል የቋንቋ ማስተማሪያ መርህ ላይ ተመስርቶ መልመጃዎችን የንባብና የስነ-ልሣን ጥያቄ በሚል አከፋፈል የቋንቋ ገጽታዎችን ለያይቶ ቅንጅት በማሳጣት በቃል ወይም በጽሁፍ የሚሰጥ መልስ ሁሉ ክሂልን ያዳብራል በሚል አስተሳሰብ አጫጭር መልሶች በዚህ በኩል ያለባቸውን ጉድለትም በአለመገንዘብና የመምህሩን የእርማት ጫና ለመቀነስ የክሂሎችን መዳበር ማዳከምም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተጨማሪ መንስኤ ነው፡፡ (ይህም በቃለ መጠይቁ ውጤት ከተዘረዘው የመጽሐፉ ሞዴል ቃላዊ አቀራረብ አለመሆን ጋር ምክንያት የሚዛመድ በመሆኑ በመምህራኑ ምስክርነት በክፍል ውስጥ ያሳደረው አሉታዊ ተጽእኖ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ

ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት መልመጃዎች አቀራረብ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ደካማ ጐኖች ቢያስወግድ ቃላትን መማርን ሊያስተምር እንደሚችል በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

## 5.3 የመፍትሄ ሀሣብ

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ወደፊት ለሚዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍም ሆነ ለሌሎች ተከታታይ መጻህፍት መነሻ እንዲሆኑ የሚከተሉት አስተያየቶች /መፍትሄ ሃሳቦች/ በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

1. በቃላዊ ርዕዮት /Lexical approach/ ላይ የተመሠረተ የመፃህፍት ዝግጅትን መጠቀም፡፡
   - 1.1 ከማይጨበጠው ከቋንቋ ይልቅ ቋንቋ ለሚወክለው ለቃላት ይበልጥ ትኩረት በመስጠት ተማሪዎች ቃላትን ማወቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነና በነርሱም ሙሉ በሙሉ መጠቀምን እንዲለምዱ፣
   - 1.2 በሰብአዊ ባህሪ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በፓለቲካዊ፣ በሳይንሳዊና ወዘተ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ለምሳሌ እንደ ጤና፣ ስራ፣ አለባበስ፣ ልዩ ልዩ ግንኙነቶች፣ ወዘተ ከመሳሰሉ በዙሪያቸው አዳዲስ ቃላትን ሊያሰባስቡ ከሚችሉ ውሱን ርዕሶች ጋር የተያያዙ ቃላትን ትኩረት እንዲሰጧቸው ለማድረግና ለማለማመድ
   - 1.3 ተማሪዎችን የሚያነሳሳ፣ ስለ አማርኛ ቃላትና ባጠቃላይም ቋንቋ እንዴት እንደሚሰራ እንዲገነዘቡ የሚያደርግ
   - 1.4 አጠቃላይ ክሂልን በቃላት ትምህርት አቀናጅነት የሚያሳድግ፣ በቋንቋ ገፅታዎች ውህደታዊ ትምህርትና ሌሎች የቋንቋ አይነቶችንም የሚያቀርብ መማሪያ መጸሀፍ ማዘጋጀት ከላየ የጠቀስናቸውን ችግሮች የሚቀርፍ እንደሆነ ይታመናል /ሀርመርና ሮዝነር፣ 1991፡1 / ፡፡

2. “እየተሳተፋችሁ፣ እያጠናችሁና እየተገበራችሁ ግልጋሎታዊና የቃላት ሚዛናዊ ገፅታዎችን በማሰስ ቃላትን መማርን ተማሩ” በሚለው መርሀ ላይ ተመስርቶ መማሪያ መጽሐፉን በዚህ ጥናት አባሪ “ረ” ነጥቦች መሠረት ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ አካሄድ ለአሰሳ ከሚረዱ የቃላት ዘርፎችና ይዘቶች በተጨማሪ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ሰንጠረዥ 2-6 በተግባር ላይ የዋሉትን መመልከት ይቻላል፡፡

3. የቃላት ፍቺን ያለ መዝገበ-ቃላትና ያለ ሌሎች ሰዎች እርዳታ በራስ ጥረት፣ በቃላት ቅንጅት፣ በቋንቋ ድግግሞሻዊ ባህሪና በሌሎች ልዩ ለዩ ጥቆማዎች አማካኝነት ለመማር የሚያስችለውን አውዳዊ ነሲብ ስራ/contextual guess work/ ስልትን በመማሪያ መጽሀፍ

ውስጥ በማካተት ተማሪዎች ቃላትን መማርን እንዲማሩ የሚያደርገውን የቃላት ክሂል ማስጨበጥ፡፡

4. ተማሪዎች በፈጠራ ቃላትን የሚጠቀሙበትን መንገድ መጽሐፉ ውስጥ ማካተት ለምሳሌ በምስረታ አማካኝነት ሲባሉ ለሌሎች ሊገቡ የሚችሉ ግን ቀደም ብለው በሌላ ሰው ያልተባሉ አዳዲስ ቃላትን መፍጠር፣ ሐረጉችንም በስነፅሁፋዊ ውበታቸው ፈጥረው እንዲጠቀሙባቸው የሚያደርጉ የቃላት ግጥሚያ ልምምዶችን እንዲያደርጉ የሚያነሳሱ፣ አዳዲስ ቃላቱ እንዴት እንደተፈጠሩና ታሪካዊ አመጣጣቸው ምን እንደሆነ የሚያሳውቁ፣ ወዘተ... ጉዳዮችን ስለቃላት እንዲያውቁ በማድረግ ተማሪዎች ቃላትን መማርን እንዲማሩ ማድረግ ችግሩን ሊያስወግድ እንደሚችል በአጥኝውና አጥኚው በክለሳ ድርሳናት ክፍል በጠቀሳቸው በብዙዎቹ ምሁራን ይታመናል፡፡

# ዋቢዎች (BIBLIOGRAPHY)


Asfaw Melaku and Simon Murison-Baulie. 1976, "Language Teaching Materials," in Bender, M.L. and et al. (eds.) *Language in Ethiopia.* London: oxford University press

Berhane Dessie 1988. *An Evaluation of Modern vocabulary Teaching Methods and The Extent To which These are Implemented In Fresh-man English Courses.* Addis-Ababa University: School of graduate Studies

Bright, J.A. and Mc Gregor. G.P. 1978. *Teaching as a Second Language.* London: Longman Group Ltd.

Carnu, Annie Marie. 1978. "The First Step in Vocabulary Teaching." *The Modern Language Journal.* Montreal: pp. 262 - 272.

Carter, R. and M. Mc Carthy, eds. 1988. *Vocabulary and Language Teaching.* New York: Longman Group(UK) Ltd.

Davis, F.B. 1983. *Fundamental Factors of comprehensive in Reading.* In L.M. Genfile, M.L. Kanil, J.S. Blanchard

Crystal, David. 1991. *A Dictionary of Lingustics and Phonetics.* Cambrige Blackwell Pulic.

Frisby, A.W. 1957. *Teaching English.* London: Robert Maclehose and company Ltd.

Gairns, R. and S. Redman. 1986. *Working with words: A Guide to Teaching and Learning Vocabular.* Cambridge: Cambridge University press.

Gareuet, F. 1981. *Developing reading skills.* A practical Guide to Reading comprehension excercise. Cambridge University Press.

Goodlad,John I. 1966. *School, Curriculum and the Individual.* Toronto: Blaisde II publishing company.

Hailu Alemu. 1994. *High School teachers Attitudes Towards an Awareness-Raising Approach to Vocabulary Teaching.* Addis Ababa University: School of graduate studies.

Harmer, J. and R. Rossner. 1991. *More than Words: Vocabulary for Upper Intermediate to Advanced Student.* ESSEX: Longman Group (UK) Ltd.

Mekonnen Hundie. 1984. *Evaluation of The Underlined English Vocabulary Items. In The "English For New Ethiopia" Series for Grades 9 to 12.* Addis Ababa University: School of Graduate Studies.

Knight, George R. 1980. *Philosophy and Education.* Michigan S: University Press.

Lado, Robbert 1955. "Patterns of Difficulty in Vocabulary." *Language Learning.* Vol. VI No. 142 pp.23 - 45.

_____________.1964. *Language Teaching. A Scientific Approach,* New York, MC Graw - Hill, Inc.

Mackey, William Francis 1965. *Language Teaching Analysis.* London: Longmans, Green and Co. Ltd.

Martin Marilyn. 1984. "Advanced Vocabulary Teaching": The Problem of Synonyms, *Modern Language Journal.* Pp. 130 - 137.

Mc. Carthy M. 1990. *Vocabulary.* Oxford: Oxford University press.

Tesfay Mehzentu. 1990. *An Evaluation of the Effectiveness of Current Techniques. In Vocabulary Teaching to Grade four Student.* Addis Ababa University: School of Graduate Studies.

Meara, Paul. 1982."Vocabulary Acquisition: A Neglected Aspect of Language Learning", *Surreys l.* London: Cambridge University Press.

Mezynski Karen. 1983. " Issues Concerning the Acquisition of Knowledge: Effects of Vocabulary Training on Reading Comprehension" *Review of Educational Research.* Vol. 53 No. 2, pp. 253 - 279.

Morgan, J. and M. Rinvolucri. 1986. *Vocabulary.* Oxford: Oxford University press.

Murray, Donald. 1982. *Learning by Teaching: Selected Articles, Writing and Teaching.* Portsmouth: Heineman Educational Books, Inc. pp. 3,4,8,15 - 21, 77, 140 142.

Nuttall, C., 1982. *Teaching Reading Skills in a Foreign Language.* London: Heinemann Educational Books.

Pratte, Richard. 1971. *Contemporary Theories of Education,* Toronto: Intent Educational publishers.

Richards, J. C. 1987. *The Context of Language Teaching,* New York: Cambridge University press.

Rudzka, J. et al. 1985. *More words you need (Teacher's Book).* London: Macmillan publishers Ltd.

Smith, Stephenson S. 1952. *How to Double Your Vocabulary (3rd ed.).* New York: Thomas Y. Crowell company.

Tayler, L. 1990. *Teaching and Learning Vocabulary.* New York: Prentice Hall International (UK) Ltd.

Wallace, M. J. 1982. *Teaching Vocabulary.* London: Heinemann Educational Books Ltd.

Wilkins, D.A. 1972. *Linguistics in Language Teaching,* London: Edward Arnold (Publishers) Ltd.

_____________.1978. *Linguistics in Language Teaching.* London: The English Language Book Society and Edward Arnold ( publishers) Ltd.,

William E. 1954. *Reading in the Language Classroom*. London : ME Millan Publishing Ltd.

ሀብተማርያም ወርቅነህ፡፡ 1963፡፡ *የቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት፡፡* አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም፡ ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

ህላዊ ገ/እግዚአብሔር፡፡ 1960፡፡ *ማለፊያና መግቢያ 2ኛ መፅሀፍ፡፡* አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

መስፍን ልሳኑ፡፡ 1949፡፡ *የአማርኛ መፅሔት ቃላት፡፡* አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ሰለሞን ግዛው፡፡ 1978፡፡ *"የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍት ግምገማ"፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ (ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡)

የሥርዓተ ትምህርት ዋና ክፍል፡፡ 1984፡፡ *የ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ ፡፡* አዲስ አበባ ፣ ት.መ.ማ.ማ ድርጅት፡፡

በክሬ ጌታ፡፡ 1975፡፡ *"የአማርኛ ቋንቋ ይዘት በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች"*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ /የዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ/፡፡

በየነ ማሞ፡፡ 1985፡፡ *"በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የቋንቋ ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው"*፡፡ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ማስተርስ ዲግሪ /አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት /ያልታተመ/፡፡

ተ/ማርያም ፈንታዬ፡፡ 1970፡፡ *ኖንተ ጥበብ ዘስነ-ፅሑፍ፡፡* አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ ትምህርት ሚኒስቴር 1970 ፡፡

ትንሣኤ ብርሃኔ፡፡ 1988፡፡ *"የአማርኛ ቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት"፡፡* /የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት ማስተርስ ዲግሪ/ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት /ያልታተመ/፡፡

አምሣሉ አክሊሉና ደምሴ ማናህሎት፡፡ 1982፡፡ *ጥሩ ያማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው?*፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

አምባዬ ፀሃዬ፡፡ 1987፡፡ "የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የቋንቋ ትምህርቶች በፓሊሲው አቅጣጫ እንዴት ይዘጋጃሉ?" *መፅሔተ ትምህርት፡፡* ቅፅ 1 ቁጥር 1 ፡፡

አስፋው አመና፡፡ 1975፡፡ *"የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ በሁለት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች"*፡፡ /የዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ/፡፡

አያሌው አስፋው፡፡ 1985፡፡ *"ከ1933 - 1983 ዓ.ም ባሉት አመታት ውስጥ በአገልግሎት የዋሉ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ዝርዝር አይነትና የይዘት ግምገማ"*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ለዲግሪ ሚሟያ የቀረበ፡፡

ደሴ ሙሉአለም፡፡ 1972፡፡ *"ቋንቋና ትምህርት በኢትዮጵያ"*፡፡ /ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ /ያልታተመ/፡፡

ዳኛቸው ወርቁ፡፡ 1977፡፡ *የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ፡፡* አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጌታቸው አዱኛ፡፡ 1986፡፡ *"ለአሥረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ"፡፡* ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ት/ቤት የቀረበ ጥናት /ቴሲስ/፡፡

## አባሪ ሀ

## ለ 9ኛ ክፍል መምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናትና ተቋም
የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት
አማርኛ በማስተማር ዘዴ
M.A. ኘሮግራም

መግቢያ

የተከበሩ ውድ መምህር

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ አማርኛን በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ በሀገራችን በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ለማስተማር በ1984 ዓ.ም ታትሞ እስከአሁን በስራ ላይ በአለው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርትን አቀራረብ ተገቢነት በመፈተሽ ለሚደረገው ጥናትና ምርምር አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው፡፡ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው በእርስዎ ቀና ትብብር ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ ሲቻል በመሆኑ የቀረበው መጠይቅ በጥሞና ተመልክተው በሚያውቁትና በሚገነዘቡት ሁኔታ አስተማማኝ ምላሽ እንዲሰጡኝ ስጠይቅ ቀና ትብብምዎ እንደማይለየኝ በመአማመን ነው፡፡

በተጨማሪም የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥናትና ምርምር ጉዳይ ብቻ የሚውል መሆኑን በትህትና አረጋግጣለሁ፡፡

ክፍል አንድ

የግል ሁኔታን በተመለከተ

እባክዎ በሚመለከትዎ ላይ የ ☒ ምልክት በማድረግ ተገቢውን መረጃ ይጻፉ እንደ አስፈላጊነቱም በክፍት ቦታዎች ላይ ይሙሉ (አስተያየትዎን ይጻፉ)

1.1 የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም

1.1.1 ከፍተኛ 4 ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ☐
1.1.2 አብዩት ቅርስ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ☐
1.1.3 ደጃዝማች ወንድራድ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ☐
1.1.4 ዳግማዊ ሚኒሊክ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ☐
1.1.5 አቃቂ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ☐
1.1.6 ጥቁር አንበሳ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ☐

1.2 የትምህርት ደረጃዎ

1.2.1 12 + 1 --------------------------- ☐
1.2.2 12 + 2 (ዲፕሎማ)------------------ ☐
1.2.3 12 + 3 --------------------------- ☐
1.2.4 B. A. -------------------------------- ☐
1.2.5 M. A. -------------------------------- ☐

1.3 የሰለጠኑበት አብይ ትምህርት

1.3.1 አማርኛ ---------------------------- ☐
1.3.2 እንግሊዘኛ ------------------------- ☐
1.3.3 ስነ ልሣን -------------------------- ☐
1.3.4 ሌላ ካለ ይግለጹ _______________

1.4 የሠለጠኑበት ንዑስ ትምህርት

1.4.1 እንግሊዘኛ-------------------------- ☐
1.4.2 አማርኛ -------------------------- ☐
1.4.3 ስነ ልሣን -------------------------- ☐
1.4.4 ሌላ ካለ ይግለጹ _______________

1.5 ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ አማርኛን ያስተማሩባቸው የክፍል ደረጃዎች

1.5.1 9ኛ ክፍል
1.5.2 10ኛ ክፍል ☐
1.5.3 11ኛ ክፍል ☐
1.5.4 12ኛ ክፍል ☐

1.6 በያዝነው የትምህርት ዘመን የሚያስተምሩባቸው የክፍል ደረጃዎች

1.6.1 9ኛ ክፍል ☐
1.6.2 10ኛ ክፍል ☐
1.6.3 11ኛ ክፍል ☐
1.6.4 12ኛ ክፍል ☐

1.7 ከ1985 ዓ.ም ወዲህ በስራ ላይ የዋለውን የ9ኛ ክፍል አማርኛ ማስተማሪያ መፅሐፍ በመጠቀም አማርኛን ያስተማሩባቸው አመታት ብዛት

1.7.1 አንድ አመት ---------- ☐
1.7.2 ሁለት አመት ---------- ☐
1.7.3 ሦስት አመት ---------- ☐
1.7.4 አራት አመት ---------- ☐
1.7.5 አምስት አመት---------- ☐

1.8 በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛን ያስተማሩባቸው አመታት ብዛት

| | | |
|---|---|---|
| 1.8.1 | ከ1-5 ---------- | ☐ |
| 1.8.2 | ከ6-10 ---------- | ☐ |
| 1.8.3 | ከ11-15 ---------- | ☐ |
| 1.8.4 | ከ16-20 ---------- | ☐ |
| 1.8.5 | ከ21-25 ---------- | ☐ |
| 1.8.6 | ከ26-30 ---------- | ☐ |
| 1.8.7 | ከ30 ዓመት በላይ ------ | ☐ |

## ክፍል ሁለት

### የአዳዲስ ቃላት ማስተማሪያ ስልቶችን በተመለከተ

2.1 ከሚከተሉት የመማሪያ መፅሐፉ ክንውኖች ውስጥ የትኞቹ በምን ያህል ደረጃ ለአዳዲስ ቃላት ማስተማሪያነት እጥቅም ላይ ያውላሉ? በየስልቱ ጎን የተዘረዘሩት ቁጥሮች ስልቶች የሚገኙባቸው የመማሪያ መጽሐፉ ገፆች ስለሆኑ ለማመሳከሪያነት በተፈለገው ጊዜ መመልከት ይችላል፡፡

| ስልት | ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ሁልጊዜ እጠቀምበታለሁ | በመጠኑ እጠቀምበታለሁ | አልፎ አልፎ እጠቀምበታለሁ | ጭራሽ እልጠቀምበት ም |
| ሀ. በማጥበቅና በማላላት የቃላት የተለያዩ ትርጉሞችን መመርመር | | | | |
| ለ.. የተለያዩ ቅጥያዎች ለይቶ ማመልከት | | | | |
| ሐ. በአናባቢና በተነባበ ድምፆች የሚጨርሱቃላትን መለየት | | | | |
| መ. የስም ገላጮችን ለይቶ ማውጣት | | | | |
| ሠ. የቃልትን የንግግር ክፍሎች ለይቶ ማውጣት | | | | |
| ረ. በአርባታ ስያሜ መስጠት | | | | |
| ሰ በምንባቡ ፍቺ መሠረት ዐረፍተ ነገር መስራት | | | | |
| ሸ. በምንባእኡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሠረት ፍቺ መስጠት | | | | |
| ቀ. ለተሠጡ የመግለጫምዎች ዝርዝር ሊቆምሙየሚችሉ ስሞችን መናገርና በግልባጭም ለስሞች ዝርዝር መገለጫ መስጠት | | | | |
| በ. ከአንድ በላይ ፍቾዎችን መስጠት | | | | |
| ተ. ተመሣሣይ ቃላት መስጠት | | | | |
| ቸ. ተቃራሪ ቃላት መስጠት | | | | |
| ኋ. በማዛመድ መተርጎም | | | | |
| ነ. በጥንድ ቃላት መሓል የሚገኝን | | | | |

| ስልት | ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ሁልጊዜ እጠቀምበታለሁ | በመጠኑ እጠቀምበታለሁ | አልፎ አልፎ እጠቀምበታለሁ | ጭራሽ አልጠቀምበትም |
| የትርጉም ልዩነት ማመልከት | | | | |
| ኘ. በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተሰመረባቸው ቃላት ሑአግባባቸው መሰረት ትርጉም መምረጥ | | | | |
| አ. በምንባብ ውስጥ ቃላቱ በዘይቤነት የሚወክሉትን መጠቆም | | | | |
| ከ. በምንባቡ ሓረግን የሚተካ ቃል መምረጥ | | | | |

2.2. በክፍል ውስጥ ከንውን ከሚከተሉት የቃላት ይዘቶች በየትኞቹ ላይ በምን ያህል ደረጃ ያተኩራሉ?

| ይዘት | ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በከፍተኛ ደረጃ አተጁርበታለሁ | በመካከለኛ ደረጃ አተኩርበታለሁ | በዝቅተኛ ደረጃ አተጁርበታለአሁ | በፍጹም ትኩረት አልሰጥም |
| ሀ. የትርጉም ዝምድናዎች (Seense Relations) | | | | |
| ለ. ተረትና ምሣሌዎች ( Proverbs ) | | | | |
| ሐ. የቃላት አብሮነቶች (Collections) | | | | |
| መ. አባባሎች (Expressions) | | | | |
| ሠ. ምሳያዎች (analogies) | | | | |
| ረ. ጥመራዎች (Compoundings) | | | | |
| ሰ. መደሑኛ ቃላት(Formal Words) | | | | |
| ሸ. ኢመደበኛ ቃላት (Informal Words) | | | | |
| ቀ. ሞያ ነክ ቃላት (Technical Words) | | | | |
| በ. በተማሯቸው አዳዲስ ቃላት ታሪክ እንዲናገሩ ርዕስ እንዲሰጡ፣ በተሰጡ ርዕሶች ላይ ትንታኔ እንዲይደርጉ ማድረግ | | | | |

## ክፍል ሦስት

የቃላት መልመጃዎቹን አሰራር በሚመለከት

ከዚህ በታች በቀረበው የመጠይቁ ክፍል ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛ ሆኖ ባገኙት ስር የ ምልክት በማድረግ ተገቢውን መረጃ ይጻፉ

3.1. መልመጃዎቹን የሚያርመው ማን ነው?

3.1.1. እኔ (የክፍሉ የአማርኛ መምህር) ------------------------------

3.1.2. መልመጃዎቹን የሠሩት ተማሪዎች ራሳቸው በግል -------------

3.1.3. አንዱ የሌላውን ስራ እየተለዋወጡ በግል ----------------------

3.1.4. በቡድን ተደራጅተው የእያንዳንዱን ተማሪ በየተራ በቡድን -----

3.1.5. ሁለት ሁለት እየሆኑ የሁለቱንም በጋራ -----------------------

3.1.6. ሌላ መንገድ የሚጠቀሙ ከሆነ ይግለጹ?------------------------

3.2 የቃላት መልመጃቹ በክፍል ውስጥ በምን መልክ ይሰራሉ?

3.2.1 በተናጠል በግለሰብ ደረጃ ------- ☐

3.2.2 በጥንድ ------------------------- ☐

3.2.3 በቡድን ------------------------- ☐

3.2.4 በጥንድና በቡድን---------------- ☐

3.2.5 በጥንድና በግል------------------ ☐

3.2.6 በግልና በቡድን --------------- ☐

3.2.7 በሁሉም ---------------------- ☐

3.2.8 ሌላ ካለ ቢገልጹ ---------------- ☐

3.3 የቃላት መልመጃዎቹ በጽሁፍ በምን ያህል ደረጃ ይቀርባሉ?

3.3.1 በከፍተኛ ደረጃ ይቀርባሉ ------------------

3.3.2 በመካከለኛ ደረጃ ይቀርባሉ -----------------

3.3.3 በዝቅተኛ ደረጃ ይቀርባሉ -------------------

3.3.4 በፍጹም አይቀርቡም --------------------

3.4 የቃላት መልመጃዎቹ በቃል በምን ያህል ደረጃ ይቀርባሉ?

3.4.1 በከፍተኛ ደረጃ ይቀርባሉ ---------------

3.4.2 በመካከለኛ ደረጃ ይቀርባሉ -------------

3.4.3 በዝቅተኛ ደረጃ ይቀርባሉ ------------------

3.4.4 በፍጹም አይቀርቡም ------------------

## ክፍል አራት

የመማሪያ መጽሀፉ የቃላት መልመጃዎች በተማሪዎች የባህሪ ለውጥ ላይ የሚኖራቸውን ድርሻ በሚመለከት

ከዚህ በታች የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች አራት አራት መመዘኛ አማራጮች አሏቸው፡፡ ለየርዕሰ ጉዳዩ ተገቢ ሊሆን በሚችለው በአንዱ አማራጭ መመዘኛ ስርየ X ምልክት በማድረግ አስተያየቶዎን ይግለጹ፡፡

| ተ.ቁ. | አርዕስተ ጉዳይ | መመዘኛ ምርጫ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ጥሩ | ጥሩ | ደካማ | በጣም ደካማ |
| 4.1 | ተማሪዎቹ ይሚሰጧቸውን የቃላት መልመጃው ለመስራት ያላቸው ፍላጎት | | | | |
| 4.2 | ተማሪዎቹ የቃላት መልመጃዎቹን ከሠሩ በኋላ ለማሣረም ያላቸው ፍላጎት | | | | |
| 4.3 | ተማሪዎቹ የቃላት መልመጃዎቹን መሠረት በማድርግ ጥያቄዎችን የማቅረብ ጉጉት | | | | |
| 4.4 | የቃላት መልመጃዎቹ የተመሠረቱባቸውን ምንባቦች አንብቦ የመረዳት የተማሪዎች ችሎታ | | | | |
| 4.5 | የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የጽህፈት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው አስትተዋጽኦ | | | | |
| 4.6 | የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የማዳመጥ ችሎታ ለምዳበር ያላቸው አስተዋጽኦ | | | | |
| 4.7 | የቃላት መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ያላቸው አስተዋጽኦ | | | | |
| 4.8 | የቃላት መልመጃዎቹ የስነ ጽሁፍ ችሎታን ለማድበር የምማያበረክቱት አስተዋጽኦ | | | | |
| 4.9 | የቃላት መልመጃዎቹ የስነ መዋቅር ችሎታን የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ | | | | |

ክፍል አምስት

## ጠቅላላ አስተያየት

በሚያስተምሩበት ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት መልመጃዎቹን አቀራረብ በሚመለከት ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት ይዘርዝሩ

______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
____________________________________

## አባሪ ለ

# ለፌድራሉ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም
# የቋንቋ ቡድን መሪ የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

መግቢያ

የተከበሩ የቋንቋ ቡድን መሪ

የዚህ ቃለ - መጠይቅ ዋና ዓላማ በ1984 በመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ አሁንም እየተሰራበት ያለውን የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት አቀራረብ ለመመርመር በሚደረገው ጥናት አጋዥ የሚሆኑ መረጃወችን መሠብሠብ ነው፡፡ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው የእርስዎ ቀና ትብብር ሲታከልበት በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና ተመልክተው በሚያመቸዎ ቀጠሮ ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጡኝ ስጠይቅ የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥናትና ምርምር ጉዳይ ብቻ የሚውል መሆኑን በትህትና አረጋግጥለዎታለሁ፡፡

አመሰግናለሁ፡፡

ቃለ መጠይቅ

የትምህርት ደረጃዎ____________________

አጠቃላይ የአገልግሎት ዘመንዎ ____________________

በመምህርነት ____________________

በርዕሰ መምህርነት ____________________

በትምህርት ባለሞያነት ____________________

አሁን ያሉበት የስራ ክፍል ____________________

በክፍሉ ያለዎት የሥራ ድርሻ ____________________

መሪ ጥያቄዎች

1. ለመጀመሪያ ጊዜ በ1984 ዓ.ም ታትሞ እስካሁን በመደበኛ 2ኛ ደረጃ ትምህረት ቤቶች በስራ ላይ ያለውን የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ሒደት በተመለከተ፡-

    ሀ. በዝግጅቱ የተሳተፉት ሰዎች ከምን ከምን ክፍል የተውጣጡ ነበሩ?

ለ. ግለሰቦቹ የተመረጡባቸው መመዘኛዎች ምን ምን ነበሩ?

ሐ. የአዘጋጂዎቹን የትምህረት ደረጃና የስራ ልምድ ቢገልጹልኝ?

2. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከሌሎች የቋንቋ ገጽታዎች ጋር ሲወዳደር በተለይ ለቃላት የተሰጠው ቦታ ምን ይመስላል?

3. በዚሁ መጽሐፍ መልመጃ ሁለት ላይ ያሉትን የቃላት መልመጃዎችና በሌሎች ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ባላቸው መልመጃዎች ላይ ከትምህርት ባለሞያዎች ከመስክ ተግባራት በመልሶ ምገባ /Feed Back/መልክ ለቋንቋ ቡድኑ የቀረቡ አስተያየቶች ካሉ ቢገልጹልኝ?

4. የመጸሐፉ ምንባብ አመራረጥ ምንን መሠረት ያደረገ ነው? ይህስ ለቃላት አመራረጡ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አለ?

5. መጽሀፉ የቃላትን ልዩ ልዩ ባህሪያት ለተማሪዎች ከማስገንዘብ አኳያ ምን ያህል እገዛ ያደርጋል ይላሉ?በዚህ በኩል ይጐድለዋል የሚሉት ባህሪ ካለ ቢገልጹልኝ?

6. ከ1985 ዓ.ም በፊት ይሰራበት ከነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ይሔኛው በተለየ ቃላትን አስመልክቶ ካለው ድክመትና ጥንካሬ የተወሰነውን ቢጠቅሱልኝ?

7. በአዲስ መልክ በ1989 ዓ.ም የተሻሻለውና በአዲስ አበባ ገና በስራ ላይ ያልዋለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አሁን እየተሰራበት ካለው የተሻለ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ያለው ይመስለዎታል? የተሻለ ነው የሚሉ ከሆነ ካለፈው እትም ድክመቶች መሀል ያሻሻላቸውን በመጠኑ ቢጠቅሱልኝ?

አመሰግናለሁ፡፡

# አባሪ ሐ

## በ1984 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመውን የ 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላዘጋጁ የትምህርት ባለሙያ የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

### መግቢያ

የተከበሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ አዘጋጅ

የዚህ ቃለ-መጠይቅ ዋና ዓላማ በ1984 በመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ አሁንም እየተሰራበት ያለውን የ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት አቀራረብ ለመመርመር በሚደረገው ጥናት አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን መሠብሠብ ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው የእርስዎ ቀና ትብብር ሲታከልበት በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና ተመልክተው ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጡኝ ስጠይቅ የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥናትና ምርምር ጉዳይ ብቻ የሚውል መሆኑን በትህትና አረጋግጥለዎታለሁ፡፡

አመሰግናለሁ፡፡

### ቃለ መጠይቅ

የትምህርት ደረጃዎ ____________________

አጠቃላይ የአገልግሎት ዘመንዎ ____________________

በመምህርነት፣ ____________________

በሌላ ቢጠቅሱልኝ፣ ____________________

የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ____________________

ዋና ትምህርት ____________________

ንዑስ ትምህርት ____________________

### መሪ ጥያቄዎች

1. በ1984 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመውንና በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች እስከ አሁን በስራ ላይ የለው የ9ኛ ክፍለ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ለማዘጋጀት እርስዎ እንዴት እንደተመረጡ ቢገልፁልኝ?

2. ለዚህ ስራ ከመመረጥዎ በፊት በመማሪያ መፅሀፍት ዝግጅት ልምድ ነበርዎት?
3. የመማርያ መፅሀፉ ዝግጅት ዋና አላማ ምን ነበር?
4. በመፅሀፉ ውስጥ ያሉት የቋንቋ ልዩ ልዩ ገፅታዎች የተመረጡት እንዴት ነበር?
5. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት የተመረጡበት መስፈርት ወይም መመሪያ ካለ ቢያብራሩልኝ?
6. ምንባቦቹስ እንዴት ተመረጡ?
7. ለቃላት ትምህርቱ አቀራረብ ቴክኒክና ስልት (Strategy)በምንጭነት የሚጠቀስ ሞዴል ካለ ወይንም በተማሪዎችና በመምህራን ሊታወቅ ይገባል የሚሉት ስርአታዊ አካሄድ (patern)ካለ ቢገልፁልኝ?
8. ተጨማሪ አስተያየት አለዎት?

## አባሪ መ

## የቋንቋ ቡድን መሪው ቃለ-መጠይቅ መልስ

ጥያቄ 1. ለመጀመሪያ ጊዜ በ1984 ዓ.ም ታትሞ እስካሁን በመደበኛ 2ኛ ደረጃ ትምህረት ቤቶች በስራ ላይ ያለውን የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ዝግጅት ሒደት በተመለከተ፡-

ሀ. በዝግጅቱ የተሳተፋት ሰዎች ከምን ከምን ክፍል የተውጣጡ ነበሩ

ለ. ግለሰቦቹ የተመረጡባቸው መመዘኛወች ምን ምን ነበሩ

ሐ. የአዘጋጂዎቹን የትምህርት ደረጃና የስራ ልመድ ቢገልፁልኝ

መልስ ሀ. ከመላው ኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ በተሰጣቸው ኮታ መሠረት የተወከሉ መምህራን ከትምህርት ቢሮ የትምህረት መርሀ- ግብር ባለሙያዎች ከአ.አ. ዩኒቨርስቲ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል መምህራን ፣ ከመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል መምህራን፣ ከትምህርት ሚኒስቴር ሱፐርቪዥን መምሪያ፣ ከባህል ሚኒስቴር አግባብነት ያላቸው ባለሙያዎች፣ ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ባለሙያ፣ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ባለሙያ

ለ. የትምህረት ደረጃቸው ቢ ኤ(B.A.) ሆኖ በአማርኛ ቋንቋ የሰለጠነ፣ የማስተማር ልምድ ያላቸው፣ የመማሪያ ማስተማሪያ መፃህፍትን ለማዘጋጀት ተሳትፎ ወይም ልምድ ያላቸው፣ በርእሰ-መምህርነት ወይምበሱፐርቫይዘርነት የሰለጠኑ የትምህርት ባለሙያዎችና የስርአተ-ትምህርት ባለሙያዎች ነበሩ፡፡

ሐ. ፒ ኤች ዲ(P.H.D)፣ ማስተር(M.A.)፣ ቢ ኤ(B.A.)፣ ዲፕሎማ(Diploma)፣

ጥያቀ 2. በዚህ መፅሀፍ ውስጥ ከሌሎች የቋንቋ ገፅታዎች ጋር ሲወዳደር በተለየ ለቃላት የተሰጠው ቦታ ምን ይመስላል?

መልስ፡ የቋንቋ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጠው ተማሪዎችን በተለያዩት የቋንቋ ክሂሎች ማለት በያንዳንዱ ዘርፍ በመነጣጠል ሳይሆን በሁሉም ተግባቦታዊ ክሂሎች የተመጣጠኑ ችሎታዎችን አጎልብተው በተግባራዊ

እንቅስቃሴያቸው እንዲጠቀሙበት ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህረት አላማዎች

1. ማዳመጥ ክሂልን ማዳበር፣
2. የመማር ክሂልን ማዳበር፣
3. የማንበብ ክሂልን ማዳበር፣
4. የመፃፍ ክሂልን ማዳበር፣
5. የስነ ልሳን ችሎታን ማጎልበት
6. የስነ ፅሁፍ ችሎታን ማጎልበት ናቸው፡፡

ስለሆነም አንዱን ካንዱ ነጥሎ የማጥናት ሂደት የለም፡፡ በተቻለ መጠን ሁሉንም በተጣጣመና በተቀናጀ መንገድ ለመማር ማስተማር ይበጃል ተብሎ የተዘጋጀ መፅሀፍ ነው፡፡ ይህ ሲባል ደግሞ መፅሀፍ ፊፅሞ የተዋጣለት ነው ማለት አይደለም፡፡ የስርአተ-ትምህርት ዝግጅት በሂደት የሚሻሻልና የሚለወጥ ስለሆነ፣ ባሁኑ ጊዜ ይህ የተባለው /በ1984 የተዘጋጀው/ የ9ኛ ክፍል የቋንቋው መማሪያ መፅሀፉ በ1989 ተሻሽሎ በቀረበው የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያ ከ1990 ጀምሮ ለሽግግር ዘመናት ስራ ላይ እንዲውል በመላው ሀገሪቱ ተሰራጭቷል፡፡ ስለዚህ ባሁኑ ጊዜ የፌደራሉ የስርአተ -ትምህርት ኢንስቲትዩት፣ የቋንቋው ቡድን የሚያውቀው በ1984 ታትሞ ሲያገለግል የቆየው የክፍሉ የመማሪያ መፅሀፍ በሌላ ጥራዝ እንደተተካ ነው፡፡

ጥያቀ 3. በዚሁ መጽሀፍ መልመጃ ሁለት ላይ የሉትን የቃላት መልመጃዎችና በሌሎች ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ባላቸው መልመጃዎች ላይ ከትምህርት ባለሙያዎች ከመሰክ ተግባራት በመልሶ-ምገባ /feed back/መልክ ለቡድኑ የቀረቡ አስተያየቶች ካሉ ቢገልጹልኝ?

መልስ ከላይ በተ.ቁ2 እንደተገለፀው መፅሃፉ ያለበትን ደካማነት በመገንዘብ ነው እንዲሻሻል ተደርጎ በሌላ የተተካው፡፡ ይህም የሆነው ቡድኑ ከመስክ ባገኘው በመልሶ-ምገባ /feed back/ከባለሞያዎች በተሰጡ አስያየቶችና፣ ከአውደ-ጥናት በተገኙ ነጥቦችና የትምህርት ፓሊሲውንም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

ጥያቄ 4. የመፅሐፉ ምንባብ አመራረጥ ምንን መሠረት ያደረገ ነው? ይህስ ለቃላት አመራረጡ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ አለ?

መልስ መፅሐፉ በአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በጋራ ሲዘጋጅ ምንባቦች ለመሳሪያነት ሲመረጡ ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነበር

ሀ. የክፍሉን ተማሪዎች ደረጃ ከመመጠን አንፃር

ለ. ከተማሪዎች ማህበራዊ አውድ ጋር የሚጣጣሙ ይዘቶችን ከማካተት አኳያ፣

ሐ. ከዘላቂነት አኳያ፣

መ. የተሟላ መልእክት ከማስተላለፍ ሁኔታ አንፃር፣

ሠ. የቋንቋ ጥያቄዎችን ለማውጣት ካላቸው አመቺነት አንፃር፣

ረ. ከማሳሰብ፣ ከማመራመር ወዘተ አኳያ፣

ሰ. ተግባራዊ ከመሆን አኳያ፣

ሸ. ከማራኪነት፣ ከኪነ ውበት አቀራረብ፣ ሳቢነት አንፃር፣ ወዘተ...

ጥያቄ 5. መፅሀፉ የቃላትን ልዩ ልዩ ባህሪያት ለተማሪዎች ከማስገንዘብ አኳያ ምን ያህል እገዛ ያደርጋል ይላሉ?በዚህ በኩል ይጐድለዋል የሚሉት ካለ ቢገልፁልኝ?

መልስ የነበረው መፅሀፍ ቃላትን ብቻ በተለይ ባዘነበለ መንገድ የሚያስተምር ነው ማለት አይቻልም፡፡ ከላይ በተ.ቁ 2. ለማመልከት እንደተሞከረው፣ ሁሉንም በተቀናጀና በተመጣጠነ መንገድ ለማስተማር ይረዳል ተብሎ የቀረበ ነበር፡፡ አሁን ግን በሌላ ተተክቷል፡፡

ጥያቄ 6. ከ1985 ዓ.ም በፊት ይሰራበት ከነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ይሔኛው በተለይ ቃላትን አስመልክቶ ካለው ጥንካሬና ድክመት የተወሰነውን ቢጠቅሱልኝ?

መልስ ከ1985 በፊት የነበረው የክፍሉና የሌሎችም ክፍሎች የቋንቋው መማሪያ መጻህፍት በብዙ መንገድ ችግሮች ነበሩባቸው፡፡ የቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ሳይሆኑ የጊዜው የፓለቲካ ትምህርት ማስተማሪያ መሳሪያዎች ነበሩ ማለት ይቀላል፡፡ ስለነበሩም ትምህርቱን ተማሪዎች ይጠሉት ነበር፣ መምህሩም በመፅሃፉ ውስጥ የሰፈሩትን ሀሣቦች በሚያስተምሩበት ሂደት ብዙ ፈተናዎችን እየተጋፈጡ ችግሮችም ደርሰውባቸዋል፡፡

ጥያቄ 7. በአዲስ መልክ በ1989 ዓ.ም የተሻሻለውና በአዲስ አበባ ገና በስራ ላይ ያልዋለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ አሁን እየተሰራበት ካለው የተሻለ

የቃላት ትምህርት አቀራረብ ያለው ይመስልዎታል? የተሻለ ነው የሚሉ ከሆነ ካለፈው እትም ድክመቶች መሀል ያሻሻላቸውን በመጠኑ ቢጠቅሱልኝ?

መልስ ለዚሁ ጥያቄ ይህንን ጥናት የሚያካሂደው ባለሙያ ቢፈትሸውና በተጨባጭ ሂሳዊ ግምገማውን ቢያቀረብ የሚሻል ይመስለኛል፡፡

## አባሪ ሠ

## የመጽሐፉ አዘጋጅ ባለሙያ ቃለ መጠይቅ መልስ

ጥያቄ 1. በ1984 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመውንና በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች እስከ አሁን በስራ ላይ የለውን የ9ኛ ክፍለ አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ለማዘጋጀት እርስዎ እንዴት እንደተመረጡ ቢገልፁልኝ?

መልስ ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ በሥርዓተ ትምህርት የአማርኛ ፓናል አባል ስለነበርኩ በዝግጅቱ ተሳትፌያለሁ፡፡

ጥያቄ 2. ለዚህ ስራ ከመመረጥዎ በፊት በመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት ልምድ ነበርዎት?

መልስ ለሙከራ ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ - 9ኛ ክፍል የመማሪያ ማስተማሪያ መፅሐፎችን በማዘጋጀት ልመድ ነበረኝ፡፡

ጥያቄ 3. የመማርያ መፅሀፉ ዘግጅት ዋና አላማ ምን ነበር?

መልስ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ትምህርት ዐላማዎች በመማሪያው መፅሐፉ መግቢያ ላይ ተጠቅሰዋል፡፡

1. ተማሪዎች ይበልጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ይኖራቸዋል፡፡
2. ተማሪዎች ይበልጥ ጥሩ የማንበብ ክሂል ያዳብራሉ፡፡
3. ተማሪዎች ይበልጥ ጥሩ የመፃፍ ክሂል ይማራሉ፡፡
4. ተማሪዎች ይበልጥ የሥነ ልሳን ዕውቀት የቀናጃሉ፡፡
5. ተማሪዎች ይበልጥ የሥነ ፅሁፍ ዕውቀት ያገኛሉ፡፡

ጥያቄ 4. በመፅሀፉ ውስጥ ያሉት የቋንቋ ልዩ ልዩ ገፅታዎች የተመረጡት እንዴት ነበር?

መልስ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪየ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት የቋንቋ ልዩ ልዩ ገፅታዎች /ይዘቶች/ የተመረጡት

1. ከ1ኛ 8ኛ ክፍል የሉትን የአማርኛ መማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍት ይዘቶች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አምዳዊ ግንኙነቶችንና ጎናዊ ግንኙነቶችን መሠረት በማድረግ፣
2. አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የሚያዳብሩ፣ ሰዋሰዋዊና ሥነ ፅሑፋዊ ዕ ውቀቶችን የሚያስገኙ ይዘቶች እንዲካተቱ በማድረግና

3. ተማሪዎች የቃላት፣ የፌሊጣዊ አነጋገሮች የዘይቤና የቅኔ ዕውቀት የሚያገኙባቸው ይዘቶች እንዲካተቱ በማድረግና
4. በትምህርቱ ሂደት ወቀት ይዘቶች የተሰጠውን የክፍለ ጊዜ ብዛት የሚሸፍኑ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተመርጠዋል

ጥያቄ 5. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት የተመረጡበት መስፈርት ወይም መመሪያ ካለ ቢያብራሩልኝ?

መልስ ቃላቶች የተመረጡባቸው መሥፈርቶች

1. ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል የተማሯቸውን ቃላት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት
2. የተማሯቸውን ለማስታወስና ለማጠናከር አዳዲስ ቃላትን እንዲያውቁ፣
3. ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚመጥኑ መሆናቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣
4. በመማሪያው መፅሐፍ ውስጥ በቅጥያ "ለ" ከተዘረዘሩት የንባብ መጻህፍት ካሉት ቃላት ለደረጃው የሚመጥኑትን ቃላት በመምረጥና
5. ከሌሎች ረዳት መፅሐፎች ለደረጃው የሚመጥኑትን ቃሎች በመምረጥ፣ ከመዝገበ ቃላት፣ ከሰዋሰው መጻህፍት፣ ከቅኔና ከዘይቤ መፅሀፎች ወዘተ፡፡

ጥያቄ 6. ምንባቦቹስ እንዴት ተመረጡ?

መልስ. ምንባቦች የተመረጡት

1. ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ያሉትን የምንባብ ይዘቶች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አምዳዊ ግንኙነታቸውንና ጎናዊ ግንኙነታቸውን መሠረት በማድረግ፣
2. የስድ-ፅሁፍና የግጥም ፅሑፍ ምንባቦች ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ መሆናቸውን በማጤን፣
3. የምንባቦችን መልዕክት፣ የአፃፃፍ ሥልት፣ የቃላት ሁኔታ፣ ሰዋሰዋዊ አካባቢ፣ ወዘተ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና ለክፍል ደረጃው የሚመጠኑ መሆናቸውን በማጥናትና
4. ምንባቦች በቡድን አባላት ተመርጠው አባላቱ አንብበውና ተወያይተውባቸው መርጠዋቸዋል እነዚሁ ምንባቦች ሲምፓዚየም ተዘጋጅቶ ከየ2ኛ ደረጃው የአማርኛ መምህራን፣ የዩኒቨርስቲ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች አጠቃላይ ዝግጅቱን ተችተውና አስተካክለው በወሰኑት መሠረት የተመረጡ ምንባቦች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ መማሪያ መፅሐፉ ከሞላ ጎደል ኅብረተሰቡ የተሳተፈበት ዝግጅት ነው፡፡

ጥያቄ 7. ለቃላት ትምህርቱ አቀራረብ ቴክኒክና ስልት (Strategy)በምንጭነት የሚጠቀስ ሞዴል ካለ ወይንም በተማሪዎችና በመምህራን ሊታወቅ ይገባል የሚሉት ስርአታዊ አካሄድ (pattern)ካለ ቢገልፁልኝ?

መልስ የቃላት ትምህርት አስተማሪዎችም ሆነ ተማሪዎች የሚጠቀሙበት ሥልት

1. የቃላትን ትርጉም ፈልጎና መርመሮ እንዲያውቅ በማስቻል ከዐ.ነገር ውስጥ ባላቸው የአገባብ ትርጉም፣ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ባላቸው ትርጉም በውስጣቸው በያዙት የትርጉም ብዛት፣ በቃሉ ውስጥ ድምፆች ሲጠብቁና ሲላሉ ባላቸው ትርጉም፣ ዕማሬአዊና ፍካሬያዊ ትርጉም፣

2. የቃሎችን ሰዋሰዋዊ አገባብ በማሳወቅ
   የስሞችን ጠባይ በማሳወቅ /ስሞችና ተውላጠ ስሞች/፣
   የግሦችን ጠባይ በማሳወቅ
   የአገባብ ቃሎችን ጠባይ በማሳወቅ /ቅፅል፣ ተውሳከ ግሥ፣ መስተዋድድና መስተፃምር/
   የቃለ አጋኖ ቃሎችን ጠባይ በማሳወቅ፣

3. የቃላትን አመሠራረት በማሳወቅ
   ነፃ ምዕላዶች፣
   ነፃ ምዕላዶችና ቅጥያዎች፣
   ድርብ ቃላት፣
   ቃላት ከሌላ ቃላት መመሠረት ወዘተ...

ጥያቄ 8. ተጨማሪ አስተያየት አለዎት?

መልስ በአጠቃላይ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ /በ1984 ዓ.ም የታተመው/ በመግቢያው ውስጥ የተጠቀሱትን አምስት ዓላማዎች ከግቡ የሚያደርሱ ይዘቶችን ያቀፈ ነው፡፡

በዝግጅቱ ወቅትም የሥርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና የትምህርት ባለሙያዎች የተሳተፉበት ነበር፡፡ በመሆኑም የኅብረተሰብ ተሳትፎ እንዳለበት አያጠራጥርም፡፡

አንድ ሥርዓተ-ትምህርት ተዘጋጅቶ ለተወሰነ ዘመን ካገለገለ በኋላ እንደሚለወጥ ይታመናል፡፡ በዚሁ መሠረት በ1984 የታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍም ይበልጥ ተሻሽሎ በጥራት እንደሚዘጋጅ እተማመናለሁ፡፡

## አባሪ ረ

# ከ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በናሙናነት የተወሰዱትን ምንባቦችና መልመጃዎች ለመገምገም የተዘጋጀ ዝርዝር መፈተሻ (Checklist)

1. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አጠቃላይ ዝግጅት የተመሰረተው ተማሪዎችን እያሰሱ ቃላትን መማርን እንዲማሩ በሚያደርግ ዘዴ ላይ ነው?

1.1. አሰሳው የቃላት ትርጉምን ለማካተት ይሞክራል?ማለትም መልመጃዎቹ ....

1.1.1. ከአማሪያዊ የቃላት ትርጉም ችሎታ አኳያ የቃላት መልመጃዎቹ በቃላቱና በተወከሉት ነገሮች፣ ሁኔታዎች፣ ድርጊቶችና ወዘተ... መሀል ያሉትን ብቸኛ ተተኳሪ ሀሳቦች በአውድ እያስለዩ የቃላቱን ግላዊ የትርጉም ውክልና አጉልተው ፍቻቸው ምን ማለት እንደሆነ በማሳወቅ በአሰሳ የመማር ስልትን ለማስጨበጥ ይሞክራሉ? (ሀርመርና ሮዝነር፣ 1991:III )

1.1.2. ፍካሬያውይና ሌሎች ከአንድ በላይ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በተመለከተ ሰፊ ወይም ጠባብ ሊሆኑ የሚችሉና በጊዜ ሂደት በመሰረታዊው የትርጉም ውክልና ላይ በተደራራቢነት የታከሉ የተለያዩ የቃላትን ከአንድ በላይ ትርጉሞች በማሳወቅ እራሳቸውን ችለው እያሰሱ እንዲማሩ የሚያስችሉ እገዛዎችን ለማድረግ ይሞክራሉ? (ታይለር፣ 1990፡2)

1.1.3. ተመሳሳይ፣ ተቃራኒና ተካትቶ በመባል የሚታወቁትን የትርጉም ዝምድናዎች በሚመለከት ቃላትን ለመተርጎም በሚያስችሉ ተዋልዷዊና ምክንያታዊ ግንኙነት ላይ በተመሰረቱና ትውስታን በሚያጠናክሩ ስነ ልቦናዊ ስልቶች ለመጠቆም ይሞክራሉ? (ሪቻርድስ፣ 1987 :179)

1.1.4. ከአውዳዊ የትርጉም ችሎታ ጋር በተገናኘ ቃላት በጥቃቅን ክፍሎች ለምሣሌ፡- እንደ ግኡዝ፣ ህያውና ሰብአዊ በሚል አከፋፈል ተከፍለው ትርጉማዊ ዋጋቸው በአውድ ሊለይ በሚችልበትና ትርጉም ጠቋሚ የቃላት ገጽታ ፍንጮችም በተገቢ ስርጭት የቀረቡበት ሁኔታ በቃላት መልመጃዎቹ ውስጥ እንዲካተቱ ተሞክሯል? (ሪቻርድስ፣ 1987 : 181)

1.2. አሰሳው የቃላት አጠቃቀምን እንዲያካትት ለማድረግ ተሞክሯል?

1.2.1. ከተለዋጮች፣ ፈሊጦች፣ ተረትና ምሳሌዎች፣ ምስያዎችና እውቀት አኳያ በዲስኩር ሞዴልነት አዋቂነት የሚለካው በንግግር በጽሁፍ ውስጥ ጥቅም ላይ በሚውሉት ቃላት መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ውሱን፣ ሰፊና ሁለንተናዊ አዛማጅ የትርጉም ውክልና ደረጃን ጠብቀው እያስለዩ የቃላትን አዛማጅ ትርጉም በማሳወቅ የቃላትን ሀይል ለመጠቀም በሚያስችል መልክ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማሳየት የሚሞክር በቂ ፍንጭ አለ? (ሪቻርድስ፣ 1987፡ 178)

1.2.2. ከመደበኛ፣ ኢ መደበኛና ሙያ ነክ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ አንፃር፣

1.2.2.1. ቃላቱ በንግግርም ሆነ በጽሁፍ በተግባር የሚውሉበትን ተዘውታሪነት መጠን፣

1.2.2.2. ቃላቱን ለመጠቀም የሚገድቡ ለምሳሌ እንደየቃላት እርጅናና ዘመናዊነት፣ መልክአ ምድራዊ ልዩነት፣ የንግግር የመግባቢያ መስክ (Field of discourse) ልዩነትና ማህበራዊ ሚናን ለመገንዘብ በሚያስችል መልክ በየትኛው አውድ? በማን? መቼ? እጥቅም ላይ እንደሚውሉ እያስለዩ የቃላቱን አጠቃቀማዊ ገጽታ ያሳውቃሉ? (ታይለር፣ 1990፡1 ፣ ሪቻርድስ፣ 1987፡177-178)

1.2.3. የቃላት አብሮነትን ከማሳወቅ አኳያ ለትምህርት የቀረቡት ቃላት ከተለያዩ የቃላት አይነቶች ጋር ያላቸውን የጎንዮሽ በጽሁፍ አቀማመጥ ከግራ ወደ ቀኝ ግንኙነት በአጠቃቀማዊ ባህርያቸው እያስለዩ የአሰሳውን ተግባር ለማጠናከር ይሞክራሉ? (ታይለር፣ 1990፡2 )

1.3. የቃላት መልመጃዎቹ በአሰሳ የቃላት ምስረታን ለማካተት ይሞክራሉ?

1.3.1. ቅጠላንና ጥመራን በተመለከተ ቀጣይ ምእላዶችን በመጠቀምና የተለያዩ ቃላትን በማጣመር የተፈጠሩ አዳዲስ ቃላትን በመመርመርና ከዚህ ቀደም ጥቅም ላይ ያልዋሉ ያልተሰሙና ቢሰሙ ትርጉማቸው አዲስ የማይሆን የቃላት ማእድንን አውጥቶ የመጠቀም ህግጋትን በስራ ላይ እያዋሉ የቃላት አመሰራረትን ለማሳወቅ ይሞክራሉ? (ሪቻርድስ ፣ 1987፡180)

1.3.2. ቅጠላዎችንና ፣ ጥመራዎችን፣ ሆህያትንና ድምጸችን ከማሳወቅ አንፃር በማጥበቅ፣ በማላላትና ወዘተ... የቃላት አፈጣጠርን ህግጋት በመጠቀም ታህታይ ቅርጸችንና ሌሎች የእርባታ ገጽታዎችን ሊያስለይ በሚችሉበት ሁኔታ የቃላት አመሰራረት እውቀትን ለማስጨበጥ ይሞክራሉ?

1.4. የቃላት መልመጃዎቹ የቃላት ሰዋሰውን በአሰሳ ለማስለየት ይሞክራሉ?

1.4.1. የንግግር ክፍሎች ስርጭት እውቀትን በተመለከተ የአዳዲስ ቃላትን አገባባዊ ቦታ በሚያስለይ መልክ እያቀረቡና ልዩ ልዩ ትርጉሞችን ፍንጭ በመጠቀም አውዳዊ ነሲብ ቴክኒክን በማጠናከር አሰሳውን ተግባራዊ ለማድረግ ይሞክራሉ? (ሪቻርድስ ፣ 1987፡179)

1.4.2. የቀጣይ ምእላዶችንና የቃላት ሙያዎችን ሰዋሰዋዊ ሚና በተመለከተ ከቃላቱ ጋር የተዛመዱ አወቃቀራዊ ባህሪያትን ለምሳሌ እንደተሳቢ መኖርና አለመኖርን፣ እንዲሁም ሙያ ነክ አመልካች ቅጥያዎችን ትርጉም ወዘተ... እያስለዩ ቃላትን

በሰዋሰዋዊ ባህሪ ገጽታቸው በማሳወቅ አሰሳውን ለማጎልበት ይሞክራሉ?

2. የመማሪያ መጽሐፉ ክንውኖች በስነ ትምህርታዊ አካሔድ ቅደም ተከተል ላይ የተመሠረቱ ናቸው? ማለትም መልመጃዎቹ ....

2.1. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተሳተፎ ክንውኖችን በየትምህርት ርዕሱ መነሻነት እንዲያካትቱ ተሞክሯል?

2.1.1. የንባብ ክንውንን በተመለከተ፣

2.1.1.1. መልመጃዎቹ መረጃ በመስጠት ቀጣይ ክንውኖችን ወደ ውይይት ወይንም ወደ ተግባር ለመምራት በመሞከር፣

2.1.1.2. የተማሪዎችን ስሜት ሊያነሳሳ፣ የተለያዩ አዳዲስ ቃላትን በዙሪያው ሊያሰባስብ በሚችል የርዕስ ስያሜና በራሱ በርእሰ ጉዳዩ ላይ በመምከር ተማሪዎችን እንዲወያዩ (እንዲተገብሩ) በመቀስቀስ ፣

2.1.1.3. ቀጥሎ መጠናት ያለባቸውን ቃላት ጽንሰ ሀሳቦች መሰረት በማስተዋወቅ፣

2.1.1.4. የቃላትን የክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች አቀናጅነት ሚና ትኩረት በማስገኘት አላማ ላይ የተመሰረቱ ክንውኖችን ለማስተግበር ጥረት የሚያደርጉ መሆናቸው?

2.1.2. ተራክቦአዊ ውይይትን በተመለከተ መልመጃዎቹ እርእሰ ጉዳዩን ከተማሪዎች ገጠመኝና ተሞክሮ ጋር በማያያዝ ተሳትፎው ከመምሰል ይልቅ በመሆን ላይ እንዲመሰረት የተማዎችን ሚና ወደፊት ሊገጥም በሚችል የክንውን ልምድ ላይ እንዲጎለብት ለማድረግ በመሞከር፣ የመመራመር ባህልን እንዲያዳብሩና

ሚናን በመጫወት (Role Playing) ችግር ፈች የሆኑ የቋንቋ ትምህርት ተግባራትን ለመለማመድ እንዲችሉ የሚያደርጉ?

2.1.2.1. መጠይቆችን በጥንድ የመሙላት፣

2.1.2.2. የግል ሀሳብን እንዲለዋወጡ የማድረግ፣

2.1.2.3. ከርእሱ ሳይወጡ መረጃዎችን እንዲያነፃጽሩ የማድረግ ክንውኖችን በአዳዲስ ቃላት ማስተዋወቂያነት በመነሻቸው ለማቅረብ ይሞክራሉ?

2.1.3. የቃላት ተግባርን በተመለከተ አዲሶቹ ቃላት የተሰባሰቡባቸውን እርእሶች በመነሻ በሚያስተዋውቅ መልክ ቃላትን እያዛመዱ የተማሪዎችን ስሜት ለማነሳሳት ይሞክራሉ?

2.2. በመልመጃዎቹ ውስጥ የጥናት ክንውኖችን ለማካተት ተሞክሯል?

2.2.1. ሠንጠረዥ በመሙላት ቃላትን የማጥናት ስልትን በተመለከተ በተለይ የቃላት አፈጣጠርንና አጠቃቀምን ለማጥናት የንግግር ክፍሎችን ምእላዳዊ ለውጥና ልዩልዩ ተለዋዋጭ የቃላት ግጥሚያዎች ባህሪያትን የሚያሳውቁ የቃላት ምስረታንና አብሮነት ህግጋትን በማሰስ ከተሳትፎ ወደ ጥናት የክንውን ደረጃ የተሸጋገሩትን ለመመርመር በሚያስችል መልኩ እንዲደራጁ ተሞክሯል?

2.2.2. ክፍት ቦታዎችን በመሙላት ማጥናትን በተመለከተ ቃላትን በተገቢ አውዳዊ ትርጉማቸውና ሰዋሰዋዊ ቦታቸው በመጠቀም አውዳዊና መዋቅራዊ አሰሳዎችን በአዳዲሶቹ ቃላት ላይ ለማካሄድ እንዲያስችሉ ጥረት ተደርጓል?

2.2.3. በማዛመድ ማጥናትን በተመለከተ፣

2.2.3.1. የቃላት ስብስብን ከስእሎች ስብስብ ጋር እማሬያዊ ትርጉሞችን ለማጥናት ፣

2.2.3.2. ግሶችን ከእንስሣት ስእሎች ጋር (የተለዋጮችን አፈጣጠር ሁኔታ ለማጥናት)፣

2.2.3.3. ቃላትና አባባሎችን ከትርጉማቸው ከሚመነጭ ስሜት ጋር ፊሊጦችን ለማወቅ ፣ ወዘተ... በሚያስችል መልክ በማዛመድ የቃላትን ሀይል ለማሳወቅ ይሞክራሉ?

2.2.4. ቃላትን በመወያየት ማጥናትን በተመለከተ የግል እውቀትንና መዝገበ ቃላትን በመጠቀም የንግግር ክሂልን እያዳበሩ ቃላትን ለማሰስ በሚያስችል መልክ እንዲቀርቡ ለማድረግ ተሞክሯል?

2.2.5. በትርጉም ፍለጋ ክንውን አዳዲስ ቃላት ማጥናትን በተመለከተ "እንዲህ ማለት ምን ማለት ነው?" ብሎ በደረቁ ከማፋጠጥ ይልቅ ጥያቄዎቹን ወደ ግል ህይወት በማምጣት ለምሣሌ አዳዲስ የስሜት መግለጫ ቃላትን ደርድሮ "ይህ አይነቱ ስሜት የሚሰማችሁ መቼ ነው?" እያሉ በመጠየቅና ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ አውጡ በሚል አይነት የቃላትን ትርጉም በአሰሳ ለማሳወቅ ይሞክራሉ?

2.2.6. በሁለት ቃላት መሀል ያለን የትርጉም ልዩነት በማሳየት ቃላትን ማጥናትን በተመለከተ ባጠቃላይና በውሱን፣ በእማሬያዊና በፍካሬያዊ፣ ወዘተ... ትርጉሞች በቃላት መሀል ያሉ ልዩነቶችን በመመርመር የአዳዲስ ቃላቱን ባህሪ በአሰሳ ለማስጠናት ይሞክራሉ?

2.3. በመልመጃዎቹ ውስጥ የትግበራ ክንውኖችን ለማካተት ተሞክሯል?

2.3.1. ርዕሶችን በተመለከተ ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት በማራኪ ርዕ ስነት እንዲጠቀሙባቸው፣ የተሰጧቸውን ያልተለመዱ ርዕሶች እንዲገልጹ ፣ ስለ ርእሶቹ ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ፣ ለመፃፍም ሆነ ለመናገር የሚያስችሏቸውን ሀሳቦች እንዲያሰባስቡ በማድረግ ለርእሶቹ መሰረት የሆኑትን አዳዲስ ቃላት በራሳቸው አገላለጽ

በተግባር ላይ እንዲያውሏቸውና ወዘተ... ተግባራትን እንዲፈጽሙ ከላይ በተሳትፎና በጥናት ክንውኖች አሰሳዊ ዘዴ እየዳበረ የመጣውን ትምህርት ውጤት በተግባር እንዲያሳዩ ለማድረግ ያስችላሉ?

2.3.2. ተግባራት ማፃፍን በሚመለከት ቀደም ባሉት ክንውኖች የተማሯቸውን ቃላት በመጠቀምና የየምእራፎቻቸውን አርእስተ ጉዳዮች ሣይለቁ ማስታወቂያዎችን፣ ተዋስኦዎችን፣ ደብዳቤዎችን፣ መጣጥፎችን፣ የግል ገጠመኞችን፣ ልዩ ልዩ ገለፃዎችንና ወዘተ... በመዘርዘራዊ (informative) ፣ በማግባቢያ (propagative) ና በፈጠራ (creative) የአፃፃፍ ስልቶች ለመፃፍ ያስችላሉ?

2.3.3. ታሪክ በመንገር የትግባራ አይነት አዳዲስ ቃላትን መማርን የመማር ተግባራዊ ስልትን በተመለከተ በየምእራፉ ቀደም ባሉት ክንውኖች ከምንባብ አልፈው የንግግር ቃላት ወደ መሆን ተሸጋግረው እንደሆን ውጤቱን በተግባር ይገልጽና በቃላቱ አጠቃቀም የበለጠ ልምድ የመፍጠር ደረጃ ላይ ተደርሶ እንደሁ ይታወቅ ዘንድ ታሪክ ፈጥረው እንዲናገሩባቸው በማድረግ የንግግር ክሂሎችን ለማዳበር ይሞክራሉ?

2.3.4. በግምገማ የቃላት አማማር ስልትን በተመለከተ አንድን ነገር፣ ሁኔታ፣ ድርጊት፣ ወዘተ... ተመልክቶ በራስ አባባል ስያሜ በመስጠት፣ ተግባሩን በመግለጽ፣ በትምህርቱ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በቃላት አሰሳ የተገኙ ተውሳከ ግሶችን ተጠቅሞ ሁኔታዎችን በመግለጽና ወዘተ የማስተላለፊያ ክሂሎችን (productive skills) ለማዳበር ይሞክራሉ?

2.3.5. ሚናን በመጫወት ቃላትን የመተግበር ስልትን በተመለከተ ተማሪዎች ከርእሱ ሳይወጡ በቃለ-ምልልስ፣ በአጫጭር ድራማዎችና ወዘተ... የድርሻቸውን እየተወጡ የተማሯቸውን ቃላት በተግባር ላይ እንዲያውሏቸው የሚያስችሉ ሙከራዎች ተካትተውባቸዋል? (ሀርመርና ሮዝነር፣ 1991፡ix)

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎች ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ሲሳይ ተበጀ

ፊርማ ______________

አድራሻ፡- የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ቀን 30 1 1991

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋንቋዎች ጥናት ተቋም
ድህረ ምረቃ መርሀግብር

ADDIS ABABA UNIVERSITY
INSTITUTE OF LANGUAGE STUDIES
FACULTY GRADUATE COMMISSION

☎ 11-17-35, 55-08-44 Ext. 263 ✉ 1176

ቀን
Date: December 22, 1998
ቁጥር
Ref. No. ILS/FGC/32/98/91

**TO:** Dean, School of Graduate Studies

**FROM:** Akalu Getaneh (Ph.D)
Chairman, Faculty Graduate Commission, ILS

**SUBJECT:** Correction of M.A. Thesis

This is to confirm that Sisay Tebeje has included the necessary corrections into his thesis as recommended by the Examination Committee.

Thank you.